


የአዕምሮ እድገት ውስንነትን በፍቅር

ገጽ 16

በዘመናዊነቱ ሞዴል ተደርጎ የሚወሰደው የየካ-2 መኪና ማቆሚያ ፕሮጀክት



ገጽ 14

እፕድ

# አዲስ ዘመን

82ኛ ዓመት ቁጥር 224 ሚያዝያ 14 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!






# በረመዳን ወር የነበሩ መልካም እሴቶችን እንደሚያስቀጥሉ የእምነቱ ተከታዮች ገለጹ

## - 1444ኛው ኢድ አልፈጥር በትናትናው ዕለት ተከብሮ ውሏል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በረመዳን ወር ስንተገብራቸው የነበሩ መልካም ሥራዎችና የተላበስነውን መልካም ሥነምግባር ከረመዳን በኋላም እናጠናክራለን ሲሉ የእስልምና እምነት ተከታዮች ገለጹ። 1444ኛው ዒድ አልፈጥር በትናትናው ዕለት በመላ ኢትዮጵያ ተከብሯል።

ኢድ አልፈጥርን ለማክበር በአዲስ አበባ ትንሿ ስታዲየም የተገኙት ኡስታዝ ሀሰን መሃመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ሕዝበ ሙስሊሙ በረመዳን ፆም ወቅት ያሳየውን የመረዳዳት፣ የመከባበር እና የተቸገሩትን ወገኖች የመርዳት ተግባር በበዓሉም ሆነ ከበዓል በኋላ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል። ለዚህም የተቸገሩ ወገኖችን መርዳት፣ ተካፍሎ መብላት እና ህሙማንን መጠየቅ ይገባል ብሏል።

በልተን ያልጠገብነው፤ ተኝተን ያላረፍነው ያለንን ማካፈል ባለመቻላችን ነው ያሉት ኡስታዝ ሀሰን፤ በልተን የምንጠግበውና ተኝተን የምናርፈው ያለንን ማካፈል ስንችል መሆኑን ሕዝበ ሙስሊሙ አውቆ ኢድን ከተቸገሩ

በረመዳን ወር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






ሙፈሪያት ካሚል

# «ከመጥፎ ነገር የራቀ፣ የተቸገረን የረዳና መከባበርን ያጎለበተ ሁልጊዜም ኢዱ ነው» - የእምነት አባቶች

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- ከመጥፎ ነገር የራቀ፣ የተቸገረን የረዳና መከባበርን ያጎለበተ ሁልጊዜም ኢዱ ነው ሲሉ የእስልምና እምነት አባቶች ተናገሩ። 1444ኛው ዒድ አልፈጥር በትናንትናው ዕለት ተከብሮ ውሏል።

የ1 ሺህ 444ኛው ኢድ አልፈጥር ላይ የተገኙት ሀጅ ሙሐመድ ሰብዲን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኢድ አልፈጥር በጁምዓ ቀን መከበሩ ደስታችን እጥፍ ድርብ እንዲሆን አድርጓል። ‹‹በቦረና እና በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች በሰው ሠራሽና በተፈጥሮ አደጋ ተፈናቅለው የነበሩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን በመደገፍ የረመዳንን ወር አሳልፈናል። ይህም እምነቱን

«ከመጥፎ ነገር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ሀጅ ሙሐመድ ሰብዲን

ፎቶ፡- ዳኜ አበራ



ኡስታዝ ካሚል ጣሃ



አህመድ ሁሴን

በውጭ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ጥቅምና ደህንነት የሚያስከብር ሕጋዊ ሥርዓት ተዘረጋ

ገጽ 4

ግብርናው ከዝናብ ጥገኝነት ተላቆ ወደመስኖ ሥራ እንዲሸጋገር እየተሠራ ነው

ገጽ 4





# ለበዓላቱ ከ255 ሺህ ኩንታል በላይ ጤፍ በሸማች ማህበራት አማካኝነት ተሰራጭቷል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- ለትንሳኤ በዓል እና ለኢድ አልፈጥር የምርት እጥረት እንዳያጋጥም ከ255 ሺህ ኩንታል በላይ ጤፍ በአዲስ አበባ ከተማ ለሚገኙ ሸማች ማህበራት መሰራጨቱን የኢትዮጵያ ሕብረት ሥራ ኮሚሽን አስታወቀ።

በኢትዮጵያ ሕብረት ሥራ ኮሚሽን የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ወይዘሮ ጫልቱ ታምሩ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የትንሳኤ በዓልና የኢድ አልፈጥርን አስመልክቶ የምርት እጥረት እንዳይፈጠር በከተማዋ ከ255 ሺህ ኩንታል በላይ የጤፍ ምርት እንዲሰራጭ ተደርጓል።

እንደ ወይዘሮ ጫልቱ ከሆነ፤ በአዲስ አበባ ከተማ በ11ዱም ክፍለ ከተሞች በሚገኙ የተለያዩ ቦታዎች ላይ ምርቱ እንዲሰራጭ ተደርጓል። ሕብረት ሥራ ማህበራት ባላቸው የማከማቻና የገንዘብ አቅም መሠረት ምርቶችን ከህብረት ሥራ ኮሚሽኑ ገዝተው አከፋፍለዋል ብለዋል።

በዚህም በማህበራቱ በኩል አንድ ኪሎ ጤፍ በአማካይ በ60 ብር ሲሸጥ የቆየ ሲሆን፣ በርካታ ዜጎችም ምርቱን በተመጣጣኝ ዋጋ ማግኘት ችለዋል ሲሉ ተናግረዋል።

በሸማች ማህበራት በኩል አንድ ኪሎ የስንዴ ዱቄት 60 ብር ሲሸጥ፤ የበቆሎ ዱቄት ደግሞ በኪሎ 37 ብር ለገበያ መቅረቡን ገልጸዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ 138 ሸማች የሕብረት ሥራ ማህበራት የሚገኙ ሲሆን፣ በተጨማሪም በከተማ ዙሪያ 40 ሸማች ማህበራት በሥራ ላይ ናቸው ብለዋል።

ሸማች ማህበራቱ ሦስት የምርት ዓይነቶች በተለይም የግብርና፣ የኢንዱስትሪ ምርቶች እና የእንስሳት ተዋጽኦ ምርቶችን ለሸማቾች በማቅረብ ላይ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

ወይዘሮ ጫልቱ እንደገለጹት፤ ከግብርና ምርቶች የስንዴ፣ የበቆሎ ዱቄት እና ምስር ጤፍ በሕብረት ሥራ ማህበራቱ በኩል ለገበያ እየቀረቡ ይገኛል። ከኢንዱስትሪ ምርቶች ደግሞ ዘይት፣ ፓስታ፣ ማካሮኒ ቀርበዋል። በተጨማሪ በእንስሳት ተዋጽዖ አይብ፣ ቅቤ፣ ዶሮ፣ እንቁላል፣ በግ እና ፍየል ለገበያ ቀርበዋል።

በቀንድ ከብት ደረጃ ጀሞ አካባቢ ጨፌ የሕብረት ሥራ ማህበር የተለያዩ የእርድ እንስሳትን ለኅብረተሰቡ ማቅረቡን ጠቁመዋል።

የኢንዱስትሪ ምርቶችን በተመለከተ ከአጠቃላይ ምርቱ 20 በመቶ ብቻ ለሸማች ማህበራት ይደርሳል ያሉት ወይዘሮ ጫልቱ፤ በመሆኑም ግብይቱን ለማረጋጋት ለሸማቾቸች ማህበራት ሰፊ መጠን ያለው ምርት እንዲቀርብ ጥረት ይደረጋል ብለዋል።

ችግሩን ለመፍታት ኮሚሽኑ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና ከንግድ እና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ጋር በጋራ እየተሠራ ይገኛል ሲሉ ተናግረዋል።

# የጤና ሚኒስትሯ ዒድን ከታካሚዎች ጋር አሳለፉ

**በኃይሉ አበራ**



ፎቶ ገባቦ ገብሬ

አዲስ አበባ፡- የጤና ሚኒስትር ዶክተር ሊያ ታደሰ በየካቲት 12 ሆስፒታል ተገኝተው ታካሚዎች እና የሕክምና ባለሙያዎች ጋር ኢድ አልፈጥርን በጋራ አሳለፉ።

ዶክተር ሊያ በሆስፒታሉ ከሚገኙ የሕክምና ባለሙያዎች እና ታካሚዎች ጋር በዓሉን ያከበሩ ሲሆን፣ በሆስፒታሉ የሕፃናት የቃጠሎ ሕክምና ክፍል የሚገኙ ህመምተኞችንም ጎብኝተዋል።

የሕክምና ባለሙያዎችም የሕክምና ሥራ ላይ በመሆን በዓል እያሳለፉ በመሆኑ ሊመሰገኑ ይገባል ያሉት ዶክተር ሊያ፤ ለመላው ሕዝበ ሙስሊምም መልካም በዓል ተመኝተዋል።

የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ዮሐንስ ጫላ በበኩላቸው ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የጤና ባለሙያዎች ቤታቸውን ጥለው ሁለተኛ ቤተሰባቸው ከሆኑት ታካሚዎቻቸው ጋር በዓልን እያሳለፉ ነው ብለዋል።

የካቲት 12 ሜዲካል ኮሌጅ በዚህ ዓመት 100ኛ ዓመቱን የሚያከብር አንጋፋ ሆስፒታል መሆኑን አስታውሰው ሆስፒታሉ በተለይ በቃጠሎ ሕክምና ክፍል በርካታ የሕክምና ባለሙያዎችን ሲያሰለጥን የቆየና ከመላው አገር ለመጡ ታማሚዎች አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝ ነው ብለዋል።

ሆስፒታሉ ከ600 ሺህ በላይ የሚጠጉ ካርዶችን ከወረቀት ነፃ አድርጎ ሙሉ በሙሉ ዲጂታላይዝ በማድረግ እና ወደ ሌሎች ሆስፒታሎችም በማስፋት እየሠራበት ነው ብለዋል።

ከተማ አስተዳደሩ ጤናው ላይ በልዩ ትኩረት እየሠራ መሆኑን የገለጹት ዶክተር ዮሐንስ፤ ጤናው ላይ መሰማራት ለሚፈልጉ ባለሀብቶች ጭምር መሬት በማቅረብ ከተማዋን አንድ የጤና መዳረሻ ለማድረግ እየተሠራ ነው ብለዋል።

በከተማዋ የጤናውን ዘርፍ ተደራሽ ለማድረግና ሆስፒታል የሌላቸው ክፍለ ከተሞች ላይ የሆስፒታል ማስፋፋት ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ጠቁመዋል።

በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ እና በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለከተሞች ከ450 በላይ አልጋ መያዝ የሚችሉ ዘመናዊ ሆስፒታሎች እንዲሁም ዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል 300 አልጋ የመያዝ አቅም ያለው የማስፋፊያ ግንባታ እየተሠራ መሆኑንም ገልጸዋል። በጥሩነሽ ቤጂንግ ሆስፒታልም ከ200 አልጋ በላይ የሚይዝ የትራኮማ ማዕከል እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

ሆስፒታሉ በከተማዋ ትልቁን የታካሚ ቁጥር የሚይዝ በመሆኑም የሆስፒታሉን ደረጃ በሚመጥንና ቅርስነቱን በጠበቀ መልኩ ክፍሎችን ለማደስም እንደሚሠራም ገልጸዋል።

# ከ180 በላይ ድርጅቶች የፕላስቲክ ቆሻሻዎችን መልሶ ጥቅም ላይ እያዋሉ ነው

## - በዓመት ከሚመረተው ቆሻሻ ስድስት በመቶው ጥቅም ላይ ይውላል

**ሄለን ወንድምነው**



አዲስ አበባ፡- እንደ አገር ከ180 በላይ ድርጅቶች የፕላስቲክ ቆሻሻዎችን መልሰው ጥቅም ላይ እንዲውሉ የማድረግ ሥራ እያከናወኑ እንደሚገኙ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን አስታወቀ። በዓመት ከሚመረተው 380 ሺህ ቶን የፕላስቲክ ቆሻሻ ስድስት በመቶው ጥቅም ላይ እንደሚውል አስታውቋል።

በኢፌዴሪ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ሕግ ተከባሪነት ዳይሬክተር አቶ ግርማ ገመቹ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ እንደ አገር ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ ተሰብስበው ጥቅም ላይ የሚውሉ የፕላስቲክ ቆሻሻዎችን የማብዛት ሥራ የተለያዩ ድርጅቶች እየሠሩ ይገኛሉ።

ከ180 በላይ ድርጅቶች የተለያዩ የፕላስቲክ ቆሻሻዎች ሰብስበው መልሰው ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል የተለያዩ ሥራዎችን እያከናወኑ ይገኛሉ ያሉት አቶ ግርማ፣ የፕላስቲክ ቆሻሻዎች ተፈጭተው ወደ ውጭ አገር ከመላክ ጀምሮ በአገር ውስጥ ለግንባታ ቁሳቁስ የሚያገለግሉ የተለያዩ ጥሬ ዕቃዎች እየተመረቱ እንደሚገኙ አስታውቀዋል።

መልሰው ጥቅም ላይ የሚውሉት የፕላስቲክ ቆሻሻዎች ለግንባታ ግብዓቶች ለኮንክሪት፣ ለመጠቅለያ፣ ለግድግዳ ንጣፎች እና ተያያዥ አገልግሎቶች ጥቅም ላይ የሚውሉ ሲሆን፤ በአገሪቱ ያለውን ከፍተኛ የግንባታ ግብዓት ፍላጎት ለማሟላት ያግዛል ብለዋል።

በተጨማሪም የፕላስቲክ ኮዳዎች ተፈጭተው ወደ ውጭ አገር እንዲላኩ በማድረግ የውጭ ምንዛሬን ለማስገኘት ፋይዳቸው የጎላ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

እንደ አገር በዓመት 380 ሺህ ቶን የፕላስቲክ ቆሻሻ የሚመረት ሲሆን፤ ስድስት በመቶ የሚሆነው መልሶ ጥቅም ላይ ይውላል ሲሉ አቶ ግርማ አስታውቀዋል።

የፕላስቲክ ቆሻሻን በዘላቂነት ጥቅም ላይ ለማዋል የፕላስቲክ ቆሻሻ አመንጪዎች የክፍያ ሥርዓት የለም። በመሆኑም አብዛኛው ቆሻሻ የመሰብሰብ ሥራ የሚከናወነው በመንግሥት ነው። ይህ ደግሞ አሰባሰቡ ደካማ እንዲሆን፣ መልሶ ጥቅም ላይ የሚውለው የፕላስቲክ ቆሻሻ መጠን አናሳ እንዲሆንና በሚፈለገው ልክ ማምረት እንዳይቻል አድርጎታል ሲሉ አስረድተዋል።

የፕላስቲክ ቆሻሻዎችን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል አካባቢያዊ፣ ማህበራዊ እና ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ አለው ያሉት አቶ ግርማ፤ አካባቢያዊ ጠቀሜታው በፕላስቲክ ቆሻሻ አማካኝነት በአካባቢው የሚደርሰውን የአየር፣ የውሃ፣ የአፈር እና የመሠረተ ልማት ብክለት ማስቀረት ነው ብለዋል።

ማህበራዊ አገልግሎቱ ደግሞ በርካታ ወጣቶች በተለያዩ ከተሞች ላይ የፕላስቲክ ቆሻሻዎችን እየለቀሙ የዕለት ጉርሳቸውን ከማሟላት ባለፈ ቋሚ የሥራ ዕድል መፍጠር እንዲችሉ አድርጓቸዋል ሲሉ አብራርተዋል።

አዳዲስ ጥሬ ዕቃ ከውጭ አገራት ገዝተን የምናስገባው እንዳለ ሆኖ የፕላስቲክ ኮዳዎች ተፈጭተው ወደ ውጭ መላክ በመቻላችን የውጭ ምንዛሬ እንድናገኝ በማድረጉ ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳው የጎላ ነው ሲሉም አቶ ግርማ ገልጸዋል።




# በትግራይ ከሚያዝያ 21 ጀምሮ ተጓዥ ባዛር ይካሄዳል

**ማርቆስ በላይ**

አዳስ አበባ፡- በትግራይ የንግድ ሥርዓቱን ለማነቃቃት የትግራይ የንግድ እንቅስቃሴ ለቀጣናዊ ሰላም በሚል መሪ ሃሳብ ተጓዥ ባዛር በተለያዩ የትግራይ ከተሞች እንደሚካሄድ የንግድና ቀጣናዊ ትስስርና የትግራይ ንግድ ማህበራት ዘርፍ አስታወቁ።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ የትግራይ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት እና የኢትዮጵያ ንግድ ማህበራት ዘርፍ ምክር ቤት ጋር በጋራ በሰጡት መግለጫ ላይ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር የንግድ ሥርዓትና ላይሰንሲንግ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ተሻለ በልሁ እንደገለጹት፣ ባዛሩ ባለፉት ሁለት አመታት ተቋርጦ የነበረውን የትግራይ ክልል የንግድ ሥርዓት ወደ ነበረበት ለመመለስ የሚያስችል ነው።

እንደ አቶ ተሻለ ገለጻ ተጓዥ የንግድ ባዛሩ በሚያዝያ 21 ቀን የፌዴራልና የክልል ከፍተኛ ባለሥልጣናት በተገኙበት በመቀሌ ከተማ ይከፈታል።

ተጓዥ ባዛሩ በተለያዩ የክልሉ ከተሞች የሚካሄድ መሆኑን የገለጹት ሚኒስትር ዴኤታው በመቀሌ፣ በውቅሮ፣ በአዲግራትና በማይጨው ከተሞች ይካሄዳል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ንግድ ማህበራት ዘርፍ ተወካይ ዶክተር ደገላ አርጋኖ በበኩላቸው ተጓዥ ባዛሩ ተቋርጦ የነበረውን የንግድ እንቅስቃሴ ለማነቃቃት የሚያስችልና ለአንድ ወር የሚቆይ ነው።

የትግራይ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ተወካይ አቶ ካሳዬ ላዕከ በበኩላቸው በባዛሩ መሠረታዊ ሸቀጦች ወደ ክልሉ ተጉዘው የንግድ ሥርዓቱን ወደ ነበረበት በመመለስ ኅብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ ከፍተኛ እገዛ እንደሚኖራቸው ተናግረዋል።

ባዛሩ የትግራይ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ከአምነን ማርኬትና ፕሮሞሽን ጋር በመተባበር የሚካሄድና ለአንድ ወር የሚቆይ መሆኑ ተገልጿል።

# በመዲናዋ 501 አካባቢዎች ለአደጋ ተጋላጭ ናቸው

**መስከረም ሰይፉ**



አቶ ፍስሀ ጋርደው

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙ 501 አካባቢዎች ለአደጋ ተጋላጭ መሆናቸውን የአዲስ አበባ እሳት አደጋ ሥራ አመራር ኮሚሽን አስታወቀ። በከተማዋ በዘንድሮው ዓመት ብቻ ከ300 በላይ የእሳት አደጋ መድረሱ ተጠቁሟል።

«እኛም ሚና አለን» በሚል መሪ ቃል ከአርቲስቶችና ከጋዜጠኞች ጋር በተካሄደው የውይይት መድረክ ላይ የኮሚሽኑ ዋና ኮሚሽነር አቶ ፍስሀ ጋርደው እንደገለጹት፤ ኮሚሽኑ በ2015 ዓ.ም በዩኒቨርሲቲዎች ባሠራው ጥናት አዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙ 501 አካባቢዎች የአደጋ ተጋላጭ መሆናቸው ተለይቷል።

ከተለዩት የአደጋ ዓይነቶችም 219 አካባቢዎች ለእሳት፣ 180 አካባቢዎች ለጎርፍ ፣ 78 አካባቢዎች ለመሬት መንሸራተትና 24 አካባቢዎች ለትራፊክ አደጋዎች ይበልጥ ተጋላጮች መሆናቸው ታውቋል ብለዋል።

አካባቢዎቹን ለአደጋ ተጋላጭ ያደረጓቸው ዋና ዋና መንስኤዎችም የመሬት አቀማመጣቸው፣ የመሬት አጠቃቀሙ ደረጃውን የጠበቀ አለመሆን፣ የፍሳሽ ማስወገጃዎች በቆሻሻ መደፈንና በየመንገዱ ከዳናቸው የሚነሳ የመንገድ ጉድጓዶች ዋና ዋናዎቹ መሆናቸውን ተጠቅሷል።

አዲስ አበባ ከተማ ከ2011 ዓ.ም እስከ 2015ዓ.ም ድረስ ከሁለት ቢሊዮን 237 ሚሊዮን ብር በላይ በድንገተኛ አደጋዎች ምክንያት ኪሳራ ማጋጠሙን አውስተው፤ የአደጋ ቁጥጥር ሠራተኞች አደጋዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ባደረጉት ጥረትም ከ60 ቢሊዮን 284 ሚሊዮን ብር በላይ ማዳን መቻሉን ዋና ኮሚሽነሩ አብራርተዋል።

ኮሚሽኑ አደጋን ለመቀነስና ለመከላከል በሚደረገው ዝግጅት በሰው ኃይልና በግብአቶች የሚወሰን ቢሆንም ያሉት ዘጠኝ ቅርንጫፎችና ሠራተኞች በቂ አለመሆናቸውን ጠቅሰዋል።

እንደ ዋና ኮሚሽነሩ ገለጻ፤ ተቋሙ አቅሙን ለማሻሻል አንድ ነጥብ 10 ቢሊዮን ብር ያስፈልገዋል።

ተቋሙ በርካታ ማሻሻዎችን እያደረገ መሆኑንና ከዚህ ቀደም ወደ አደጋ መቀበያ ስልክ በቀን ሦስት ሺ የሚሆኑ ሰዎች ለስድብና ለፌዝ ይደውሉ ነበር ያሉት ኮሚሽነሩ፤ በአሁኑ ጊዜ ይኸው የስልክ መስመር በመዲናዋ ብቻ እንዲታጠርና የደዋዩ ማንነት እና አድራሻ ጭምር እየተመዘገበ ተጠያቂ የሚሆንበት አሠራር በመፈጠሩ ይህን ችግር መፍታት መቻሉን ገልጸዋል።

በተጨማሪም የእሳትና አደጋ ሥራ አመራር ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አቶ ይከፈለው ወልደመስቀል በአዲስ አበባ ከተማ አደጋን ለመከላከል አስቀድሞ የሚሠራው ሥራ ዝቅተኛ በመሆኑ አደጋዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ መሆኑን ተናግረዋል።

በመዲናዋ የሚገኙ በርካታ ተቋማት አደጋን ለመከላከል መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶችን የማያሟሉ መሆኑን አመልክተው፤ በመዲናዋ ከሚገኙ አምስት ሺ ከሚሆኑ ተቋማት መስፈርቱን አሟልተው የተገኙት 25 ብቻ መሆናቸውን አመልክተዋል።

በከተማው ካሉ 108 ባለ ኮከብ ሆቴሎች ውስጥ አስተማማኝ የእሳት አደጋ መቆጣጠሪያ ያሟሉት 13 ብቻ መሆናቸውን ጠቁመው፤ በመዲናዋ ውስጥ ከሚገኙ 605 ፋብሪካዎች ውስጥ ደግሞ አምስቱ ብቻ የአደጋ መከላከል የጥራት ማረጋገጫ ያላቸው መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

እንደ አቶ ይከፈለው ገለጻ፤ በከተማዋ በዘንድሮው ዓመት ብቻ ከ300 በላይ የእሳት አደጋ ደርሷል። ይህም የእሳት አደጋን አስቀድሞ ለመከላከል ብዙ ሥራ እንደሚጠይቅ አመላካች ነው።

# የባቱ - ሀዋሳ የፍጥነት መንገድ ግንባታ 57 በመቶ ደርሷል

**ሳሙኤል ወንደሰን**



አዲስ አበባ፡- የሞጆ - ሀዋሳ የፍጥነት መንገድ አካል የሆነው የባቱ - አርሲ ነገሌ- ሀዋሳ የፍጥነት መንገድ የግንባታ አፈጻጸም 57 በመቶ መድረሱን የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር አስታወቀ።

የባቱ - አርሲ ነገሌ- ሀዋሳ የፍጥነት መንገድ ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ አቶ አዲስሕይወት ታደሰ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የሞጆ - ሀዋሳ የፍጥነት መንገድ አካል የሆነው የባቱ - አርሲ ነገሌ እና የአርሲ ነገሌ - ሀዋሳ የፍጥነት መንገድ ግንባታዎች የእያንዳንዳቸው የግንባታ አፈጻጸም 57 በመቶ ደርሷል።

የባቱ - አርሲ ነገሌ እና የአርሲ ነገሌ - ሀዋሳ 109 ነጥብ አንድ ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው የፍጥነት መንገድ መሆኑን የተናገሩት ሥራ አስኪያጁ፤ ፕሮጀክቱን በሦስት ዓመት ተኩል ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም የሲሚንቶ እጥረት እና የመሬት ወሰን ችግሮች አፈፃፀሙን አዘግይተውታል ብለዋል።

የፕሮጀክቱን ተግዳሮቶች ለመቅረፍ እና የፕሮጀክቱን ፈጣን ፍጻሜ ለማረጋገጥ በመንግሥትና በባለድርሻ አካላት የተቀናጀ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ የቻይና ኤግዚም ባንክ 52 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው የአርሲ ነገሌ - ሀዋሳ መንገድ ፕሮጀክት አምሥት ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር ወጪ በማድረግ የበጀቱን 85 በመቶ እንደሸፈነ ጠቅሰዋል። ቀሪው የፕሮጀክቱ በጀት የተሸፈነው በኢትዮጵያ መንግሥት መሆኑን አክለው ተናግረዋል።

እንደ ሥራ አስኪያጁ ገለፃ፤ የሞጆ - ሀዋሳ የፍጥነት መንገድ ግንባታ በአራት ምዕራፎች ተከፍሎ እየተሠራ የሚገኝ ፕሮጀክት ነው። የፕሮጀክቱ የመጀመሪያ ምዕራፍ ከሞጆ - መቂ፤ ሁለተኛው ከመቂ - ባቱ፤ ሦስተኛውና አራተኛው ምዕራፍ ደግሞ ከባቱ - አርሲ ነገሌ እና ከአርሲ ነገሌ - ሀዋሳ በመባል የተከፈለ ነው።

የፍጥነት መንገዱ ምዕራፍ አንድ ሞጆ - መቂ እና ምዕራፍ ሁለት መቂ - ባቱ ከዚህ ቀደም ተጠናቅቀው ለትራንስፖርት አገልግሎት ክፍት ተደርገዋል ያሉት አቶ አዲስሕይወት፤ የባቱ - አርሲ ነገሌ እና የአርሲ ነገሌ - ሀዋሳ የፍጥነት መንገድ ግንባታ በ2016 የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ይጠናቀቃል ተብሎ ይጠበቃል ብለዋል።

የሞጆ - ሀዋሳ የፍጥነት መንገድ ግንባታ ለዘላቂ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ከፍተኛ ድርሻ ያለው እና በመስመሩ ላይ የሚገኙትን ወረዳዎች፣ ከተሞችና የእርሻና የኢንዱስትሪ ቦታዎችን የሚያገናኝ ነው ያሉት ሥራ አስኪያጁ፤ የቱሪስት መስህብ የሆኑ ቦታዎችን ለማገናኘት እና ከአዲስ አበባ-ሞያሌ - ናይሮቢ - ሞምባሳ ያለውን የኢትዮጵያን የወጪና የገቢ ንግድ እንቅስቃሴ በከፍተኛ ሁኔታ ለማሳለጥ የሚረዳ መንገድ ነው ብለዋል።

መንገዱ 10 ሺህ ኪሎ ሜትር የሚሸፍነው የታላቁ የምሥራቅ አፍሪካ ኮሪደር የካይሮ- ደቡብ አፍሪካ ኬፕታውን ትራንስ አፍሪካን ሃይዌይ አካል ነው።

ዜና



ፕሮፌሰር እያሱ ኤሊያስ

# ግብርናው ከዝናብ ጥገኝነት ተላቆ ወደመስኖ ሥራ እንዲሸጋገር እየተሠራ ነው

## - እስካሁን 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በመስኖ ለምቷል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- ግብርናው ከዝናብ ጥገኝነት ተላቆ ወደመስኖ ሥራ እንዲሸጋገር በትኩረት እየተሠራ ነው ሲሉ በግብርና ሚኒስቴር የተፈጥሮ ሀብት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ፕሮፌሰር እያሱ ኤሊያስ ገለጹ። በኢትዮጵያ በተለያዩ የውሃ አማራጮች 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በመስኖ ማልማት እንደተቻለ የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

ፕሮፌሰር እያሱ ኤሊያስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ግብርና ላይ የተመሠረተ ቢሆንም ግብርናው ዝናብ ላይ ጥገኛ ሆኖ በመቆየቱና በአየር ለውጥ ምክንያት የዝናብ መቆራረጥ ሲያጋጥም ጫና ይደርስበታል።

ጫናውን ለመቀነስ በዋናነት በዝናብ ጥገኝነት ላይ ተመስርቶ ለበርካታ ዓመታት ሲሠራበት የቆየውን አሠራር ወደመስኖ ልማት እንዲቀየር ሰፊ ጥረት እየተደረገ ይገኛል ብለዋል።

እንደ ፕሮፌሰር እያሱ ገለጻ፤ ቀደም ሲል በአገር አቀፍ ደረጃ 800 ሺህ ሄክታር መሬት ብቻ በመስኖ ውሃ አማራጭ ይለማ ነበር። ከሦስት ዓመት ወዲህ በተለይ ከበጋ መስኖ ልማት መስፋፋት ጋር ተያይዞ 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በክረምትና በበጋ መስኖ ማልማት ተችሏል።

በሰፋፊ እርሻዎች፣ በአርሶና አርብቶ አደሮች እንዲሁም በቤተሰብና በማህበረሰብ ደረጃ ጥቅም ላይ የሚውሉ የውሃ መስኖ አማራጮችን በማስፋት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ጥረት መደረጉን ጠቁመዋል።

አብዛኛው የመስኖ ሥራ የሚሠራው ቆላማ አካባቢዎች ላይ ሲሆን ትልልቅ ወንዞችና ሊለማ የሚችል ሰፊ መሬት ባለበት ቦታዎች ላይ የመስኖ ልማቱ እየተስፋፋ መሆኑን ፕሮፌሰር እያሱ አስታውቀዋል።

ከዝናብ ያልተላቀቀ ግብርና ድርቅና ጎርፍ እየተፈራረቀበት ዘላቂና የተረጋጋ ኢኮኖሚ መፍጠር አያስችልም ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የተለያዩ አገራትን ልምድ ከአገራችን ዕውነታ ጋር በማጣጣም መስኖ ልማት ዘላቂ የግብርና ምርታማነትን ለማረጋገጥ ወሳኝ በመሆኑ እየተሠራበት ይገኛል ብለዋል።

ከዝናብ የተላቀቀ የግብርና ሥርዓትን ለመገንባትና አርሶ አደሩ በበለጠ በመስኖ ልማት ሥራ እንዲሳተፍ ለአርሶ አደሩ የውሃ መሳቢያ ፓምፖችንና ተያያዥ መሣሪያዎችን በየጊዜው እያቀረበ ይገኛል ሲሉ ተናግረዋል።

በተጨማሪ ለአርሶአደሮች በውሃ አጠቃቀም፣ የአመራረት ሥርዓትና የተለያዩ የአቅም ማጎልበቻ ጉዳዮች ላይ ስልጠናዎች እየተሰጠ እንደሚገኝ ፕሮፌሰር እያሱ አስረድተዋል።

ሚኒስትር ዴኤታው እንደገለጹት፤ ከመስኖ ልማቱ ጋር በተያያዘ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራን ውጤታማነት ለመጨመር ኅብረተሰቡ በባለቤትነት መንፈስ የሚሠራባቸው መንገዶች መጠናከር አለባቸው።

# የእንግሊዘኛ መማሪያ መጻህፍትን ወደ ቪዲዮ በመቀየር ትምህርት እየተሰጠ ነው

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡ የሁለተኛ ደረጃ የእንግሊዘኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍትን ወደ ቪዲዮ በመቀየር የኦንላይን ትምህርት እየተሰጠ መሆኑን የትምህርት ሚኒስቴር ገለጸ።

በትምህርት ሚኒስቴር የአይሲቲና ዲጂታል ትምህርት ዋና ስራ አስፈጻሚ ዶክተር ዘላለም አሰፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ከ9ኛ እስከ 12ኛ ያሉ የእንግሊዘኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍትን ወደ ቪድዮ በመቀየርና ዲጂታላይዝ በማድረግ በካሪኩለሙ መሰረት እንዲሁም ለሌሎች ከቅድመ መደበኛ እስከ 8ኛ ላሉ ክፍሎች መሰረታዊ ክህሎቶች ላይ በማተኮር የእንግሊዘኛ ቋንቋ የኦንላይን ትምህርት እየተሰጠ ነዉ።

እንደ ዶክተር ዘላለም ገለጻ ትምህርቱ የሚሰጠዉ እንደ መደበኛ ሳይሆን ለመደበኛ ትምህርቱ አጋዥ እንዲሆን ነዉ። የኦንላይን ትምህርቱ ጥሩ ይዘቶች ያሉት እና በአለምአቀፍ ደረጃ ጥሩ የሚባሉ እንደ ብሪቲሽ ካዉንስል ያሉ ተሳትፈዉበት መምህራንም ተቀርጸዉ ለተማሪዎች የሚያቀርቡት ነዉ።

ለርን ኢንግሊሽ (learn Engilish) የተሰኘዉ የኦንላይን ትምህርት ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በመተባበር እንደሚሰጥ ጠቁመዉ ተማሪዎች ያለምንም ክፍያ በቀላሉ በእጅ ስልክ ወይም በኮምፒዩተር ትምህርቱን በነጻ አዉርደዉ መከታተል እንደሚችሉ ገልጸዋል።

በገጠር አከባቢ ለሚኖሩና ኢንተርኔት ማግኘት ለማይችሉ ተማሪዎች የተቀረጹ ትምህርቶችን በሲዲ በማድረግ የሚሰጣቸዉ ሲሆን በፕላዝማ እና ትምህርት ቤት ዉስጥ ባሉ የኮምፒውተር ላብራቶሪዎች በመጠቀም ትምህርቱን መከታተል እንደሚችሉ ገልጸዋል።

የትምህርትን ጥራት ከሚጠብቁ ነገሮች ዋነኛዉ ትምህርትን በቴክኖሎጂ መደገፍ እንደሆነ የሚናገሩት ዶክተር ዘላለም የኦንላይን ትምህርቱ የተማሪዎችን እንግሊዘኛ ቋንቋ የመናገር ፣የመስማት ፣የማንበብ እና የመጻፍ ክህሎቶችን በማሳደግ ረገድ ትልቅ አስተዋጾ ያለዉ በመሆኑ ተማሪዎች https://learnenglish.moe.gov.et የሚለዉን ድህረገጽ በመጎብኘት ትምህርቱን መከታተል እንደሚችሉ ተናግረዋል።

አጠቃላይ ትምህርት ላይ ብዙ መስራት እንደሚጠበቅ የሚናገሩት ዶክተር ዘላለም፤ ተማሪዎች የሚያጋጥማቸዉን የመጽሀፍት እጥረት ለመቅረፍም ሁሉንም የመማሪያ መጻህፍቶቻቸዉን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ካዘጋጀዉ ዲጂታል ላይብረሪ ማግኘት እንደሚችሉ ጠቁመዋል።

ዲጂታል ላይብረሪዉ ብዙ ተማሪዎች እየተጠቀሙበት እንደሆነ ገልጸዉ ሁሉም የአንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ዲጂታል ላይብረሪዉን https://elearn.moe.gov.et ብለዉ በመግባት በነጻ መጠቀም እንደሚችሉ ጠቁመዋል።

ትምህርትን በቴክኖሎጂ የመደገፍ ሂደት ላይ አሁን ላይ እንደ ችግር ሊነሳ የሚችለዉ አብዛኞቹ ተማሪዎች በገጠር አከባቢ የሚኖሩ በመሆኑ ኢንተርኔት የማግኘት ችግር ሊገጥማቸዉ መቻሉ እንዲሁም የእጅ ስልክ ወይም ታብሌት በማስፈለጉ መሆኑን የገለጹት ዶክተር ዘላለም፤ በየትምህርት ቤቱ አነስተኛ የኮምፒዩተር ላብራቶሪ ቢኖር ችግሩን መቅረፍ እንደሚቻልም ጠቁመዋል።

ባንኮች፣ለትርፍ ያልተቋቋሙ የእርዳታ ድርጅቶች፣ ወላጆች፣ የልማት ድርጅቶች እና ነጋዴዎች ማህበራዊ ሃላፊነታቸዉን በመወጣት በሚችሉት ዓቅም ትምህርት ቤት ድረስ ወርደዉ ለተማሪዎች ዉድ ያልሆኑ ታብሌቶችን በመግዛት እገዛ እንዲያደርጉና ትምህርትን በቴክኖሎጂ ለማገዝ የሚደረገዉ ጥረት አካል እንዲሆኑ ዶክተር ዘላለም ጥሪ አቅርበዋል።

# በረመዳን ወር የነበሩ መልካም እሴቶችን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ሰዎች፣ ከተፈናቀሉ ዜጎች እና ከስደት ተመላሾች ጋር በመሆን ለማክበር ከምን ጊዜውም በላይ ተነሳሽነቱ ጨምሯል ብለዋል።

አቶ መሀመድ ሙዘየር በበኩላቸው፤ ኢድ አልፈጥር በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ ትልቅ ትርጉም አለው። ኢድ አልፈጥር ማለት በረመዳን ወር የሠራናቸው ሥራዎችን ውጤት የምንቀበልበት ዕለት ነው። ስለዚህ ኢድን የረመዳን ፆም ትሩፋት በመሆኑ ከተቸገሩ ሰዎች ጋር በመሆንና በመደገፍ የምናከብረው በዓል ነው። ይህም እውነተኛ የበዓል እርካታና ደስታ እንድናገኝ ያስችላል ብለዋል።

በረመዳን ወር ውስጥ ስንተገብራቸው የነበሩ መልካም ሥራዎችና የተላበስናቸውን ሥነምግባር ከረመዳን በኋላም ማስቀጠል ይገባል። በረመዷን ወር ያዳበርናቸው መልካም ሥራዎች ከረመዳን ውጪም ከሕይወት ጋር ተቀናጅተው ኢስላማዊ ስብዕና በመላበስ ማስቀጠልና ከፈጣሪ ጋር ያለውን ትስስር ማጠናከር ይኖርብናል ብለው፤ የኢድ አልፈጥር በዓል ሙስሊሙ ኅብረተሰብ በፆም ወቅት የሠራቸውን መልካም ተግባራትና ዱዓ ተቀባይነት እንዲያገኙ የበለጠ በጎ ተግባር የሚሠራበት ዕለት ነው ብለዋል።

በአእምሯችን እና በልባችን ላይ እዝነት፣ በረከት እና ሰላምን ከሚያጎናፅፈው የረመዳን ወር በኋላ በአንድነት የረመዳንን ፍፃሜ የምናደርግበት ኢድ አልፈጥር በመድረሱ ተደስተናል። ይህ ትልቅ ዕድል በእኛ አቅም የገጠመን ሳይሆን በአላህ መልካም ፈቃድ መሆኑን አውቀን ሁላችንም ኢድን በምስጋና ማክበር ጀምረናል ብለዋል።

«ኢድን ለማክበር ሕዝበ ሙስሊሙ በየዓመቱ ከተለያዩ ቦታዎች ወደስታዲየም ይመጣል። ይህም ኢድን የአንድነት፣ የፍቅርና የመተሳሰብ ባህላችንን የሚያጠናክር መሆኑን የሚያሳይ ነው» ያሉት የእምነቱ ተከታዮች፤ የአገሪቱን አንድነትና የሕዝብን ሰላም ለመጠበቅ ሁሉም በየሃይማኖቱ በዱዓ ማገዝ ይኖርበታል ብለዋል።፡

እንደአገር የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመታገል ለዘመናት ያዳበርናቸውን ጠንካራ እሴቶች በማጠናከር ለሰላምና ለአንድነት መሥራት ያስፈልጋል፤ በዚህ ረገድ ወጣቱ ትውልድ ለአገሪቱ ሰላም ዘብ ሊቆም ይገባል ያሉት የእምነቱ ተከታዮች፤ ከሌላ እምነት ተከታዮች ጋር ሰላምንና አንድነትን በሚያጠናክር መልኩ በዓሉን እንደሚያከብሩት ተናግረዋል።

# «ከመጥፎ ነገር የራቀ፣ የተቸገረን የረዳና...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ከመከተል ባሻገር ትልቅ ደስታ ፈጥሮልናል። ኢድ አልፈጥር ሲከበር ደጋፊ ቤተሰብ ለሌላቸው አቅመ ደካሞች ያለንን በማካፈል ነው»።

የኢድ አልፈጥር ትልቁ ደስታ ያለንን ተካፍሎ መብላት ነው ያሉት ሀጅ ሙሐመድ፤ እንደ አገር ለመለወጥ የእምነቶች ሁሉ እሴት የሆነውን መቻቻልና መከባበርን ልናጎለብት ይገባል። ሰላም ከምንም ነገር በላይ ነው፤ እስላም ማለት ደግሞ ሰላም እንደመሆኑ መጠን የሰላም ደቀ መዛሙርት ልንሆን ያስፈልጋል። ይህ ሲሆን ለአገር ሰላምና ደህንነት መከበር ሚናው ከፍተኛ ነው። ለዚህም ሕዝበ ሙስሊሙ ለአገር አንድነትን ለማስጠበቅ የእምነቱን አስተምህሮ መጠበቅ ያስፈልጋል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ኩሩ፤ ጨዋና እንግዳ ተቀባይ ሕዝብ መሆኑን የገለጹት ሀጅ ሙሐመድ፤ ኢትዮጵያ የተለያዩ ማንነቶችና የእምነት ተከታዮች የሚገኙባት አገር ናት። ስለዚህ ከሁሉም የእምነት ተከታዮች ጋር ተቻችሎና ተከባብሮ በአንድነት ለአገር ልማትና ዕድገት የበለጠ በመሥራት አንድነቷ የተጠበቀች ኢትዮጵያን መፍጠር እንደሚገባ ገልጸዋል።

ኡስታዝ ካሚል ጣሃ በበኩላቸው፤ አገር ሰላም በመሆኑ ሙስሊሙ ማህበረሰብ በአንድነት ወጥቶ ኢዱን አክብሯል። ኢድ የአንድነት በዓል ነው፤ ሁሉም በየአካባቢው በአንድ ሜዳ ላይ በመሰባሰብ አንድነቱን፣ ፍቅሩን፣ እዝነቱንና መተሳሰቡን የሚገልጽበት ልዩ በዓል ነው። ኢድን ከሌሎች ሶላቶች ልዩ የሚያደርገው ይህ በአንድነት በመሰባሰብ አብሮነትን ለማስቀጠል የሚያስችል የአንድነት መገለጫ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በረመዳን ጾም ሶላት ከመሰገዱ በፊት አንድ አባወራ እንደየቤተሰቡ መጠን ያለውን እንዲያካፍል ይታዘዛል ያሉት ኡስታዙ፤ ይህ የሆነው ከአንዱ ቤት የኀዘን ከአንዱ ቤት የደስታ ስሜት እንዳይፈጠርና ሁሉም እንዲደሰት ነው። ኢድ የሚከበረው ለአንድ ቀን ብቻ አይደለም። ስለዚህ ከመጥፎ ነገር የራቀ፣ የተቸገረን የረዳ መከባበርን ያጎለበተ ካለ ሁልጊዜም ኢዱ ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ የብዙ ብሔረሰቦች፤ የበርካታ እምነቶች ያሉባት አገር ናት። ስለዚህ አንዱ አንዱን መተቸት የእምነታችን አስተምህሮ አይፈቅድም። መተሳሰብና መከባበር ከሌለ እንደ አገር አደጋ ይደቀናል። ስለዚህ አንድነትን ማጠናከር ያስፈልጋል።

አቶ አህመድ ሁሴን በበኩላቸው፤ አገራችን በሰላም እንድትቀጥል የአላህን ሕግጋቶች ጠብቆ መጓዝ ተገቢ ነው። አገራችን ላይ ጉዳት ያደረሱ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ ከስተቶች አልፈዋል። እሱን ታሳቢ በማድረግ ኢድን ማክበር ከሙስሊሙ ማህበረሰብ ይጠበቃል።

እምነት በአገር ላይ መከበር የሚችለው አገርን ስናስቀድም ነው። ጥሩ ያልሆኑ ልዩነቶችን ወደ ጎን በመተው ተከባብሮ መኖር ያስፈልጋል። የኃይማኖት አባቶችም ሥነ ምግባር የተላበሰ ትውልድ እንዲኖር ሰላምን፤ ፍቅርን አብዝቶ መስበክ አለባቸው። «አላህ ለከፉዎች ዋጋቸውን እሰጣለሁ» ይላልና ከፉ የሚያስቡትን በመምከር ሰላምን ማስቀጠል እንደሚገባ አቶ አህመድ ገልጸዋል።

1 ሺህ 444ኛው ኢድ አልፈጥር ትናንት በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ በደማቅ ሁኔታ ተከብሯል።

# በውጭ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ጥቅምና ደህንነት የሚያስከብር ሕጋዊ ሥርዓት ተዘረጋ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በውጭ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ጥቅም፣ መብትና ደህንነት ማስከበር የሚያስችል ሕጋዊ ሥርዓት መዘርጋቱን የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር አስታወቀ።

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ሚኒስትር ሙፈሪያት ካሚል ከውጭ አገራት የሥራ ስምሪት ጋር ተያይዞ የተገኙ ውጤቶችን በተመለከተ መግለጫ ሰጥተዋል።

በሚኒስትር ሙፈሪያት ካሚል የተመራ ልዑክ በቤይሩት፣ በሊባኖስና በሳዑዲ አረቢያ ተዘዋውሮ ዜጎች የተሻለ ደመወዝ እንዲከፈላቸው፣ መብትና ደህንነታቸው እንዲከበር ለማድረግ ከአገራቱ መንግሥታት ጋር ስምምነት መደረጉን በሰጡት መግለጫ አስታውቀዋል።

የተደረሰው ስምምነት ዜጎች ወደነዚህ አገራት በሕጋዊ መንገድ ገብተው መሥራት እንዲችሉ ያደርጋል ያሉት ሚኒስትሯ፤ የአገሪቱ መንግሥት ከአሠሪዎች አያያዝ፣ ከሠራተኞች ደመወዝ ክፍያ፣ ከእረፍት ጊዜ አሰጣጥ፣ ከመብት እና ደህንነት አጠባበቅ አንጻር ክትትል እንደሚያደርግ አስታውቀዋል።

የተዘረጋውን ሥርዓት ተከትለው በሕጋዊ መንገድ ወደ ሊባኖስ አገር ለሚሄዱ ሠራተኞች ትርጉም ያለው ደመወዝ እንዲከፈላቸውና መብትና ደህንነታቸው እንዲጠበቅ ያስችላል ብለዋል።

በሳዑዲ አረቢያ በነበራቸው ቆይታ ከፍተኛ የሠራተኛ ፍላጎት መኖሩን ማረጋገጣቸውን የጠቀሱት ወይዘሮ ሙፈሪያት፤ ሠራተኞች ትርጉም ያለው የደመወዝ ጭማሪ እንዲደረግ፣ መብትና ደህንነታቸው እንዲጠበቅ ተነጋግረናል ብለዋል።

ስምምነቱን ከዚህ በፊት ሠራተኞች በሕገወጥ መንገድ ሲኖሩ ሕጋዊ ከለላ እንዳይኖራቸው ይደረጉ የነበሩትን ችግሮች ከመቅረፉም ባለፈ ሕገወጥ የሰዎች ፍልሰትን እንደሚያስቀር አብራርተዋል።

አንድ ሰው ለሥራ በሚሄድበት አገር ሁለት ዓመት የኮንትራት ውል የሚፈራረሙ ሲሆን፤ ካልተመቻቸው በሕጋዊ መንገድ የመቀየር መብት እንዳላቸው ወይዘሮ ሙፈሪያት ገልጸዋል።

ወይዘሮ ሙፈሪያት እንደገለጹት፤ የዜጎች ስምሪት እንደ ከዚህ ቀደሙ በግለሰቦች መልካም ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን፤ መንግሥት ለመንግሥት በሚደረግ ጠንካራ የድጋፍና የክትትል ሥርዓት ላይ የተመሠረተ ነው። በዚህም መንግሥት ሳያውቀው ከሚሠሩበት ቤት በሕገወጥ መንገድ መጥፋት ወንጀል ይሆናል።

ሠራተኞች ወደ ውጭ አገራት ለሥራ ሲሠማሩ ሕጋዊ ሥርዓቱን ተከትለው ሊሆን እንደሚገባ ያስገነዘቡት ሚኒስትሯ፤ ክፍያቸውን፣ መብታቸውንና ደህንነታቸውን መከታተል ያስችላል ብለዋል።

በሥራ ስምሪቱ ላይ የሚሳተፉት ዜጎች በከፊል እና ሙሉ ለሙሉ የሰለጠኑ ሲሆኑ፤ በመዳረሻ አገራት ያለውን ባህል፣ ሃይማኖት እና የሥራ ሁኔታውን አውቀው እንዲሄዱ 94 የስልጠና ማዕከላት ተከፍተው ስልጠና እየተሰጣቸው እንደሚገኝ አስታውቀዋል።

በዚህም ዙር 67 ሺህ የሚጠጉ ዜጎች በመጀመሪያው ዙር ስልጠና ተሳትፈው ስልጠናውን ያጠናቀቁ ሲሆን፤ በሁለተኛው ዙር ስልጠና ደግሞ 68 ሺህ የሚጠጉ ዜጎች በስልጠናው እየተሳተፉ እንደሚገኙ አስረድተዋል። የሚሰጠው ስልጠና በሚሄዱበት መዳረሻ አገራት ተፈላጊና ተወዳዳሪ መሆን እንዲችሉ ያደርጋቸዋል ብለዋል።


በመዳረሻ አገራት የሚገኙ ኤምባሲዎች ሥራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ሠራተኞች ያሉበትን ሁኔታ ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ የሚያስችላቸው ሲስተም መዘርጋቱንም አስታውቀዋል።

በተደረገው ስምምነት መሠረት በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ ስልጠና ያልወሰደ ዜጋ ወደ ማንኛውም መዳረሻ አገራት መሄድ እንደማይችል አስታውቀዋል።

ከዚህ በፊት ከኳታር፣ ከጆርዳን፣ ከሳውዲ አረቢያ እና ከዩናይትድ አረብ ኢሚሬቶች ጋር ሕጋዊ ስምምነት እንዳለ ወይዘሮ ሙፈሪያት አስታውሰዋል። እንደ መዳረሻ የአፍሪካና የአውሮፓ አገራት እየመጡ እንደሚገኙም አስታውቀዋል።

# አገልግል

## የቅዳሜ መጽሔት





በዘመናዊነቱ ሞዴል ተደርጎ የሚወሰደው
የየካ-2 መኪና ማቆሚያ ፕሮጀክት

ገጽ 14

"ኢትዮጵያ ለእስልምና ያደረገችው አስተዋፅኦ ተቆጥሮ አያልቅም"

- ሼህ ሱልጣን ሀጂ አማን ኤባ
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት

ገጽ 6




የአዕምሮ እድገት ውስንነትን በፍቅር

ገጽ 16

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ኪነጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

ባህል፣ ኪነ ጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ
አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

### አፍሪካዊቷ መልህቅ

# በመዲናዋ ባህላዊ እሴቶችን ለማስረጽ

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

የአዲስ አበባ አስተዳደር ባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ የነዋሪውን ሕዝብ ባህላዊ እሴቶች አገር በቀል ዕውቀቶችን ለማስረጽ ለማስቀጠልና ለማስተዋወቅ እየሠራ ይገኛል። ቢሮው የባህል እሴቶች እንዲለሙ፤ አገራዊ ባህላዊ የእደ ጥበብ ሀብቶች እንዲተዋወቁና ለቱሪስት መስህብ እንዲሆኑና ለአገርም ገቢ እንዲያመነጩ ባህልን እንዲጠብቁ ይሠራል። ለዚህም በተለያዩ ጊዜያት ዐውደ ርዕይ፣ የባህል ሳምንታት፣ ዐውደ ጥናት እና የፓናል ውይይቶች በማዘጋጀት እና በማስተዋወቅ የሠራቸው ሥራዎች አሉ።

ያለንበት ዘመን የሉላዊነት (Globalization) ዓለም ነው። ዓለም ወደ አንድ መንደር የመጣችበት ዘመን ነው። ለዚህ ደግሞ የጽሑፍ የድምጽና የምስል መረጃዎች ሚናቸው ከፍተኛ ነው። ግን ዘመኑ ያመጣል የበይነ መረብ መረጃዎችና ሌሎችም ከአዎንታዊ ሚናቸው ጎን ለጎን የጎንዮሽ ጉዳትም (አሉታዊ) አላቸው። ዜጎች የራሳቸውን ባህል ንቀውና ለቀው የምዕራባውያን ባህል ናፋቂና አድማቂ ሆነው የሚገኙበት። የባህል ወረራን ሲባል አልባሳቱ እና ሙዚቃዎች ሌሎችንም እንዳሉ ሆነው፤ ሱሰኝነቱ ወጣቱና በወይዛዝርቱ ዘንድ መስፋፋቱ በአብዛኛው በታዳጊ አገሮች እየታየ ነው። እንደ ጃፓን፣ ቻይና፣ ሕንድ፣ ኮርያ እንዲሁም የተወሰኑ አረባውያን አገሮች ባህላቸውን ጠብቀው የባህል ወረራውን ለመከላከል ሲጥሩ ይታያሉ።

የባህል እሴቶችን ስናስብ በመዲናችን በርካታ ባህላዊ አልባሳት፣ የእደ ጥበብ የፈጠራ ምርቶች፣ ለገበያ ይቀርባሉ። እንደ መርካቶ ባሉ የገበያ አካባቢዎች ባህላዊ የአለላ እና የስንደዶ ስፌት ምርቶች ማለትም ሰፌድ፤ መሶብ ሌማት የሚባሉት ለገበያ የሚቀርቡበት ቦታ አለ። መቼም ሰፌድ ሲባል እንጀራ ማውጫ የስንደዶ ምርት መሆኑን ሁላችንም እናውቃለን። መሶብ እና ሌማት የማያውቅ ዜጋ ካለ ምናልባት ባህሉን የማያውቅ ልንለው እንችላለን። መሶብ እንጀራ የሚቀመጥበት ሲሆን ሌማት ደግሞ ለምሳም ሆነ ለእራት ገበታ የሚቀርብበት የስንደዶ ስፌት ነው። በከተማችን ሌማትን ለጌጥ ይገለገሉበታል እንጂ ሰዎች ብዙም ምግብ አያቀርቡበትም። በባህል ምግብ ቤቶች ግን ሌማት ገበታ ያቀርቡበታል።

እንቅብ፣ ቁና፣ እርቦ፣ አገልግል የሚባሉ የስንደዶ ምርቶችም በአዲስ አበባ እያገለገሉ አይደለም። ከተሜዎች ባያውቁትም በገጠር ብዙዎቹ ይጠቀሙበታል። እንቅብ ትልቁ ነው። ከዚያ እንደ ደረጃቸው ቁና፣ እርቦ ይባላሉ። እርቦ የሚባለው ስፌት ስያሜው ሩብ ከሚለው ቃል ነው የመጣው ይላሉ ሩብ ኪሎ ለማለት ነው። በገጠር ሚዛን በቅርብ ቦታ ስለሌለ እህል በእርቦ አራት ጊዜ ሠፍሮ ለጎረቤቱ የሰጠ ሰው 100 ኪሎ እንደሰጠ ይታመናል። በመርካቶ ዶሮ ተራ አካባቢ እነዚህ ባህላዊ ምርቶች ይሸጣሉ። ለግድግዳ እና ለጠረጴዛ ጌጥ የሚሆኑ ቀለምማ (የአለላ የስንደዶ) የስፌት ምርቶችም። ይህም በአዲስ አበባ ባህላዊ እሴቶቻችን አሁንም ተፈላጊነት እንዳላቸው ያሳየናል። የአገልግል ስፌት ከውጪው በቆዳ ይለበጣል። በገጠር ለአክፍሎት፣ ሰዎችን ለመጠየቅ ሩቅ መንገድ ሲሄዱ ዳቦም ሆነ አነባበሮ ይዘውበት እንኳን አደረሳችሁ ይሉበታል። በከተማ ግን በግድግዳ ጌጥነት ያገለግላል። ይሄም በራሱ ባህልን መያዝ ነው።

ሌላው ከዚሁ ጎን የምንገለገልባቸው የሸክላ ዕቃዎችም ነባር የባህል እሴቶቻችን ናቸው። በኢትዮጵያ ቡናና ጀበና አይነጣጠሉም። ጀበና ከሸክላ የሚሠራ የቡና ማፍያ መሆኑ ይታወቃል። ብርሌውና ጠጁም እንዲሁ ባህላችን ነው። በኢትዮጵያ በሁሉም ብሔር ውስጥ የማይታጣ፤ ጀበናን ዘመኑ ያመጣው የቡና ማሽን እንኳ ባህላዊ ርስቱን ሊያስለቅቀው ያልቻለ የቅርስና ባህል ቁስ ነው። ጀበና ተጥዶ ቡናው ሲጠጣ ሰው በሲኒው ረከቦቱ ሥር ተኮልኩሎ እንደ አዲስ አበባ ባሉ ከተሞች ሲዝናና ሲጽናና ታያላችሁ። የቡና ማፍላት ባህላችን ከተጋንበት በተባበሩት መንግሥታት የሳይንስና የባህል ድርጅት ዩኔስኮ በማይዳሰስ የዓለም ቅርስ አድርገን ልናስመዘግበው የሚችል ነው። የእንጀራ ምግባችንም ሳይዘነጋ ነው።

ስለ ባህላዊ የሸክላ ሥራዎች ስናስብ ድስት፣ ምድጃ (ጉልቻ)፣ ጣባ፣ የጭቅና ሸክላ፣ የእንጀራ ምጣድ፣ ምንቸት ማሰሮ እንስራ ጋን ይጠቀሳሉ። በአዲስ አበባ በመርካቶ ሸክላ ተራ (ምናለሽ ተራ) በቀጨኔ፣ በሽሮ ሜዳ ለገበያ ይቀርባሉ። የከተማ ሰው የሸክላ ድስት፣ አነስተኛ ድስት (ተጋቢኖ ሽሮ የሚቀርብባት) እንዲሁም የክትፎና ዱለት ጣባ፣ የጭቅና ጥብስ ማቅረቢያ ሸክላ እና ጉልቻ፣ የማገዶ የእንጀራ ምጣድ፤ እንዲሁም ኤሌክትሪክ ምጣድ እየሠሩ የሚሸጡ ሰዎች ደግሞ የእንጀራ ምጣዱን በገፍ እየገዙ አበጃጅተው የሚሸጡበት ነው። ምናለሽ ተራ ብትሄዱ (ምጣዱ ጀርባው ከመሓል እስከ ጫፍ ዙሪያውን የኤሌክትሪክ ሽቦ እየተቦረቦረ እንዲገባበት ተደርጎ በብዛት ሲሠራ) ታያላችሁ። ሻይ ቡና ለማፍላት የሚችል ልክ እንደ እንጀራ ምጣድ በኤሌክትሪክ የሚሠራ አነስተኛ ምድጃም ገበያ ላይ ይገኛል። ውሃ የሚቀዳበት እንሥራ፣ ጠላ የሚጠቀምበት ጋን ከሸክላ የተሠሩ ናቸው። በገጠሩ አሁንም የሚገለገሉበት ነው።


በአዲስ አበባ ባልዲ እና ጀሪካን አገልግሎት ሲውሉ እነ እንሥራ አረፉ። በከተሞች እንሥራ ሙቀትም ቅዝቃዜም ቢኖር ለረጅም ሰዓት እንዳሉ ውሃ እንደያዙ ሞቅ ቀዝቀዝ ሳይሉ መቆየት ይችላሉ። የብረት/ የፕላስቲክ ባልዲ ግን በሙቀት ቦታ ሰዎች ውሃቸው ለመጠጣት የሚሄዱት አማራጭ በማጣት ነው። መቼም የተሻለ ቴክኖሎጂ ሲመጣ መጠቀም እንዳለብን እናምናለን። ‹‹የራስን ጥሎ የሌላውን አንጠልጥሎ›› የሚያስኬድ የባህል ወረራ ግን እዳ መሆኑን መገንዘብ ይገባል።

የአዲስ አበባ ባህል ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ሂሩት ካሳው ባለፈው ጥር መጨረሻ ‹‹ባህሎቻችን የአንድነት ካስማ›› በሚል መሪ ቃል በጥር ወር መጨረሻ በተካሄደው የባህል ሳምንት ፌስቲቫል ላይ ባደረጉት ንግግርም፣ የከተማዋ ነዋሪዎች የራሳቸውን ወግና ባህላዊ እሴቱን ጠብቆ በማልማት እና ለገበያ ትስስር ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ከሁሉም በላይ ደግሞ የከተማዋን ነዋሪዎች እርስ በእርስ የባህል ትስስርና አንድነት ይበልጥ ለማጠናከር የሚያስችል እድል ይፈጥራል ብለዋል።

# የዘመን እንግዳ

# "ኢትዮጵያ ለእስልምና ያደረገችው አስተዋፅኦ ተቆጥሮ አያልቅም"

**-ሼህ ሱልጣን ሀጂ አማን ኤባ**
**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት**



ፎቶ፡ አዮብ ተፈሪ

**አስመረት ብስራት**

ሼህ ሱልጣን ሀጂ አማን ኤባ ይባላሉ። ተወልደው ያደጉት ወልቂጤ ቢሞራ የምትባል መንደር ውስጥ ነው። በአገራቸው ባህል መሰረት ቁርአንን የቀራ ሼህ በአካባቢው ካለ የአካባቢውን ልጆች ጠዋት ከማለዳ እስከ ከብቶች ማሰማሪያ ሰዓት ድረስ ያስቀራሉ። የአካባቢውን ልጆች ሰብስበው ቁርኣን ያስቀሩ የነበሩት ደግሞ አባታቸው ሸህ አማን ኤባ ናቸው። ሸህ ሱልጣን ከአባታቸው እግር ስር ቁርኣን ቀርተው ነበር ያደጉት።

በእስልምና ሀይማኖት ትምህርት ልጆች ቤተሰቦቻቸው ጋር ተቀምጠው ከተማሩ ሙሉ ትኩረታቸውን ለሀይማኖት ትምህርቱ አይሰጡም ተብሎ ስለሚታሰብ ከወልቂጤ ተነስተው ወደ ስልጤ፤ ሀላባና ወደ ጅማ በመሄድ ይማሩ ነበር። ሼህ ሱልጣንም በተለያዩ አጎራባች ወረዳዎች በመሄድ ከታወቁ ሼሆች እግር ስር ቀርተዋል።

በመቀጠል ወሎ ክፍለ አገር በ1977 ዓ.ም ለአራት አመታት ቀርተው ወደ አገራቸው ሲመለሱ በወቅቱ የነበረው አስተዳደር የሶሻሊዝም ርእዮተ ዓለም ተከታይ ስለ ነበር ሀይማኖታቸውም በነፃነት ማራመድ ሲሳናቸው ወደ ሱዳን ያቀናሉ። በሱዳን ሁለት ዓመት ከቆዩ በኋላ ወደ ሳውዲ አረቢያ ባገኙት ነፃ የትምህርት እድል አማካኝነት ይጓዛሉ። በዛም በአረብኛ ቋንቋ የመጀመሪያ ድግሪ፤ በእስልምና ሀይማኖት ትምህርት ሁለተኛ ድግሪያቸውን አግኝተዋል።

ሼሁ በሳውዲ አረቢያ ለአስራ አምስት ዓመታት ቆይታቸው በሳውዲ በሚገኙ ከተሞች ማለትም በመዲና ለሶስት ዓመታት፤ በዋና ከተማው ሪያድ አምስት ዓመት፤ መካ ሁለት ዓመት፤ በጅዳ ደግሞ ለአምስት ዓመታት ከቆዩ በኋላ በአገራቸው ኢትዮጵያ የስርኣት ለውጥ በመምጣቱ ወደ አገራቸው መመላለስ ጀመሩ።

ጠቅልለው ኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር ሲወስኑ አንድ ምግባረ ሰናይ ድርጅት ከፍተው በድህነት ውስጥ ላሉ ሰዎች እርዳታ የሚያደርግ፤ መስጊዶችን የሚሰራ፤ ቁርኣንም በተገቢው መልኩ ለሁሉም እንዲዳረስ የማድረግ ስራን የሚከውን ድርጅት ለማቋቋም አሰቡ። ለዚህ መነሻ የሆናቸው ደግሞ በሳውዲ አረቢያ በነበራቸው ግንኙነት የገንዘብ ድጋፎችን በማሰባሰብ ለወገን ጠቃሚ የሆኑ ተግባሮችን ሲያከናውኑ መቆታቸው ነው።

አሁን ሼህ ሱልጣን ሀጂ አማን ኤባ የአዲስ አባበ ከተማ አስተዳደር እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት በመሆን በማገልገል ላይ ይገኛሉ። የረመዷን ፆምንና የኢድ በዓልን በተመለከተ ከእኚህ ታላቅ አባት ጋር ቆይታ አድርገናል፤ መልካም ንባብ።

**አዲስ ዘመን፤ ረመዷን ማለት ምን ማለት ነው ከሚል ጥያቄ እንነሳ?**

**ሼህ ሱልጣን ሀጂ አማን፤** "ረመዷን" ማለት . . . በቁርአን ላይ እንደተገለጸው፥ ከአላህ ዘንድ የወራት ቁጥር 12 ናቸው። እነሱም፡- ሙሀረም፣ ሰፈር፣ ረቢዕ አልአወል፣ ረቢዕ አልሳኒ፣ ጅማድ አልኡላ፣ ጅማድ አልአኺራ፣ ረጀብ፣ ሻዕባን፣ ረመዷን፣ ሸዋል፣ ዙል ቀኢዳ እና ዙል ሂጃ ናቸው። ከላይ በቀረበው አገላለጽ መሰረት፥ "ረመዷን" ማለት ከ12ቱ ወራት የዘጠነኛው ሥያሜ ነው።

ረመዷን ከሌሎች ወራት የሚለይበት በርካታ ምክንያት እንዳሉት ይገለጻል። ከሌሎች ወራት ከሚለይባቸው ምክንያቶች አንዱ "ቁርአን የወረደበት ወር መሆኑ ነው። በተጨማሪም ረመዷን የሠደቃ፣ የራህመት፣ የጀነት በር የሚከፈትበት፣ የጀሃነም በር የሚዘጋበት፣ በጎ ሥራዎች ሲሠሩ ከአላህ ዘንድ እጥፍ ክፍያ (አጅር) የሚያስገኝ በመሆኑ ከሌሎች ወራት ይለያል።

እንዲሁም ረመዳን "ለይለቱል ቀድር" የተሰኘች የ1ሺህ ወራት የአምልኮ ምንዳ ልታስገኝ የምትችል አንዲት ሌሊት የምትገኝበት ወር በመሆኑ ልዩ ነው። ወሩም የበረከት ማግኛ ወር በመሆኑ ሙስሊሞች እንዲጾሙ ይጠበቃል ።

የረመዷን ወር በርካታ ትሩፋት አሉት። ቁርአን በብዛት የሚቀራበት፣ "ቀልቦች" ወደ ፈጣሪያቸው ቀጥ የሚሉበት፣ ርኅራሔ የሚበዛበት፣ ሠደቃ የሚሠደቅበት፣ የቸርነት፣ የልገሣ፣ የደግነት፣ የተካፍሎ መብላት እና የመረዳዳት ወር መሆኑ ከትሩፋቶቹ መካከል የሚጠቀሱ ናቸው።

የረመዷን ወር በሦት አሥር ቀናት የሚከፈል ሲሆን፥ ከሦስቱ አሥሮች የመጨረሻው አሥር ("አሸረ አልአዋኺር") ይሰኛል። በአጠቃላይ "ረመዷን" የ "ኢባዳ"(በጾምና በጸሎት ወደፈጣሪ መመለሻ) ወር ቢሆንም የሦስተኛው አሥር ቀናት የተለዩ በጾም በጸሎት ማሳለፊያ ጊዜ (የ"ኢባዳ" ሌሊቶች) ናቸው።

የረመዷን የመጨረሻው ሣምንት ሌሊቶች ከሌሎች ሣምንታት ምክንያቶቹ መካከል፥ ነብዩ መሐመድ (ሰለሏህ ዓለይሂ ወሰለም) ያደርጉት እንደነበረው ሥራ ትቶ፣ እራስን አቅቦ ለ"ኢባዳ" ማስቀመጥ ቀኑንም ሌሊቱን በመስጂድ ማሳለፍ ("ኢህቲካፍ" መግባት) አንዱ ነው። በመሆኑም ወደ መስጂድ ለ "ኢህቲካፍ" የገባ ምዕመን ጊዜ የማይሰጥ ጉዳይ ካላጋጠመው በስተቀር ከመስጂድ መውጣት የማይቻልበት ሣምንት መሆኑንም ነው የሚጠቅሱት።

ሌላኛው ምክንያት በእነዚህ ሌሊቶች፥ የተራዊህ እና የተሃጁድ ሶላት ይሠገዳል፣ ሌሊቶቹ ያለዕንቅልፍ ቁርአን በመቅራት እንዲያልፉ ይደረጋል፣ መሻይኾች፣ ዑለማዎችና የመስጂድ አሰጋጆች በተለያየ የሶላት ወቅት ላይ (በዙህር፣ ዓስር፣ መግሪብ፣ ኢሻ)፣ በማኅበራዊ ጉዳይ፣ በሥነ ምግባር፣ በአምልኮ እንዲሁም በእምነቱ ዙሪያ (በዓቂዳ ጉዳይ ላይ) ምክር ይሰጣሉ ።

ሙስሊሞች "ረመዷን" ን ለቀጣዮቹ 11 ወራት የባሕርይ፣ የሥነ ምግባር፣ የአምልኮ የጥንካሬ እና የብቃት አቅም የሚያጎለብቱበት ልዩ ወር ነው።

የመጨረሻው ሣምንት ሌሊቶችንም በንቃት በኢባዳ ነው የሚያሳለፉት። የመጨረሻ ሣምንት የጾም ወቅት በኢትዮጵያ በበርካታ መስጂዶች የተሃጁድ (የሌሊት) ሶላት ይሰገዳል። በተጨማሪም ረጅም ሩኩዕ፣ ረጅም ስጁድ፣ረጂም ቂያም ያካተተ ሶላት ይሠገዳል።

በአጠቃላይ ይህ ሁሉ ለኢባዳ የሚደረገውን መስዋዕትነት በአላህ እንደመገዛት የሚከፈለውን መስዋዕትነት ለማሰልጠን ጭምር ነው።

ከ1 ሺህ ወራት ኢባዳ የላቀ ምንዳ ያላት አንድ ሌሊት (ለይለቱል ቀድር) ከቅዱሱ የረመዷን ወር የመጨረሻ ሣምንት ውስጥ «ለይለቱል ቀድር» የምትባል በረከቷ የበዛ ሌሊት አለች። ይችኑ ሌሊት «ኸይሩን ሚን አልፊሸህር» ብሏታል ቁርአን።

1 ሺህ ወር አላህን ከማምለክ በእዚች ሌሊት ላይ ጠንክሮ ማምለክ የ1 ሺህ ወራትን (83 ዓመት ከ3 ወራት በላይ) ኢባዳን ወይም አምልኮን ትተካለች። ሙስሊሞች ይችን በረከተ ብዙ ሌሊት በኢባዳ ለማሳለፍ በንቃት ሁልጊዜም ይጠባበቃሉ።

ነብዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አሥሩንም ሌሊቶች እንቅልፍ ያለባቸውን ቤተሰቦቻቸውን ቀስቅሰው የጋራ ኢባዳ እና የጋራ አምልኮ (በጀመዓ መጸለይ) በማድረግ ሳይተኙ ያሳልፉ ነበር እኛም እሳቸውን የምንከተል በመሆናችን «በአላህ መልዕክተኛ መልካም አርአያ አላቸው፤ እሳቸው የሚሉትን ሥሩ» ስለተባልን ኢባዳችንን አጠናክረን እንቀጥላለን።

ሌሊቱ በዱዓ፣ በጸሎት፣ እንዲያልፍ አላህ ይቅር እንዲል ሙስሊሞች የሚማፀኑበት ሌሊት መሆኑም ተመላክቷል። ረመዷን ሠደቃ የሚሰጥበት፣ አቅመደካሞች የሚረዱበት፣ የመተጋገዝ ወር እና ለማፍጠሪያ ማዕድ ማጋሪያ ጊዜም ነው።

**አዲስ ዘመን፤ በብዙዎች ዘንድ ተናፋቂ የነበረው የረመዳን ጾም ተጠናቋል። ስመሆኑ ጾሙ እንዴት አለፈ ?**

**ሼህ ሱልጣን ሀጂ አማን ፤** ፆም ሲታሰብ ረሃቡ ድካምን ጥሙን ብዙ ሰው ያስባል። እኛ ግን ፆምን ስናስብ ባላለቀ እያልን ነው የምንፆመው። ምክንያቱም ፈጣሪ ያዘዘውን ትእዛዝ የምንፈፅምበት በመሆኑ ነው። ፆም ጤና ለሌለው ሰው ጤናን የሚሰጥ፤ ከዚህም በላይ ምንም የሌላቸው ሰዎችን ከድህነቱም ከችግሩም የሚላቀቁበት፤ የሚረዱበት ጊዜ ነው። ፆም ላለውም ለሌለውም በበረከት የሚኖርበት፤ ፆም መልካምን ነገር ይዞ የሚመጣበት በመሆኑ ደስታ ነው በፆም ጊዜ የሚሰማን።

የዘንድሮ ፆም በአገራችን በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ምክንያት ብዙዎች በተቸገሩበት ወቀት ላይ ነው የመጣው። በዚህም ምክንያት የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት የተቻለውን እየረዳ፤ ህዝበ ሙስሊሙም ከጎረቤቱ ጋር ተካፍሎ እንዲበላ በማስተማር፤ የመስጊድ ኡለማዎችና ኢማሞችን ደግሞ ወደ ፈጣሪ ጥሪ የሚያደርጉ አካላት እርዳታ ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ አድርገናል። በዚህም ከብዙ አካላት እርዳታ ተሰብስቦ ለብዙሃኑ ተዳርሷል።

በዚህ በፆም ወቅትም በቦረና ለተከሰተው ከፍተኛ ድርቅና ረሃብ የተጎዱ ሰዎች ድጋፍ የሚውል ከየመስጊዱ የተሰባሰበ እስከ 20 ሚሊየን ብር የሚደርስ ገንዘብ ተገኝቶ ለተጎጂዎች እንዲደርስ ሆኗል። አሁን በፆሙ ጊዜ ወደ ደብረ ብርሃን አካባቢ በመጠለያ ላሉት የሚደርስ እርዳታም በማሰባሰበ ላይ እንገኛለን። በዘንድሮው ፆም አገራችን ምንም እንኳን ችግር ላይ ብትሆንም እርስ በእርስ እየተረዳዳን በጥሩ ሁኔታ አሳልፈናል።

አንድ ሙስሊም ካለው ሃብት ላይ 2ነጥብ 5 በመቶውን ለችግረኛ ወገኖች የሚሰጥበት ስርዓት አለ፤ ይህም ዘካ ይባላል። ይህ ፆምም ለተለያዩ አካላት ማለትም ለጎረቤት፤ ለቅርብ ዘመድ፤ ለሩቅ ዘመድ፤ ምንም ለሌለው ምስኪን፤ የተወሰነ አቅም ኖሮት ለማይበቃው፤ ወላጅ ላጡ ህፃናት ዘካ ይሰጣል። ከዛ በተጨማሪ ደግሞ ሰደቃ የሚባል አለ። ይህ ግዴታ ሳይሆን ራሱ ምእመኑ ከፈጣሪ ዘንድ ምንዳ እንዲያገኝ ብሎ የሚያደርገው የስጦታ ነው። እንዲህ አይነት ነገሮች በሙስሊሙ ዘንድ በጣም በስፋት የሚሰራበት ጉዳይ ነው።

በተከናወነው የጎዳና ኢፍጣርም ሁሉም ኢትዮጵያውያን ያላቸውን ይዘው ወጥተው አብረው ያፈጠሩበት፤ ያጡ ወገኖችን ለመደገፍና እርስ በእርስ የመደጋገፍ ፍላጎታቸውን ለማሳየት በነቂስ በመውጣት አብረው መአድ ቆርሰዋል። በኪሳቸው የያዙትን ደግሞ ለተቸገሩት በማለት አውጥተዋል። በዚህ መልኩ ነው እንግዲ ፆሙ ያለፈው ።

**አዲስ ዘመን፤ ሀጂ በእርስዎ ቤት የነበረው የረመዳን ጾም ሁኔታ ምን ይመስላል ?**

**ሼህ ሱልጣን ሀጂ አማን፤** እኔ በቤቴ ከሁለት ሚስቶች ስምንት ልጆች አሉኝ። እቤት ግን ያፈጠርኩት አራት ቀናት ብቻ ነው። እዚህ የህዝብ መሪ ስለሆንኩኝ የህዝብ ኃላፊነት ስላለብኝ ሰዎች በየቦታው ስለሚጠሩኝ ወደየጥሪው እየሄድኩኝ ነው የማሳልፈው። ልጆቼም ቤተሰቦቼም ይሄንን ስለሚያውቁ ቅር አይላቸውም።

### ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ



**አዲስ ዘመን፡ የኢድ በዓል የመጠያየቅና የመረዳዳት በዓል ነው ? በአጠቃላይ የኢድ በዓል ለሙስሊሞች ምንድን ነው ?**

**ሼህ ሱልጣን ሀጂ አማን፡** በዓመት ወስጥ ሙስሊሞች የሚያከብራቸው ሁለት ታላላቅ በዓላት አሉ አንዱ፤ ፆም ተፁሞ የፆም ፍቺ እለት የሚከበረው ኢድ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ፤ በሀጂ ጊዜ የሚከበር የአረፋ ኢድ የሚባል አለ። የአረፋ በዓል በሶስተኛው ወር በአስረኛው ቀን የሚፈፀም ኢድ ነው። ይሄኛው ኢድ የእስልምና ሀይማኖት ምሶሶ የሆነውን ረመዷን ፆም ጨርሰን ያለውም የሌለውም፤ ሴቱም ወንዱም፤ ትልቁም ትንሹም ይሄን ፆም ፈፅሞ፤ ፈጣሪ ያዘዘውን ትእዛዝ ተቀበሎ ወደ ፈጣሪው ቀርቦ ከፈጣሪው ምህረትን ተቀብሎ ንፁህ ሆኖ የሚወጣበት ወር ነው። ኢድ ማለት ደስታ ማለት ነው። ሀይማኖቱን ከፍ አድርጎ የሚያሳይበት ነው። ለዚህም ነው ሰፋ ባለ ቦታ የሚሰግደው።

አንድ ሰው ጀስሙ ላይ ወይም አካሉ ላይ ቆሻሻ ከነበረና ታጥቦ ሲነሳ የሚሰማው የመፅዳት ስሜት ሙስሊሙ ማህበረሰብ ከፆሙ በኋላ ያገኘዋል። በመንፃት ደስታ ይገኝበታል። ኢድ ለሙስሊሙ ደስታን የሚያጎናፅፍ ትልቅ በኣል ነው።

**አዲስ ዘመን -በኢድ ወቅት የሚከወኑ ተግባራት ምንድን ናቸው?**

**ሼህ ሱልጣን ሃጂ አማን -** በኢድ ወቅት የሚከወኑ ዋናዋና ተግባራት አሉ። የመጀመርያው ኢድ ከመሰገዱ በፊት ምንም ለሌላቸው ወገኖች የሚሰጥ ምጽዋት አለ። ዘካተል ፊጥር ይባላል። ዘካተል ፊጥር ድሆች ኢድን እንደሌሎች ወገኖቻቸው ሁሉ በደስታ እንዲውሉ የሚሰጥ መጠነኛ ስጦታ ነው። ለአንድ ሰው አራት እፍኝ ስንዴ፤ ዱቄት፤ ጤፍ ወይም ይህንን ወደ ገንዘብ በመለወጥ የሚሰጥ ስጦታ ነው። ከዚህ በኋላ ሁሉም ሙስሊም በአንድነት ለመስገድ ሰፋ ባለ ቦታ ይሰባሰብና (እዚህ አዲስ አበባ ስታዲዮም እንደሚደረገው) የኢድ ሶላቱን በጀምዓ (በጋራ) ይሰግዳል። ከዚያ ሲመለስ ከቤተሰቦቹና ከጎረቤቶቹ ጋር በጋራ በደስታ ያሳልፋል። እዚህ ላይ ግን ከምስኪን ወገኖች ጋር ተካፍሎ መብላትና መጠጣት የእምነቱ አንዱ ግዴታ ነው።

**አዲስ ዘመን፡ ኢትዮጵያ ለእስልምና እምነት ያበረከተችውን አስተዋጽኦ እንዴት ይመለከቱታል?**

**ሼህ ሱልጣን ሀጂ አማን፡** ኢትዮጵያ ለእስልምና እምነት ያበረከተችውን አስተዋጽኦ በጣም ከፍተኛ ነው። ይህ ጉዳይም በታሪክ ተመዘግቦ የተቀመጠ የዓለም ህዝብ በሙሉ የሚያውቀው ሀቅ ነው። ድሮ እስልምና ነብዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) መካ ላይ ተልከው ስለእምነት ሲያውጁ የአካባቢው ሰዎች አንቀበልም ብለው ሙስሊሞችን መዳረሻ ያሳጧቸው ጊዜ፤ መሸሻ መሸሸጊያ በአጡበት ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ሂዱ ብለው ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) ተከታዮቻቸውን አዘዟቸው። ነብዩ መሃመድ በፈጣሪ ምሪት ስለሚመሩ በዛ መሰረት ወደ ሀበሻ ሂዱ እዛ አገር ትልቅ መንግስት ወይም መሊክ አለ ያ መሊክ ማንም ሸሽቶ የሚመጣ ካለ የሚቀበል፤ በግፍ አሳልፎ የማይሰጥ፤ በፍትሃዊነት የሚመራ መንግስት ስለሆነ ይቀበላችኋል ብለው ተከታዮቻቸውን ወደ ሀበሻ ላኩ።

እነሱም መልእክቱን ተቀብለው ወደ አገራችን መጡ። በመጡ ጊዜም ልክ እንደተባለው ንጉስ ነጃሺ ተቀብሎ በተገቢው አስተናገዳቸው። ቁረሾች እነዛን ሰዎች መልሱልን የኛ ናቸው ቢሉም ንጉሱ አልመልስም በማለት መጠለያ ሆነዋል። በዛን ጊዜ እስልምና የነገሰበት አገር መዲና ላይ እንኳን የእስልምና ትምህርት ሙሉ ለሙሉ አልተዳረሰም ነበር። ይህ አኩሪ ታሪካችን በኢስላም አገሮች ላይ የሀበሻ ታሪክ ተብሎ እንደትምህርት ይሰጣል። ይህ ታሪክ በዓለም የገነነ ነው።

ሶሃባዎች (የነቢያችን ወዳጆች) ሁለት ጊዜ ነው ወደ ሀበሻ የመጡት። የመጀመሪያዎቹ 15 የነበሩ ሲሆን በቀጣየም ከ70 በላይ መጡ። እስካሁን ድረስ ትግራይ ላይ ያለው አልነጃሺ በወቅቱ የሞቱ ሳህባዎች አፅም በክብር ተቀምጦ ይገኛል። የነብያችን ልጅም መጥታ የነበረ መሆኑ ታሪክ ይናገራል።

ነብዩ መሃመድ (ሰ.ዐ.ወ) እናታቸው አሚና የሞተችው በህጻንነታቸው ነው። ኢትዮጵያዊቷ እሙይ አይመን ነብዩን በሞግዚትነት የማሳደግ ኃላፊነት ወስዳ ነብዩን በማሳደግ ኃላፊነቷን ተወጥታለች። የመጀመሪያውን አዛን (ጥሪ) ያደረገውም ቢላልም ሀበሻ ነው። ቢላልን ቁረሾች ያላደረጉት ነገር አልነበርም። እሱ ግን አንድ ፈጣሪ እያለ ነው የሞተው። እናም አገራችን ለእስልምና ያበረከተችው ታሪክ ተቆጥሮ የማያልቅ ነው።

**አዲስ ዘመን፡ ኢትዮጵያ የአይሁድ፤ የክርስትናና የእስልምና ኃይማኖቶችን ተቀብላ ያስተናገደችና ለዘመናትም በመከባበር ሳይ እንዲኖሩ ያደረገች አገር ናት። በዚህ ረገድ እርስዎ ምን ይላሉ?**

**ሼህ ሱልጣን ሀጂ አማን፡** አገሪቱ ውስጥ አይሁዶች ነበሩ፤ አሁንም አሉ ይበላል፤ ክርስትናም ቀድሞ የነበረ ሲሆን እስልምና ደግሞ ከ አንድ ሺ አራት መቶ አርባ አራት አመተ ሂጅራ በፊት ነበረ የመጣው። እንግዲህ ከዛን ጊዜ ጀምሮ ሀይማኖቶች አብረው ኖረዋል። መንግስታት ሲቀያየሩ ከፍና ዝቅ የሚሉ ነገሮች ይኑሩ እንጂ ህዝብ እንደ ህዝብ ግን በአብሮነት ተቻችሎ ተከባብሮ አብሮ መአድ ቆርሰው አብረው ኖረዋል። አሁን ግን በአገራችን ሀይማኖቶች እኩል መብት አግኝተዋል ብዬ አስባለሁ። ሁላችንም በጋራ በመሆን የሀይማኖቶች ጉባኤ ላይ አብረን እየሰራን ነው። አሁን ያለው መሪ ሀይማኖቶችን እያከበረ ያለ መሪ ነው።

እንደ አዲስ አበባ እስልምና ጉዳይ እንደ አዲስ አበባ ነዋሪ ኦርቶዶክስ ሰብሳቢ ሙስሊሙ ደግሞ ፀሃፊ ሆኖ ከሁሉም ሀይማኖት ተቋማት የተውጣጡ የሀይማኖት ተቋማት ጉባኤ አቋቁመን ለህዝቡ መተላለፍ ያለበትን ነገር ተወያይተን ተመካክረን እንደሃይማኖት አባት እናስተላልፋለን። ህዝቡ የእስልምና ሀይማኖት በዓል ሲመጣ እንደ አንድ ሰው ሆኖ በአብሮነት ተከባብሮ ተደጋግፎ መአድ የሚቆርስበት ሁኔታ ነው ያለው። አገራችን በዚህ ረገድ ምሳሌ የምትሆን አገር ናት። ህዝቡ ውስጥ ያለው መከባበርና መቻቻል በየትኛውም አገር የሚታይ አይደለም። ህዝቡ ቀድሞ የነበረውን ሁኔታ ማስቀጠል ይኖርበታል።

**አዲስ ዘመን፡ የቀደሙ የአገር እሴቶችን አስከብሮ ከማስቀጠል አንፃር ከህዝበ ሙስሊሙ ምን ይጠበቃል?**

**ሼህ ሱልጣን ሀጂ አማን፡** እኛ ለህዝበ ሙስሊሙ እያስተላለፍን ያለው መልእክት ሁላችንም የግል ሀይማኖት ቢኖረንም አገራችን ግን አንድ ናት፤ ይህችን አገር ደግሞ ሰላሟን መጠበቅ፤ ልማቷን ማስቀጠል፤ ከዚህ በፊት ይዘነው የመጣነውን የአብሮነት ባህል ማስቀጠል ይኖርብናል የሚል ነው።

ከበፊቱ የበለጠ መቻቻል ከሚለው እሳቤ ወጥተን መደጋገፍና መተባበር መፈቃቀር ህዝቡ መገለጫው እንዲሆን መሰራት ይኖርብናል። የነበረንን እሴት አሳድገን እጅ ለእጅ ተያይዘን ማደግ ይኖርብናል እላለሁ።

**አዲስ ዘመን፡ ሰላም የሁሉም ሀይማኖቶች አስተመህሮ ነውና በሰላም ችግሮችን ከመፍታት ረገድ አማኞችም ሆኑ የሀይማኖቱ መሪዎችም ምን ማድረግ አለባቸው?**

**ሼህ ሱልጣን ሀጂ አማን፡** ሁሉም ሃይማኖቶች፤ ሰላምን ፍቅርን አብሮነትን ይሰብካሉ። ያንን አስተምህሮ ደግሞ ወደ ህዝቡ የሚያስተላልፉት የተማሩ የበቁ አባቶች ናቸው። እነዚህ አባቶች በመመሪያ ውስጥ ያለውን ነው ህዝቡ ጋር የሚያደርሱት።

እርግጥ በአሁኑ ጊዜ አንዳንድ የፖለቲካ አካላት ሰላምን የማይፈልጉ፤ ጥላቻን የሚዘሩ ከሌላ በኩል አልሳካ ሲላቸው ኃይማኖት ውስጥ በመግባት ጥላቻን የመዝራት ሁኔታዎች ይታይባቸዋል። እኛ ግን እንደ ሀይማኖት አባት ሀይማኖት የግል ነው ፖለቲካ አይግባ በማለት ህዝቡን ንፁህ የሆነ መንፈሳዊ አስተምህሮ ማስተላለፍ ይኖርብናል። የሀይማኖት አባት እንደ ስሙ የሀይማኖት አባትነቱን ተረድቶ ከፖለቲካና ከሌሎች አላማዎች ማስፈፀሚያ ከመሆን ራሱን መጠበቅ ይኖርበታል።

ህዝቡም ባለችው አንድ አገር እምነቱን በተገቢው መልኩ ለማስፈፀም የአገር ሰላም ላይ ትኩረት ሰጥቶ በአብሮነት መስራት ይጠበቅበታል። ለመኖርም፤ በነፃነት ሀይማኖቱን ለማምለክም ቅድሚያ አገር መኖር ይኖርባታል።

**አዲስ ዘመን፡ አሁን አሁን ይህንን የቆየ የመከባበር ባህል ለመበረዝ የሚሞክሩ አልጠፉም። ለእነዚህ ሰዎች የሚያስተላልፉት መልዕክት ምንድን ነው ?**

**ሼህ ሱልጣን ሀጂ አማን፡** እኛ የምናስተላልፈው መልእክት ሀይማኖታዊ ነው። የፖለቲካ ችግራችሁን ሌሎች ጥያቄዎቻችሁን ወደ ሀይማኖታችን አታምጡብን እያልን ነው መልእክት የምናስተላልፈው። ፀሎት አድርገን አደብ እንዲሰጣቸው ዱኣ ነው የምናደርገው።

እኛ በእድሜያችን ብዙ መንግስታትን አይተናል። ብዙ የፖለቲካ አስተሳሰብ የነበራቸውን መንግስታትን ተመለክተናል። ሁሉም በጊዜ ሂደት አልፏል። የማያልፈው ህዝብ ነው፤ የማይጠፋው አገር ነው፤ የማይጠፋው ሀይማኖት ነው ይሄንን ህዝቡ ጠንቀቆ ማወቅ ይገባዋል፤ ሁሉንም ነገር በሰከነ አእምሮ መመልከት ተገቢ ነው።

**አዲስ ዘመን፡ አዲሱ መጅሊስ ከተቋቋም በኋላ ህዝበ ሙስሊሙ ለአገሩ ልማትና ሰላም ዘብ እንዲቆም የተሰሩ ስራዎች ካሉ ቢያብራሩልን?**

**ሼህ ሱልጣን ሀጂ አማን፡** አዲሱ መጅሊስ በአዲስ መልኩ በአዋጅ ተቋቁሟል። ይህ በአዋጅ መቋቋሙ ለእኛ በጣም ትልቅ ነገር ነው። የአዲስ አበባ መጅሊስ እንደተቋቋመው ሁሉ በየክልሉ መጅሊስ ተቋቁሟል። እኛም እንደ አዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች ወደ ክፍለ ከተማም በከተማዋ ወደ ሚገኙ አንድ መቶ ሀያ አራት ወረዳዎች አውርደን አቋቁመናል። የመስጊድም ኮሚቴ ተቋቁሞ ሀይማኖቱ በተቋማዊ ስርኣት ልምድና እውቀት ባላቸው ሰዎች እየተመራ ነው። አሁን ባለው ሁኔታ መንግስት ከጎናችን ቆሞ ትክክለኛ የተቋም ቁመና እንዲኖረው ስላደረገው እጅግ በጣም ደስተኞች ነው። ከመንግስታችን ጋር ቆመንም የሰላሙም የልማቱም ዘብ ለመቆም ተዘጋጅተን በተገቢው ስርኣት እየተመራን ነው ያለነው።

**አዲስ ዘመን፡ በመጨረሻ ሊያስተላልፉት የሚፈልጉት መልእክት ካለ?**

**ሼህ ሱልጣን ሀጂ አማን፡** ለህዝበ ሙስሊሙ ፆማችንን ጨርሰን ኢድ አልፈጥር ላይ ደርሰናል፤ ረመዷን ውስጥ ተጋግዘን ተባብረን እብረን መአድ እንደ ቆረስን ሁሉ ኢድ ደስታ ነውና በኢድም ወቅት ሆነ ከኢድ በኋላ ባሉት ቀናት የመረዳዳት ባህላችን መቀጠል ይገባዋል። በአሁኑ ወቅት በርካታ ዜጎች ችግር ውስጥ ወድቀው ስለሚገኙ በተቻለ መጠን ካለን ላይ እያካፈልን ችግራቸውን እንድንካፈላቸው አደራ እላለሁ።

**አዲስ ዘመን፡ ውድ ጊዜዎን ሰውተው ሀሳቦትን ስላካፈሉን እናመሰግናለን።**

**ሼህ ሱልጣን ሀጂ አማን፡** እኔም አመሰግናለሁ።

# ማህደረ ጤና

# የሲዳማ ክልል የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ጥረት

አስናቀ ፀጋዬ

በኢትዮጵያ ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዘውና የሀገሪቱ ዋነኛ ሞተር የሆነው ወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል ነው ። ይህ ትኩስ ሀይል በሀገሪቱ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ ነውና የእርሱ ጤና መጠበቅ ወሳኝ ጉዳይ ነው ። በተለይ ደግሞ አፍላው ወጣት የህብረተሰብ ክፍል ትኩስ ሀይልና ነገሮችን ቸኩሎ የሚወስን ከመሆኑ አኳያ ያለጥንቃቄና ግራ ቀኝ ሳያይ ሊወስን የሚችል ከመሆኑ አኳያ የጤና ምክርና መሰል የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች ያስፈልጉታል። ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ መንግስት ወጣቶች የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶችን የሚያገኙበትን ስርአት በሀገር አቀፍ ደረጃ ዘርግቶ ሲሰራ ቆይቷል። ነገር ግን ይህ አገልግሎት ለወጣቶች በበቂ ሁኔታ ተደራሽ እንዳልሆነ በሚፈለገው ደረጃ እየተሰጠ እንደማይገኝ ይነገራል ። ለመሆኑ አገልግሎቱ በሲዳማ ክልል እንዴት እየተሰጠ ነው? በዚሁ አገልግሎት አሰጣጥ ረገድ የሚታዩ ክፍተቶች ምንድን ናቸው? ክፍተቶቹን ሞልቶ አገልግሎቱን በተሟላ መልኩ ለመስጠትስ ምን ስራዎች እየተሰሩ ነው? ለነዚህ ጥያቄዎች የክልሉ ጤና ቢሮ መልስ አለኝ ይላል ።

አቶ በላይነህ በቀለ የሲዳማ ክልል ጤና ቢሮ ኃላፊና የጤና ፕሮግራሞች ዘርፍ ኃላፊ ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት የቢሮው ፕሮግራሞች ዘርፍ ሁለት ቁልፍ ዳይሬክተሮች በስሩ አሉት። አንደኛው የእናቶች፣ህፃናትና ስርዓተ ምግብ ዳይሬክቶሬት ሲሆን በፌዴራል ደረጃ ስራ ያስፈፅማል። ሁለተኛው ዘርፍ ደግሞ በሽታ መከላከልና ማጎልበት ነው ። ይህም አጠቃላይ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን ተግባራዊ ያደርጋል ። በሌላ በኩል ደግሞ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና አሀድ ከመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች ጀምሮ እስከ ጤና ኬላ ድረስ የሚሰጡ የጤና አገልግሎቶች በዚህ ዘርፍ ስር ታቅፈው ይከናወናሉ። ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን መከላከል ፣መቆጣጠር ስራዎች በዋናነት በዚሁ ሁለተኛ ዘርፍ ስር ይከናወናሉ ። ተላላፊ ያልሆኑ ትኩረት የሚሹ በሽታዎች ትኩረት ተሰጥቷቸው በዘርፉ ስር ታቅፈው ተግባራዊ ይደረጋሉ ። የግል፣የአካባቢና የጤና ተቋማት የንፅህና አጠባበቅ ቁጥጥር ስራዎች በዘርፉ ተካተው ይሰራባቸዋል።

ኃላፊው እንደሚሉት በስነ ተዋልዶ ጤና ላይ በተለይ በወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ላይ እንደሀገርም ለመስራት ታቅዶ ስራዎች እየተከናወኑ ነው። ከስነ ተዋልዶ ጤና ጋር ተያይዘው የመጡ የተዛቡ አመለካከቶችና ያልተቀረፉ በርካታ ስራ መስራት የሚጠይቁ አሉ። ከነዚህ ውስጥ አንደኛውና በክልሉም የሚታየው ችግር ወጣቶች መረጃ ማግኘት በሚገባቸው እድሜ ክልል ላይ ስነ ተዋልዶ ጤናን በሚመለከት በቂ መረጃ እንዲያገኙ ከማድረግ አንፃር ውስንነት መኖሩ ነው። በተለይ ደግሞ ከቤተሰብ ጀምሮ በትምህርት ቤቶች ከዛም አልፎ በተቋማት ላይ በተቀናጀ መልኩ የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶችን በተመለከተ ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች መረጃ የሚያገኙበትን ሁኔታ አመቻችቶ ከመሄድ አንፃርና በዚህ ረገድ የተጀመሩ ስራዎችም ቢኖሩ አሁንም ክፍቶች እንዳሉ ይታያል።

በሌላ በኩል ደግሞ ከወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ጤና አኳያ በክልሉ ባህል ተፅዕኖ ምክንያት አሁንም ድረስ ያለእድሜ ጋብቻዎች ይታያሉ። ዜሮ ያልተደረጉበት ሁኔታም አለ። ይህም አንዱ በስነ ተዋልዶ ጤና በኩል የሚታይ ችግርና ብዙ መስራት የሚጠይቅ ነው። በተለይ በክልሉ በርቀት የሚገኙ አካባቢዎች ከስነ ተዋልዶ ጤና ጋር በተያያዘ በቂ መረጃ ስለማያገኙ ችግሩ ጎልቶ ይታያል።

ከስነ ተዋልዶ ጤና አንፃር ሌላው በክልሉ የሚታየው ችግር ጤንነቱ ያልተጠበቀ የግብረ ስጋ ግንኙነት በተለይ በአፍላ ወጣቶች ማድረግ ሲሆን ፤ ይህንንም ተከትሎ ያልተፈለጉ እርግዝናዎች በስፋት ይስተዋላሉ ። እነዚህም በስነ ተዋልዶ ጤና ረገድ ክልሉ በስፋት ሊሰራባቸው የሚገቡ ናቸው። በተለይ ወጣቶች በቂ መረጃ አግኝተው በእድሜያቸው ራሳቸውን መከላከል የሚችሉበትን እድል ፈጥሮ ከመሄድ አንፃር ውስንነት እንዳለ ተረጋግጧል። ለወጣቶች አመቺና ትክክለኛ የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት እንዲያገኙ ከማድረግም አኳያ ብዙ መስራት እንደሚጠይቅ በክልሉ ተለይቷል ።

የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎትን ከሌሎች የጤና አገልግሎቶች ጋር ተጣምሮ በእኩል መልኩ የሚሰጥበት



አቶ በላይነህ በቀለ

ሁኔታ በመፈጠር በራሳቸውና ለራሳቸው በሚመች መልኩ አገልግሎቱን ማግኘት ይፈልጋሉ ። ለዚህ ደግሞ አመቺ ቦታና ጊዜ ያስፈልጋል ። ነገር ግን በዚህ ረገድ ብዙ የቤት ስራ እንዳለ ክፍተቱ ይጠቁማል ። ከዚህ በተጨማሪም የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት መስጫውም ጭምር በተለየ መልኩ ወጣቶቹ ሳይፈሩና ሳይሸማቁ ማግኘት የሚችሉበት እድልና ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይፈልጋል ። በክልሉ በተወሰኑ ጤና ተቋማት ውስጥ አገልግሎቱ የሚሰጥ ቢሆንም በሁሉም ጤና ተቋማት ውስጥ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ከመስጠት አንፃርና ወጣቶችን በምክር ፣ በክህሎትና በእውቀት እንዲዳብሩ ከማድረግ አኳያ፣ የእነሱን ስነ ልቦና ታሳቢ ባደረገ መልኩ አገልግሎቱን ከመስጠት አንፃር ውስንነቶች ይኖራሉ። ከዚህም ጋር በተያያዘ አገልግሎቱን ለማጠናከር የጤና ባለሙያዎችን ክህሎት ለማዳበር የአቅም ግንባታ ስራዎችንም ከመስራት አንፃር በክፍት ተለይቷል ።

እንደ ኃላፊው ገለፃ በስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት የሚታዩ ችግሮች በበጀት አመቱ እቅድ ላይ ተለይተዋል። በነዚህ ችግሮች ላይ የመፍትሔ ሀሳብም ጭምር ታሳቢ ባደረገ መልኩ በክልል ደረጃ እቅድ ታቅዷል። እንደሀገርም የብልህ ጅማሮ ተብሎ በእቅድ ተይዟል። የብልህ ጅማሮ ያገቡና እድሜያቸው ከአስራ አምስት እስከ አስራ ዘጠኝ የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ በተለይ ደግሞ ያለእድሜ ጋብቻ የፈፀሙ ወጣቶች ያለእድሜያቸው ልጅ እንዳይወልዱና የነገ ተስፋቸውን ማየት የሚችሉበትን እድል ለመፍጠር ታሳቢ ያደረገ የእቅዱ አካል ነው። በዚሁ መሰረትም በተቋማት ደረጃ ስራው ታቅዶ እየተሰራበት ይገኛል ። በሌላ በኩል ደግሞ ለስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት መረጃ ወሳኝ በመሆኑ ከቤተሰብና ከአቻ ጓደኛ አንፃር ባሉ ማዕከላት ከሴቶች፣ህፃናትና ወጣቶች እንዲሁም ከሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ጋር በመቀናጀት በተሳሰረ መልኩ የጋራ እቅድ እስከታች ድረስ በመዋቅር በማውጣት ወጣቶች መረጃ በበቂ ሁኔታ የሚያገኙበት ስራዎች እየተሰሩ ነው። የወጣቶች የትምህርት ቤት ጤና ክበባትን በመፍጠር እነዚህ የስነ ተዋልዶ ጤና መረጃዎች በሚኒሚዲያ እንዲደርሱ እየተደረገ ነው ። የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችም የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት መረጃዎችን በትምህርት ቤት ሚኒ ሚዲያዎች አማካኝነት ለወጣቶች እንዲያስተላልፉ ሁኔታዎች ተመቻችተዋል ።

ካለእድሜ ጋብቻ ጋር በተያያዘ የሚታውን ችግር ለመቅረፍም በክልሉ ሩቅ ቦታ የሚገኙ ስድስት ወረዳዎችን በመለየትና ተጨማሪ አጋር አካላትን በማፈላለግ በነዚህ አካባቢዎች ላይ እንዲሰሩ የማድረግ ስራዎች እየተከናወኑ ነው ። በዚህም የተሻለ ውጤት እየመጣ ይገኛል ።

በሌላ በኩል ጤና ተቋማት ላይ ያሉ ባለሙያዎች ለወጣቶች በበቂ ሁኔታ የምክር አገልግሎት እንዲሰጡና የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ፈልገው የሚመጡ ወጣቶች አገልግሎቱን በበቂ ሁኔታ እንዲያገኙ ከማድረግ አንፃር ፣ ምቹ ቦታን ከመፍጠር አኳያ እንደክልል በጀት በመያዝ ለወጣቶች አመቺ በሆኑ ቦታዎች ላይ ተጨማሪ ማዕከላትን መገንባትና አገልግሎቱን የማስፋት ስራም እየተሰራ ነው። የጤና ባለሙያዎችን ክህሎት ከመገንባትም አንፃር ስልጠናዎችን በመስጠትና በስነ ተዋልዶ ጤና ዙሪያ የሚሰሩ አጋሮችን በማንቀሳቀስ ወጣቶች አገልግሎቱን እንዲያገኙ የማድረግ ስራዎችም ጎን ለጎን እየተሰሩ ነው። በዛው ልክ ለአገልግሎቱ አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችን የማቅረብ ስራም እየተሰራ ይገኛል። በተለየ መልኩ ደግሞ ዳታዎችን በየወሩ ከታቀደው እቅድ የትኛው ወረዳና ጤና ተቋም አገልግሎቱን በእቅዱ መሰረት በአግባቡ ተግባራዊ እያደረገ እንደሆነ ክፍተቱ የቱ ጋር እንደሆነ በመለየት፣ በመተንተንና መረጃን በመጠቀም ክፍተት ያለባቸው አካባቢዎች አገልግሎቱን እንዲያገኙ የማድረግ ስራዎችም እየተሰሩ ነው ።

ኃላፊው እንደሚናገሩት የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቱ የእቅዱ አካል ተደርጓል ። በተለይ ከጤና ሚኒስቴር ጀምሮ ከተያዘው እቅድ በመነሳት እንደክልል በአሁኑ ወቅት የ2016 ዓ.ም የጤና እቅድ እየታቀደ ነው። በዚህ እቅድ ክፍተቶችን የመለየት ስራዎች ተሰርተዋል ። ከስነ ተዋልዶ ጤና ተደራሽነት አንፃር ሁሉም የጤና ተቋማት አገልግሎቱን አቀናጅተው እንዲሰጡ የማድረግ ስራዎች እየተከናወኑ ነው ። አገልግሎቱ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ እንዲሰጥ ደግሞ ማዕከላትን የመገንባትና የማስፋፊያ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ። እንደሀገር ተሞክሮ የሚሆኑ ስራዎች በክልሉ ተከናውነዋል ። በተለይ ከአስራ አምስት እስከ አስራ ዘጠኝ እድሜ ክልል ውስጥ ያሉ አፍላ ወጣቶች እንደክልል የተሰራው ስራ ሌሎች ክልሎች መጥተው ልምድ የሚቀስሙበት ስራ እየተሰራ ነው ።

የወጣቶችና የሴቶች አደረጃጀቶችን እንዲሁም ተፅዕኖ ፈጣሪ አካላትንም ጨምር በስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ዘርፍ ውስጥ በማስገባት በባህልና መሰል ምክንያቶች አገልግሎቱን የሚጎትቱ ነገሮች እንዲፈቱ የማድረግ ስራዎችም እየተሰሩ ይገኛሉ። በዚህም እንደክልል የተሻለ አፈፃፀምና እንደ ጥሩ ተሞክሮ የሚወሰድ ስራ ለማከናወን ተችሏል። በቅርቡም ከሀገር ውስጥና ከሀገር ውጪ ሰዎች ወደክልሉ መጥተው መልካም ተሞክሮዎችን የሚወስዱበት ሁኔታም እየተመቻቸ ነው።

በኢኮኖሚ ፣ማህበራዊና ፖለቲካ የበለፀገች አገር በመገንባት ለመጪው ትውልድ ማስተላለፍ የሚፈልግ ከሆነ ዛሬ ላይ መስራት አስፈላጊ መሆኑን በመረዳት በየደረጃው ያለው አመራር ጉዳዩን ይዞ እንዲመራ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች በስፋት ተሰርተዋል ። ነገር ግን አገልግሎቱን ተደራሽና ሁሉን አቀፍ ከማድረግ አንፃር ወደፊትም የሚሰሩ ስራዎች ይኖራሉ ።

**‹‹ከስነ ተዋልዶ ጤና ጋር ተያይዘው የመጡ የተዛቡ አመለካከቶችና ያልተቀረፉ በርካታ ስራ መስራት የሚጠይቁ አሉ። ከነዚህ ውስጥ አንደኛውና በክልሉም የሚታየው ችግር ወጣቶች መረጃ ማግኘት በሚገባቸው እድሜ ክልል ላይ ስነ ተዋልዶ ጤናን በሚመለከት በቂ መረጃ እንዲያገኙ ከማድረግ አንፃር ውስንነት መኖሩ ነው። በተለይ ደግሞ ከቤተሰብ ጀምሮ በትምህርት ቤቶች ከዛም አልፎ በተቋማት ላይ በተቀናጀ መልኩ የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶችን በተመለከተ ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች መረጃ የሚያገኙበትን ሁኔታ አመቻችቶ ከመሄድ አንፃርና በዚህ ረገድ የተጀመሩ ስራዎች ቢኖሩ አሁንም ክፍቶች እንዳሉ ይታያል።››**

# ነፃ ሃሳብ



**የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።**

# አዲስ አበባ፡- «የስሟን ክብር በግብሯ»

(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

### የመንደርደሪያችን ወግ

ከተወሰኑ ዓመታት በፊት ይህ ጸሐፊ በሊቢያዋ የሲርት (Sirt) ከተማ ለመገኘት ዕድል አጋጥሞት ነበር። የመገኘቱ ዋና ዓላማ በየራሳቸው ሀገር ደረጃ እና በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ በበጎ ተጽእኖ ፈጣሪነታቸው በተሰባሰቡ የአፍሪካ ምሁራን ጉባኤ ላይ ለመታደም ነበር። ጉባዔው እንዲዘጋጅ ቀጥተኛ መመሪያ የሰጡትና የመወያያ አጀንዳውን የወሰኑት የቀድሞው የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት ኮ/ል ሙሐመድ ጋዳፊ መሆናቸው ለጉባዔተኛው የተገለጠው በመክፈቻ መርሃ ግብሩ ላይ ነበር።

የጉባዔውን ዓላማ በተመለከተ ሌሎች እንደ ሽፋን የተጠቀሱ አፍሪካዊ ጉዳዮች የተነካኩ ቢሆንም በቀረቡት በርካታ የመወያያ ጽሑፎችና ይሰጡ በነበረው የተሳታፊያኑ አስተያየቶች ጎልቶ ይደመጥ የነበረው ማዕከላዊ ሃሳብ "የአፍሪካ ኅብረት ጽ/ቤት ከአዲስ አበባ መነሳት ይኖርበታል" የሚል ዋና አጀንዳ ነበር። የትኞቹ ሀገራት ይህንን ሃሳብ ጮክ ብለው ያንጸባርቁ እንደነበርና በዚህ ጸሐፊ ላይ ተፈጥረው የነበሩ ግልጽ ተጽእኖዎችን በተመለከተ ወደፊት በተገቢ ሁኔታና በዝርዝር ለማቅረብ ይሞከራል።

የኅብረቱ ጽ/ቤት ስለምን ከአዲስ አበባ ከተማ ሊነሳ እንዳስፈለገ በተሳታፊ ከተሰጡት በርካታ አሉታዊ አስተያየቶች መካከል አንዱና ለዚህ ጽሑፍ መጻፍ ምክንያት የሆነው፡- "አዲስ አበባ ከተማ የቆሸሸች ከተማ መሆኗ፤ አደባባዮቿና ጎዳናዎቿ፣ የአፍሪካ ሀገራት ኤምባሲዎች የሚገኙባቸው አካባቢዎችና ሠፈሮቿ በሙሉ በጭቃና በቆሻሻ ክምር የተከበቡ መሆናቸው" በስፋት እየተጠቀሰ ሀገሬ በብዙ የአፍሪካ ልጆች ስትነቀፍ ጆሮዬ እያደመጠ በጉባዔው መካከል ባይተዋር በመሆን ስሜቴ እንደዳመነ ሳልወድ የግድ አስተያየቶቹን አድምጫለሁ።

ውይይቱ የተቋጨው አዲስ አበባ ከተማ "አበባ - New Flower" የሚለው ስሟ ያማረው ለስያሜ አንጂ እውነታው ግን እጅግ ተቃራኒ ስለሆነ የአህጉሪቱ የመሪዎቹ ጉባዔ በጉዳዩ ላይ አጥብቀው ሊያስቡበት እንደሚገባ ምክረ ሃሳብ በመስጠት ውይይቱ እንደተጠናቀቀ አስታውሳለሁ። ምሁራኑም በሚያገኙት አጋጣሚዎች ሁሉ "የኅብረቱ ጽ/ቤት ከአዲስ አበባ እንዲነሳ በሚካሄደው ዘመቻ በንቃት እንዲሳተፉ ከአዘጋጁ ክፍል የአደራ መልእክት እንደተላለፈላቸውም ትዝ ይለኛል።

በዚያ ጉባዔ ላይ የተገኙት አብዛኞቹ የአፍሪካ ምሁራን በዚህ አጀንዳ ላይ አስተያየታቸውን ይሰጡ የነበረው በተሟሟቀ ስሜት ብቻ ሳይሆን፤ ጭብጨባም ጭምር እየታከለበት ነበር። በሀገሬ ላይ ይህንን መሰል አሸማቃቂ አስተያየት ሲዥጎደጎድ ተሸማቆ ማዳመጥ እንደ አንድ ዜጋ እንደምን ስሜትን እንደሚያቆስልና ቁጭት ላይ እንደሚጥል አንባቢው የሚረዳ ይመስለኛል። የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በተቋቋመበት ሰሞን በሀገራችን ድምጻዊያን ከተዜሙት ዜማዎች መካከል ስለ አዲስ አበባ በስፋት የተደመጠው ዜማ፤

**አማረች አሸበረቀች፣**
**ለአፍሪካ ኅብረት መሠረት ሆነች።»**

የሚለውን መልዕክት በሃምሳ ዓመታት ዕድሜ ውስጥ ሀገሬ መተግበር ተስኖት ከነጭራሹ "የኅብረቱ ጽ/ቤት" ከአዲስ አበባ ይነሳልን መባሉ በአስተያየት ሰጪዎቹ ላይ ብቻ ከመፍረድ ባሻገር ራሳችንን በራሳችን መውቀስም በተገባን ነበር የሚል የግል አቋም ነበረኝ። ብዕረ መንገዳችንን "የኅብረቱ ጽ/ቤት ምን ሲደረግ ከአዲስ አበባ ይነሳል!" በሚል ሙግት የአህጉሪቱ መሪዎች በሚሰባሰቡባቸው መድረኮች ሁሉ ተገቢውን ታሪካዊና ወቅታዊ ማስረጃዎችን እየጠቀሱ በድፍረትና በጽናት ይከራከሩ ለነበሩት ቀደምት የሀገራችን መሪዎች ክብርና ሞገስ ይሁንላቸው።

**አዲስ አበባ ከተማችን**
**በልጆቿ ብቻ ሳይሆን በባዕዳንም ጭምር ብዙ ተብሎላታል፤ ብዙም ተብሎባታል። በርካቶች ዘፍነውላታል፤ በርካቶችም ወቅሰዋታል። አያሌዎች አድንቀዋታል፤ ሺህዎችም ተቀይመዋታል። በተቃርኖ የሚገለጹትን እነዚህን መሰል የአያዎ (አይ+አዎ፤ Paradox) ገለጻዎች በተመለከተ ብዙ ሲነገርና ሲጻፍ ስለኖረ የተባለውን ደግሞ መከለሱ አስፈላጊነቱ አልታየኝም። ይልቁንስ በከተማዋ ውስጥ እየተከናወኑ ያሉትን በጎ የልማት ጅምሮች በወፍ በረር ቅኝት እየጠቃቀስን አዲስ አበባን በማድነቅ እየተነቃቃ ባለው መንፈሷ ላይ ሙቀት መጨመሩ ይበልጥ ያተጋት ይመስለናል**

"በራሷ አረም እባብ ይዛ ታስፈራራለች" እንዲሉም ይህ ጸሐፊ በዚያ ጉባዔ ላይ እንዲገኝ ጥሪ በደረሰው ወቅት ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ስለ ጉዞው ሁኔታውን በአግባቡ ለማሳወቅ ሞክሮ በወቅቱ ከነበሩ አንድ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊ "ጉዳዩ የግልህ እንጂ ሀገርን ስለማይመለከት መሄድ ያለመሄድ የራስ ጉዳይ ነው" በማለት የሰጡኝ መራራ አስተያየት ዛሬም ድረስ በአእምሮዬ ውስጥ እንዳቃጨለ ይኖራል።

### «እንደ ስማቸው የሆኑ ከተሞቻችን»

የስማቸው ትርጉምና እውነታው ከተጣጣመላቸው የሀገራችን ከተሞች መካከል ሁለቱ ባሕር ዳርና አርባ ምንጭ ውብ ከተሞቻችን በቀዳሚነት ቢጠቀሱ አግባብ ይሆናል። ከመቶ ዓመት በላይ ያስቆጠረችው ውቧ የባሕር ዳር ከተማም ሆነች ከስልሳ ዓመታት ከፍ ያለ የዕድሜ ፀጋ የተጎናጸፈችውና በአስደናቂ የተፈጥሮ መስህብ የተባረከችው የአርባ ምንጭ ከተማ ሁለቱም ድምቀታቸውና ሳቢነታቸው ከስማቸው ጋር የሚገጥም ነው።

የጣና ውበት ድምቀቷ የሆነውና በቅርቡም በዐባይ ወንዝ ላይ እየተገነባ ያለው አዲሱ ድልድይ አገልግሎቱን ሲጀምር በርግጥም ከተማዋ የሀገራችን ፈርጥ እንደምትሆን በትልቅ ጉጉትና ተስፋ እየተጠበቀ ነው።

ተፈጥሮ ያለ ስስት እምቅ ሀብቶቿን በአደራ ያሸከመቻትና ከአርባ በላይ ምንጮች የሚንፎለፎሉባት "የእግዜር ድልድይዋ" መገኛ አርባ ምጭም በተለያዩ የልማት ትሩፋቶች ውበቷ እየደመቀ ስለሆነ ተናፋቂና ተወዳጅነቷ እየጨመረ በመሄድ ላይ ነው። "ስምን መልአክ ያወጣል" የሚለው ሀገራዊ ብሂል በእነዚህ ሁለት ከተሞች ላይ ገቢራዊ ሆኗል ቢባል ከግነት አያስቆጥርም። እነዚህ ሁለት አንጋፋ ከተሞቻችን እንደ ስማቸው እንዲሁ ስለሆኑ የትናንቶቹን ስያሜ አውጭና የዛሬዎቹን አስተዳዳሪዎች ብናመሰግን ለተሻለ ውጤት ስለሚያነቃቃቸው "አሹ! በርቱልን!" በማለት አክብሮታችንን እንገልጽላቸዋለን።

### «እንደ ስሟ ለመሆን የምትታትረው አዲስ አበባችን»

አዲስ አበባ ከተማችን በልጆቿ ብቻ ሳይሆን በባዕዳንም ጭምር ብዙ ተብሎላታል፤ ብዙም ተብሎባታል። በርካቶች ዘፍነውላታል፤ በርካቶችም ወቅሰዋታል። አያሌዎች አድንቀዋታል፤ ሺህዎችም ተቀይመዋታል። በተቃርኖ የሚገለጹትን እነዚህን መሰል የአያዎ (አይ+አዎ፤ Paradox) ገለጻዎች በተመለከተ ብዙ ሲነገርና ሲጻፍ ስለኖረ የተባለውን ደግሞ መከለሱ አስፈላጊነቱ አልታየኝም። ይልቁንስ በከተማዋ ውስጥ እየተከናወኑ ያሉትን በጎ የልማት ጅምሮች በወፍ በረር ቅኝት እየጠቃቀስን አዲስ አበባን በማድነቅ እየተነቃቃ ባለው መንፈሷ ላይ ሙቀት መጨመሩ ይበልጥ ያተጋት ይመስለናል። የአዲስ አበባ ከተማ ባህል ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ለኪነ ጥበባት ባለሙያዎችና ለደራስያን ሚያዝያ 12 ቀን 2015 ዓ.ም የከተማዋን አስደማሚ ሰፋፊ ፕሮጀክቶች አስጎብኝቷል። የተጎበኙትን አስመስጋኝ ፕሮጀክቶች በተመለከተ ወደፊት በዝርዝር ለማቅረብ ስለሚሞከር ለጊዜው በአንድ ጉዳይ ላይ ብቻ አተኩራለሁ።

ከአዲስ አበባ ክፍለ ከተሞች መካከል በአንፃራዊነት አዲሱ የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ብዙ ወቀሳና እምባ ሲዘንብበት እንደከረመ በከተማዋ ነዋሪዎች ዘንድ የታወቀ ብቻ ሳይሆን በብዙ ማስረጃም የተረጋገጡ መረጃዎች በይፋ ለሕዝቡ ሲነገሩ መሰንበታቸውም አይዘነጋም። ይህ በዘርፈ ብዙ ችግሮች ተተብትቦ "በልጅነት ልምሻ" የተጠቃው ክፍለ ከተማ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ያሳየው የልማት እመርታ "ለካስ ከልብ ካለቀሱ እምባ አይገድም" የሚለውን ሀገርኛ ብሂል እንድናስታውስ ግድ ብሎናል።

በዚሁ በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ውስጥ ያሉ አደባባዮችና የመንገድ አካፋዮች በተዋቡ አበቦች ተንቆጥቁጠው ማስተዋል በርግጥም አዲስ አበባ በአዛውንትነት ዕድሜዋም ቢሆን እንደ ስሟ እያበበች ስለመሆኗ በጥሩ አብነት ሊጠቀስ ይችላል። የክፍለ ከተማው ውጫዊ ገጽታ ብቻ ሳይሆን አስተዳደራዊ ዘርፉም የመነቃቃት መንፈስ እየተስተዋለበት ነው። ምሉዕ በኩለሄ ነው ለማለት ግን በፍጹም አይቻልም፤ ጊዜውም አይደለም። የዚህን ክፍለ ከተማ የልማትና የአስተዳደር ጉዳዮች በተለየ ሁኔታ በቅርበት እየተከታተሉ ለሚያስፈጽሙት ለክብርት የከተማችን ከንቲባ ለወ/ሮ አዳነች አቤቤ እስካሁን ለተመዘገበው ውጤት ማመስገኑ ተገቢ ይመስለናል። ቀሪ ሥራዎቹ የትዬለሌ መሆናቸውን ግን እንኳን እኛ ዜጎች ቀርተን መሪዎቿም ቢሆኑ ይጠፋቸዋል ለማለት ይከብዳል።

የኑሮው ጫና፣ የቤት ኪራዩ አይደፈሬነት፣ የቢሮክራሲው ጥልፍልፍነትና የፍትሕ ጥማቱ እዬዬ እያሰኘ የሚያስለቅሳቸውና ችግሩ ያኀበጣቸው የከተማዋ ነዋሪዎች ከላይ የተገለጸው ዓይነት የማበረታቻ ምሥጋና ቁብ እንደማይሰጣቸው አይጠፋኝም። ይህንን ጽሑፍ ለማንበብ እድሉ የሚገጥማቸው አንዳንድ ወገኖችም "ውጭውን በአበባ ከማስዋብ፤ የውስጥ ጠረንን ማሳመር" የሚሉ ብሶቶች ሊያቀርቡ እንደሚችሉም ይገባኛል። የሆነው ሆኖ ግን ለትችት እየተሽቀዳደምን ለምስጋና ንፉግ መሆን የሰብእና መገለጫ ስላልሆነ መልካም ሲሰራ "አበጃችሁ በርቱ!" ማለት "ላልተሰሩት ሥራዎች ማስታወስ" ለተሻለ ሥራ ስለሚያነሳሳ ማመስገኑ የግድ ይላል።

በዚህ ጸሐፊ እምነት በከተማችን ውስጥ የሚስተዋሉ በርካታ አስተዳደራዊ ህፀፆች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በተለየ ሁኔታ ግን ዋና ዋና የከተማይቱን አደባባዮችን፣ የአውራ ጎዳና ዳርቻዎችንና አካፋዮችን በተዋቡ አበቦች ለማሳመር የሚደረገው ጥረት በተለየ ሁኔታ ሊደነቅ ይገባዋል። ለአንድ መቶ ሠላሳ ስድስት ዓመታት ያህል ስሟና ገጽታዋ እንደተቃረነ በጽኑ እንቅልፍ ስታንጎላጅጅ ለኖረችው አዲስ አበባ ለስሟ ትርጉም የሚመጥን ሥራ እየተሠራላት መሆኑ ለክርክር የማይዳርገው የተግባር ፍሬው በግልጽ ስለሚታይ ነው።

ለአብነት ያህል ከላይ በተቀስኩት የመኖሪያዬ ክፍለ ከተማ በሆነው በለሚ ኩራ እና በየካ፣ በቦሌ፣ በአራዳና በንፋስ ስልክ ላፍቶ ወዘተ. የከተማዋ ክፍሎች አደባባዮችና የመንገድ አካፋዮች ላይ ፈክተው የሚታዩት አበቦችና መናፈሻዎች ለከተማዋ ውበት ብቻ ሳይሆን ለነዋሪዎቿና ለእንግዶቿ ትልቅ የመንፈስ መነቃቃትና ደስታ እንደሚፈጥሩ መካድ አይቻልም።

ከተማዋን የሚያስተዳድሩት ሹማምንት ወደየክፍለ ከተሞች ወረድ በማለት የዘጠና ቀን እቅዳቸውን ሲገመግሙና የተጠናቀቁትንም ሲያስመርቁ በየሚዲያዎቹ እየተከታተልን ነው። እርግጥ ነው በየክፍለ ከተሞቹ በርካታ የችግር ቋጥኞች በሙሉ ተፈረካክሰው ደልዳላ ሜዳ እንዳልሆኑ ይገባናል። ነው ብለን ብንከራከርም ከአንባቢው ጋር ብቻ ሳይሆን ጥሉ ከራሳችን ኅሊና ጋር እንደሚሆን አይታበልም። እንዲዚያም ቢሆን ግን ትርጉም ያላቸው በርካታ ፕሮጀክቶች በአዲስ አበባችን እየተተገበሩ መሆናቸውን ብንክድ ከራስ ጋር መጣላት ይሆንብናል። ለተከናወኑት መልካም ተግባሮች አመስግነን ባልተሰሩት ሥራዎች ላይ አቤቱታ ማቅረቡ ተገቢም አግባብም ይሆናል።

በተለየ ሁኔታ ግን በከተማችን ውስጥ እየተከናወኑ ያሉት የአረንጓዴ ልማት ሥራዎችና የማስዋብ ጥረቶች ግለታቸውን ሳይቀዘቅዝና የወረት ሩጫ ሳይሆን በዚሁ የሚቀጥል ከሆነ አዲስ አበባችን "እንደ ስሟ ተለውጣለች" ተብላ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሳይቀር እንደምትወደስና በምሳሌነት እንደምትጠቀስ አንጠራጠርም።

ነፍሰ ሄሩ ድምጻዊ ዓለማየሁ እሸቴ ከግማሽ ክፍለ ዘመን በፊት፤ "አዲስ አበባ ቤቴ" ብሎ ያንጎራጎረውና ሌላው ዘመነ አቻው ድምጻዊ ጌታቸው ካሣ "አዲስ አበባ" በማለት ያዜመው ሙዚቃ እንደ አዲስ ታድሰው የነዋሪዎቿ ዝማሬዎች የማይሆኑበት ምክንያትም አይኖርም። "እንደ ስሟ እንዲሁ..." በማለት በነጠብጣብ የምንተወው ሀረግ በመደምደሚያ ቃል ነፍስ ዘርቶና ደምቆ ጎላ ተብሎ እንዲገለጽ አሁን የተጀመረው መልካም ሥራ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።

ለእስከ ዛሬው የአደባባዮቻችን ውበትና ድምቀት በየደረጃው ለሚገኙት የከተማዋ አመራሮች "ገለቶማ!" በማለት ምሥጋናችንን እናቀርባለን። በተለየ ሁኔታ ደግሞ አደባባዮቻችንንና ጎዳናዎቻችንን ለማስዋብ ቀን ከሌት ለሚደክሙትና በትጋት ተግባራቸውን ለሚከውኑት ባለ ወርቃማ እጆች የዕጽዋት ተንከባካቢዎችና የጽዳት ባለሙያዎች ከፍ ያለ የአድናቆትና የአክብሮት ምሥጋናችን ይድረሳችሁ እንላችኋለን። ሰላም ለሕዝባችን፤ ለዜጎችም በጎ ፈቃድ።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተናጋሪው ዶሴ

## የ‹‹ፔሮቪደንት ፈንድ›› እና የመስሪያ ቤት ብድር ያስከተለው ውዝግብ

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

ግለሰቡ ይህን ግዙፍ ተቋም ከመክሰስ ወደኋላ አላሉም። በችሎት ፊት፤ በፍርድ ዓደባባይ አቅርበውት እውነተኛ ፍርድ በመሻት እስከመጨረሻው በህግ ለመፋለም ወስነው ተነስተዋል። ሥመ ገናናው ድርጅትም ስሜ አይጎድፍም፤ የግለሰቡንም ድርጊት በዋዛ አላልፍም ሲል የህግ ክፍሉን ባለሙያዎች ምክረ ሃሳብ በመያዝና ይጠቅሙኛል ያላቸውን ሰነዶች በመሰነድ በችሎት ፊት ቀርቦ ለማሸነፍ ቆርጦ ተነስቷል።

71507 ለዚህ የክስ መዝገብ ለብቻው የሰነድ መለያ ቁጥር በሚል ተሰጥቶታል። ከሥር ፍርድ ቤት ጀምሮ እልክ አስጨራሽ ክርክሮች ተደርገውበታል፤ ዳሩ ግን ይህ ነው የሚባል መቋጫ አላገኘም። ክርክሩ በሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ መግባባት ባለመደረሱ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት የተላለፈ ጉዳይ ሆነ። የፌደራል ከፍተኛው ፍርድ ቤትም ከሥር ፍርድ ቤት የተላለፈለትን ጉዳይ በአንክሮ ተመለከተው፤ ግራ ቀኙን አመዛዘነ። በመጨረሻም የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ላይ በመመርኮዝ ብሎም ተገቢነት አላቸው ያላቸውን ህግና አንቀፆችን በማጣቀስ በተጨማሪም የተጠሪ እና አመልካችን መረጃዎችን በማመሳከር የራሱን ውሳኔ አሳለፈ።

ዳሩ ግን ጉዳዩ በዚህ አላበቃም። ሰበር ሰሚ ችሎት ደረሰ። የዚህን ፋይል የመጨረሻ የሰበር ውሳኔ ለመስማት ደግሞ መጋቢት 10 ቀን 2004 ዓ.ም የመጨረሻው ቀን ሆኖ ተቆርጦለታል። አምስት ዳኞችም ከመንበሩ ላይ ተቀምጠዋል። ታዳሚዎችም ከችሎቱ ውስጥ ተገኝተዋል። በዕለቱ የተሰየሙ ዳኞችም ግራ ቀኙን የመረመሩትን ለመበየን በሰዓቱ የተገኙ ሲሆን በአመልካች እና በተጠሪ መካካል ያለውም ውዝግብ መቋጫውን ያገኛል-መጋቢት 10 ቀን 2004 ዓ.ም።

አመልካች ሜድሮክ ወርቅ ማዕድን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሲሆን የተቋሙ ነገረ ፈጅ አቶ በአካል ቀርበዋል። ተጠሪም አቶ ሰይፈ ተፊሪ የተባሉ ግለሰብ ሲሆኑ በሌሉበት የሚታይ ሆኖ መዝገቡ ተመርምሮ ለመጨረሻ ፍርድ ከመንበሩ ላይ ተገኝቷል፤ ውሳኔም ተሰጥቶበታል።

### ጉዳዩ ምን ነበር?

በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት በሚገዛው ግንኙነት ውስጥ ሰራተኛው ስራውን ከመልቀቁ በፊት የወሰደውን ብድር ሳይመልስ ስራውን በገዛ ፈቃድ ሲለቅ አሰሪው ለሰራተኛው ሊከፈለው ከሚገባው የፔሮቪደንት ፈንድ ገንዘብ ቀንሶ ለማስቀረት የሚችልበትን የህግ አግባብ የሚመለከት ነው። ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው ሲሰሩ ከቆዩ በኋላ በገዛ ፈቃዳቸው ስራቸውን መልቀቃቸውን ገልፀው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው።

ተጠሪ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ከዘረዘራቸው የክፍያ ዓይነቶች አንዱ የፔሮቪደንት ፈንድ ሲሆን አመልካች ለዚሁ ለተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ በሰጠው መከላከያ መልስ ተጠሪ የፔሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ መሆኑን ሳይክዱ ለተጠሪ ብር 9,000 /ዘጠኝ ሺህ/ መስጠቱን፣ ቀሪውን በተመለከተ ግን አመልካች ለተጠሪ ብድር አበድሮት እንደነበረና ብድሩን ሙሉ በሙሉ ባለመክፈሉ በመካከላቸው ባለው ስምምነት መሰረት ያስቀረው መሆኑን ጠቅሶ ሊከፈለው አይገባም በማለት ተከራክሯል።

### የሥር ፍርድ ቤት ምን አለ?

የስር ፍርድ ቤትም በዚህ ረገድ የቀረበውን የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ተጠሪ ብር 9,000 መውሰዳቸውንና ከአመልካች በብድር የወሰዱት ገንዘብ መኖሩን ያለመካዳቸው ተረጋግጧል በማለት አመልካች ከተጠሪ ለዕዳ መክፈያነት ያስቀረውን የፔሮቪደንት ፈንድ ቀሪ ለመክፈል ሊገደድ አይገባም በማለት ወስኗል።

በዚህ ውሳኔ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የፔሮቪደንት ፈንድ ከደመወዝ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ካላቸው ክፍያዎች አንዱ መሆኑን ገልፆና ያለተጠሪ ስምምነት ደግሞ አሰሪ የሆነው አመልካች ለዕዳ መክፈያነት የፔሮቪደንት ፈንድ ቆርጦ ለማስቀረት የማይችል ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 59/1/ ስር የተመለከተ መሆኑን በዋቢነት ጠቅሶ አመልካች ቀሪ የፔሮቪደንት ፈንድ ክፍያ ብር 11,000.00 /አስራ አንድ ሺህ ብር/ ለተጠሪ ይክፈላቸው በማለት የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የሰጠውን የውሳኔ ክፍል ሽሮታል ሲል ይደመድማል። ታዲያ ይህ ጉዳይ በዚህ ብቻ ሊያበቃ አልቻለም፤ ወደ ሌላ የክስና የውሳኔ ምዕራፍ ተሸጋገረ።



### ሰበር የደረሰው መዝገብ

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪ በድርጅቱ ህብረት ስምምነትና በብድር ፖሊሲ መሰረት የወሰዱትን ብድር ሳይከፍሉ ስራውን በገዛ ፈቃዳቸው ከመልቀቃቸውም በላይ ብድሩ መኖሩንና ሥምምነት መኖሩንም ሳይክዱ አመልካች ከፔሮቪደንት ፈንዴ ቆርጦ እዳውን ማስቀረት አይችሉም ተብሎ መወሰኑ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 59 ድንጋጌን ይዘት፣ የግራ ቀኙን ክርክርና የፍርድ ቤቱ ውሳኔ በድርጅቱ የብድር ፖሊሲ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን አሉታዊ ተፅዕኖ በአግባቡ ባላገናዘበ መልኩ ነው በማለት ውሳኔው እንዲሻር ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው። በዚህ ሂደት ግን ብዙ ክርክሮች ተደረጉ። ለውሳኔም ሰጪውም አካል ከቀድሞ መረጃዎች ጋር በማጣመር የመጨረሻ ውሳኔ ለመስጠት በርካታ ሰነዶችም አብረው ተያይዘዋል።

አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪ ከስራ ስንብቱ በፊት የነበረበትን እዳ ከፔሮቪደንት ፈንድ ላይ ሊቆረጥ/ ሊቀነስ/ አይገባውም በማለት በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ተደረገ።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል። በዚህ ምርመራም ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችሉ ሁኔታዎችም ግልጽ እየሆኑ መጡ።

በዚህ ሁሉ የክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ነገር ቢኖር፤ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የመሰረቱትን የሥራ ውል ግንኙነት ያቋረጡት በገዛ ፈቃዳቸው መሆኑን፣ የሥራ ውል ከመቋረጡ በፊት ደግሞ በሠራተኝነታቸው ከአሰሪው በተሰጣቸው መብት መሰረት ብድር ወስደው ብድሩን እንደተጠቀሙና ዕዳውን ሙሉ በሙሉ ሳይከፍሉ የስራ ስንብት ጥያቄን ያቀረቡ መሆኑን ነው። በተጨማሪም ብድሩ ያለባቸው መሆኑንም ደግሞ በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር ያመኑ መሆኑ ተረጋጋጠ። እንዲሁም የብድሩ መሰረትም በአሰሪው ድርጅት ውስጥ ያለው የሕብረት ሥምምነት እና የብድር ፖሊሲ መሆኑ አከራካሪ ያለመሆኑን ነው። ከፍ ሲል እንደተገለፀው የአሁኑ ተጠሪ ዕዳ የለብኝም በሚል ያቀረበው ክርክር የለም ተብሎ በስር ፍርድ ቤት የታለፈ ስለሆነ አመልካች ዕዳው የተጠሪ መሆን ያለመሆኑን ሌላ ክስ እንዲመሰረት የሚጠበቅበት ህጋዊ ምክንያት የለም።

የአዋጁ አንቀጽ 59/1/ በህብረት ስምምነት በተወሰነው መሠረት ከሠራተኛው ደመወዝ ላይ መቀነስ እንደሚቻል የሚያስረዱ ሲሆን የፔሮቪደንት ፈንድ ከደመወዝ ጋር ጥብቅ ቁርኝነት ያለው የክፍያ ዓይነት ነው ቢባል እንኳ ተጠሪ ዕዳ ያለባቸው ስለመሆኑ በክርክሩ ሂደት ባልተካሄደት ሁኔታ ሌላ ግልፅ ሥምምነት የሚያስፈልግበት ህጋዊ ምክንያት የለም። በመሆኑም ተጠሪ ከአመልካች ድርጅት የወሰዱትን የብድር ገንዘብ ሳይመልሱ በገዛ ፈቃዳቸው ሥራቸውን በለቀቁበትና ዕዳው መኖሩንም በሥራ ክርክር ችሎት ባመኑበት ሁኔታ እዳውን ከፔሮቪደንት ፈንድ ቆርጦ ለማስቀረት ሌላ ግልጽ የሆነ ስምምነት ያስፈልግ ነበር ተብሎ በፌደራል ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮችን ከድንጋጌው መንፈስ እና ይዘት ጋር ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ሆኖ አግኝተናል ሲል ህጋዊ ትንታኔዎችን ይሰጣል።

በአጠቃላይ በዚህ ጉዳይ የአሁኑ ተጠሪ የወሰደውን የብድር ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ሳይመልሱ ስራውን በገዛ ፈቃዳቸው በለቀቁበትና እዳውም የሚመለከታቸው መሆኑን በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍድር ቤት በተደረገው ክርክር ባላመኑት ሁኔታ ከፔሮቪደንት ፈንድ እዳውን ቀንሶ ለማስቀረት ግልፅ ስምምነት የለም ተብሎ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መወሰኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 59/1/ ስር የተመለከተውን የድንጋጌውን መንፈስ ከአመልካች ድርጅት የህብረት ስምምነት እና የብድር ፖሊሲ ጋር ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ውሣኔው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል። በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል ሲል ማብራሪያ እና አባሪ መረጃዎችን በማጣቀስ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጥቷል- ሰብር ሰሚ ችሎት።

### ውሳኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ መለያ ቁጥር 107857 በ06/11/2003 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፌደራል ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽሯል።

2. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ መለያ ቁጥር 57350 በ19/08/2003 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በፌደራል ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ፀንቷል።

3. አመልካች ከተጠሪው ፔሮቪደንት ፈንድ በዕዳው ምክንያት ቀንሶ የወሰደውን ገንዘብ ሊመለስ አይገባም ሲል በየነ። በዚህ ፍርድ ቤት የተካሄደው ክርክር ግራ ቀኙ ወጪያቸውን በየራሳቸው ይቻሉ በማለትም መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ሲል የመጨረሻውን የሰበር ውሳኔ አሳለፈ።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

# ከሳይንስ የተጣሉ የበዓል ወቅት አመጋገቦች

**ቦጋለ አበበ**

ኢትዮጵያውያን ካለፈው ሳምንት ጀምሮ ታላላቅ ሃይማኖታዊ በዓሎችን እያከበሩ ይገኛሉ። ህዝበ ክርስቲያኑ ባለፈው እሁድ ትልቁን የትንሳኤ በአል አክብሯል፤ በዚህኛው እሁድ ደግሞ ዳግማ ትንሳኤን ያከብራል። በሙስሊሙም ዘንድ ታላቁ የረመዳን ፆም ተጠናቆ ትናንት የኢድ አልፈጥር በዓል በድምቀት ተከብሯል። እነዚህ ሁለት ታላላቅ ሃይማኖታዊ በአላት ሲከበሩ አንድ የሚያመሳስላቸው ጉዳይ አለ። ይህም የእርድ በዓል መሆናቸው ነው።

በበዓላት ወቅት ከወትሮው የተለዩ የምግብና መጠጥ ዓይነቶችን መመገብ የተለመደ ቢሆንም፣ አንዳንዶች በበዓላት ወቅት በአመጋገብ ሳቢያ ጤናቸውን ያጣሉ። በበዓላት ወቅት አመጋገብ በተለያየ ሁኔታ ጤና የሚነሳ ወይም ላልተጠበቀ አደጋና ሕይወት ማለፍ ሊዳርግ እንደሚችል የጤና ባለሙያዎች ደጋግመው ይናገራሉ።

ብዙዎቻችን ግን የመጣው ይምጣ ብለን በአብዛኛው የበዓላት ሰሞን ቀዩን ከሻኛው ካልቆረጥን፣ ጮማው በጉሮራችን ካልወረደ በዓል በዓል መስሎ አይታየንም። ይህም የአመጋገብ ባህል ለተለያዩ ችግሮች ሲዳርገን ማየት አዲስ አይደለም። ለዚህ ምክንያቶቹ ደግሞ ከመጠን በላይ መመገብ፣ ስጋና የእንስሳት ተዋጽዖን ማዘውተርና ብዛት ያላቸው የአልኮል መጠጦች መውሰድ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

አጿማትን ተከትለው በሚመጡ በዓላት አመጋገብን ማስተካከል እንደሚገባ የሥነ ምግብ ባለሙያዎችም ይመክራሉ። በተለይም የትንሣኤ በዓል በመጣ ቁጥር አንዳንድ ሰዎች ቅባት የበዛበት ምግብ ተመግበው ለሕመም የሚጋለጡበት አጋጣሚ ብዙ እንደመሆኑ በዚህ ወቅት ጥንቃቄ ማድረጉ የግድ ነው። የትንሣኤ በዓል ከረጅም ጊዜ ጾም በኋላ የሚመጣ በዓል በመሆኑ ቅባት የበዛበት ምግብ እና አልኮል መጠቀም ተገቢ አለመሆኑን የዘርፉ ባለሙያዎች ይመክራሉ። በብዙዎች ዘንድ ግን በዚህ ወቅት የአመጋገብ ባህሉ ከሳይንሱ የተጣላና ተቃራኒ ነው።

> **በበዓል ወቅት ሰዎች አልኮልን በብዛት ይጠቀማሉ። ምክንያታቸው ደግሞ የምግብ መፍጨትን ያፈጥናል በሚልና በበዓል ወቅት እንደ መዝናኛ ስለሚቆጠር ነው። ነገር ግን፣ አልኮል አብዝቶ መውሰድ ጉበት በመጉዳት ቅድሚያውን ቦታ ይወስዳል። በበዓል ሰሞን ስጋን እና አልኮልን በአንድ ላይ መውሰድ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እንደሚያመዝንም ጥናቶች ያሳያሉ**

የአብዛኛው ኢትዮጵያዊያን የበዓል አመጋገብ ተመሳሳይ ነው። ጾም ሲፈታ የእንስሳት ተዋጽዖዎችን ማለትም ሥጋ፣ ዶሮ፣ እንቁላል፣ ወተት፣ ቅቤ እና መሰል ምግቦችን መመገብ የተለመደ ነው። ይህ ደግሞ ለረጅም ጊዜ ከቅባት ርቆ የቆየው ጨጓራ በአንድ ጊዜ ለመቀበል ይቸገርና ለሕመም ይዳርጋል። ለበዓል ቅባት የበዛበት ምግብ ማዘጋጀት የተለመደ ቢሆንም፣ መጥኖ መሥራት ተገቢ ነው። ጤናን ለመጠበቅ ሰውነትን ቀስ በቀስ አለማምዶ መመገብ ይገባል።

በበዓል ወቅት ማኅበረሰቡ የሚመገባቸው የእንስሳት ተዋጽዖዎች በተፈጥሯቸው ከፍተኛ ቅባት አላቸው። በጾም ወቅት የሚዘወተሩ ምግቦች ቅባት ያልበዛባቸው በመሆናቸው ጨጓራ ለሥርዓተ ልመት ይጠቀምባቸው የነበሩ ንጥረ ነገሮች (ኢንዛይሞች) መጠናቸው ይቀንሳል። በዚህም ጨጓራ ከለመደው ሥርዓት የወጣ አመጋገብ ማለትም ቅባት የበዛባቸውን ምግቦች መመገብ ስንጀምር ሆድ መንፋት፣ ማቃጠል፣ ቁርጠት፣ የምግብ ፍላጎት መቀነስ እና መሰል ሕመሞች ያስከትላል። አንዳንድ ጊዜ ከበዓል አመጋገብ ጋር በተያየዘ ከሚከሰቱ የተለመዱ ሕመሞች በተጨማሪ በተለይ ከስጋ አመጋገብ ጋር በተያየዘ በድንገት ለሞት የሚያጋልጡ አደጋዎች ሊከሰቱ ይችላሉ። ከእነዚህም መካከል በስጋ ውስጥ የሚገኙ አጥንቶች ለድንገተኛ ሞትና አደጋ ሊዳርጉ ይችላሉ።

ስጋ በተፈጥሮው በቫይታሚን ኤ፣ ቢ እና ዲ የበለጸገ ሲሆን፣ በእነዚህ ቫይታሚኖች የበለጸገ መሆኑ ደግሞ ለዐይን መስተካከል፣ ለጥርስ ጥንካሬና ለአዕምሮ ጤንነት ትልቅ አስተጽዖ አለው። በዚህ ወቅት ግን ቀይ ስጋና ጮማን አዘውትሮ መመገብ አይመከርም። ጥናቶች እንደሚያሳዩት ቀይ ስጋን አዘውትሮ መመገብ ለልብ ሕመምና ለስኳር ሕመም መንስኤ ሊሆን ይችላል።

አስገራሚው ነገር በነዚህ በአላት ወቅት ከአመጋገብ ጋር በተያያዘ የሆድ ህመም ሲገጥመን የምንወስደው እርምጃ ነው። ወደ ህክምና በመሄድ ተገቢውን መድኃኒት ከመውሰድ ይልቅ አልኮልን መጠቀም የሚቀናቸው ብዙዎች ናቸው።

በበዓል ወቅት ሰዎች አልኮልን በብዛት ይጠቀማሉ። ምክንያታቸው ደግሞ የምግብ መፍጨትን ያፈጥናል በሚልና በበዓል ወቅት እንደ መዝናኛ ስለሚቆጠር ነው። ነገር ግን፣ አልኮል አብዝቶ መውሰድ ጉበት በመጉዳት ቅድሚያውን ቦታ ይወስዳል። በበዓል ሰሞን ስጋን እና አልኮልን በአንድ ላይ መውሰድ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እንደሚያመዝንም ጥናቶች ያሳያሉ።

ብዙዎች በበዓላት ወቅት ሳይንሱ ከሚለው በተቃራኒ ሲመገቡ ያታያል። የሚገርመው ግን ሳይንሱን ጠንቅቀው የሚያውቁ ሰዎች ጭምር የመጣው ይምጣ ብለው የተለመደውን ባህላዊ አመጋገብ ከመምረጥ ወደ ኋላ አለማለታቸው ነው።

የጤናና ስነ ምግብ ባለሙያዎች ከረጅም ፆም በኋላ በ24 ሰዓታት ውስጥ ከሁሉም የምግብ ክፍሎች ማለትም ከጥራጥሬ፣ ከአትክልትና ፍራፍሬ ከእንስሳት ተዋጽኦ የተሰባጠረ ጤናማ አመጋገብን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው በማለት ይመክራሉ። በባሕላዊ መንገድ የሚዘጋጁ እንደተልባና ሱፍ ምግቦችን ቀድሞ በመመገብ ከአፍ ጀምሮ እስከ ጨጓራ ያለውን የሥርዓተ ልመት አካሎች ወደ መደበኛው ሥራቸው እንዲመለሱ ማድረግ ሌላኛው ተገቢ መፍትሔ ነው። የምግብ መጠንን በመቀነስና የአልኮል መጠጦችን አብዝቶ ባለመጠቀም በበዓል ወቅት የሚከሰቱ ሕመሞችን ማስወገድ እንደሚቻልም ይመክራሉና እናስተውል።

# ዓለም አቀፍ

## የሱዳንን ግጭት ለማስቆም ዲፕሎማሲያዊ ጥረቶች እየተደረጉ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

<u>**አዲስ አበባ፡-**</u> አንድ ሳምንት ሊሆን የተቃረበውን የሱዳን ግጭት በአስቸኳይ ለማስቆም ዓለም አቀፍ ዲፕሎማሲያዊ ጥረቶች ተጠናክረው ቀጥለዋል።

ባለፉት ቀናት የአገሪቱ መደበኛ ጦር ከፈጥኖ ደራሽ ልዩ ኃይሉ ጋር ሲዋጋ የቆየ ሲሆን በግጭቱ ቢያንስ 400 ሰላማዊ ሰዎች ተገድለዋል። በሺዎች የሚቆጠሩ የተጎዱ ሲሆን ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ደግሞ መኖሪያቸውን ጥለው ተሰደዋል።

የተባበሩት መንግሥታት፣ አሜሪካ፣ የመካከለኛው ምሥራቅ እና ጎረቤት አገራት ኢድ አል-ፈጥርን ምክንያት በማድረግ ለሦስት ቀናት የሚቆይ የተኩስ አቁም ስምምነት እንዲደረግ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ።

ፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ ለሰብዓዊነት ተግባር ለ72 ሰዓታት ተኩስ ለማቆም ተስማምቻለሁ ብሏል። ተኩስ አቁሙ ተፈጻሚ የሚሆነው በአገሪቱ ሰዓት አቆጣጠር አርብ ከንጋቱ 12 ሰዓት ጀምሮ ይሆናል ብሏል።

ነገር ግን ትናንት የወጡ መረጃዎች እንዳመለከቱት፤ የተኩስ አቁሙ አሁንም ተግባራዊ አልሆነም። በዚህም በትናንትናው እለት የሱዳን ዋና ከተማ የኢድ አልፈጥር በዓል ላይ ከሚታየው የደስታ ስሜት በተቃራኒ የሙት ከተማ እንደሚመስሉ ተናግረዋል። የዓይን እማኞች በካርቱም የቦምብ ጥይቶች መቀጠሉን ተናግረዋል።

የዓይን እማኞች ለኤኤፍፒ የዜና ወኪል እንደተናገሩት፤ በተቀናቃኞቹ ኃይሎች መካከል ከባድ የጎዳና ላይ ውጊያዎች እየታዩ ነው።

በካርቱም እና መንታ ከተማዋ አምዱርማን የሚኖሩ ሰዎች አሁንም የድንጋጤ እና የቁጣ ስሜት እየተሰማቸው እንደሆነም ለቢቢሲ ተናግረዋል።

ቀደም ሲል የአገሪቱን ጦር የሚመሩት ጀነራል አብደል ፋታህ አል-ቡርሃን ከፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ ጋር የሚደረግ የትኛውንም አይነት ድርድር ውድቅ አድርገዋል።



ከግጭቱ መቀስቀስ በኋላ አብዛኛዎቹ ሴቶች እና ሕጻናት የሆኑ ከ10ሺህ እስከ 20ሺህ የሚገመቱ ሰዎች ከሱዳን ሸሽተው ወደ ቻድ መሰደዳቸውን የተባበሩት መንግሥት ድርጅት ገልጿል።

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን ተዋጊዎች ቢያንስ እስከ እሁድ ድረስ ተኩስ ለማቆም እንዲስማሙ ጠይቀዋል።

ብሊንከን በመግለጫቸው አገራቸው በሱዳን ስላሉ ሰላማዊ ሰዎች፣ የሰብዓዊ ድርጅት ሠራተኞች እንዲሁም አሜሪካውያንን ጭምሮ የዲፕሎማቶች ደኅንነት እጅግ አሳስቧታል ብለዋል።

የሱዳን ጦር በመግለጫው እንዳለው ጀነራል አል-ቡርሃን ከቱርክ፣ ደቡብ ሱዳን እና ከኢትዮጵያ መሪዎች እንዲሁም ከአሜሪካ፣ ሳዑዲ አረቢያ እና የኳታር የውጭ ጉዳይ ሚንስትሮች የስልክ ጥሪ ደርሷቸዋል።

ግጭቱን ተከትሎ በርካቶች መኖሪያቸውን ጥለው ተሰደዋል። የግጭቱ ማዕከል የሆኑት የአገሪቱ ጦር አዛዥ ጀነራል አብደል ፈታህ አል-ቡርሃን እና የፈጥኖ ደራሹ ልዩ ኃይል አዛዥ ጀነራል መሐመድ ሐምዳን ዳጋሎ ናቸው።

ሁለቱም ጀነራሎች በሕዝባዊ ተቃውሞ እአአ 2019 በቀድሞ ፕሬዝዳንት ኦማር አል-በሽር ላይ ፊታቸውን ከማዞራቸው በፊት በፕሬዝዳንቱ ሥር ሲያገለግሉ ነበር።

ከመፈንቅለ መንግሥቱ በኋላ ሁለቱ የጦር ጀነራሎች በሱዳን ተጽዕኖ ፈጣሪ ሆነው ቀጥለዋል። ጀነራሎቹ በሱዳን ሥልጣን ለሲቪል አስተዳደር ለማስተላለፍ ተስማምተናል ይበሉ እንጂ ዳጋሎ የሚመሩት የልዩ ኃይል አባላቱ ወደ አገሪቱ ጦር ስለሚቀላቀሉበት ሁኔታ መስማማት አልቻሉም።

አል-ቡርሃን ወደ 120ሺህ የሚጠጋ ጠንካራ ሠራዊት ያላቸው ሲሆን ዳጋሎ ደግሞ ወደ 150 ሺህ የሚጠጋ ወታደር አላቸው።

አል-ቡርሃን እና ዳጋሎን የሚያጋጫቸው ጦራቸው በአንድ ተዋህዶ ማን ይመራዋል የሚለው ብቻ ሳይሆን አለመግባባቱ የጥቅም ጉዳይም አለበት።

ሱዳን ወደ ውጭ ልካ ብዙ ገንዘብ ከምታገኝባቸው ምርቶች መካከል ወርቅ ቀዳሚው ነው። የዳጋሎ ቤተሰብ ደግሞ በወርቅ ሽያጭ እና በወርቅ ማውጫ ስፍራዎች ላይ እጁ ረዥም ነው።

ወርቅ ገንዝብ ከማስገኘቱም በላይ በሱዳን ፖለቲካ ውስጥ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ አለው። አብዛኛው ወርቅ ወደ ተባበሩት አረብ ኤሜሬቶች የሚሄድ ነው።

ከዚህ ውጭ በአፍሪካ በቆዳ ስፋት ሦስተኛ ደረጃ ላይ በምትገኘው ሱዳን የሚከሰተው አለመረጋጋት ከአገሪቱ አልፎ በቀጣናው ላሉ እና ለመላው ዓለም ስጋት ነው።

በሱዳን ቀጥተኛ ተጽዕኖ እንዲኖራቸው ፍላጎት ያላቸው አሜሪካ፣ ሩሲያ እና ሳዑዲ አረቢያ በምሥራቅ አፍሪካዊቷ አገር እየሆነ ያለውን በቅርበት እየተከታተሉ ይገኛሉ ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

ማህበራዊ

# መጋቢ አዕምሮ

# ራስን በፍጥነት መቀየር

አስናቀ ፀጋዬ

ለውጥ በየቀኑ፣ በየሳምንቱ፣ በየወሩ፣ በየዓመቱ አዳዲስ ነገሮችን መፈፀም ነው። ለውጥ ሁሌም ቢሆን ራስን ከሁኔታዎች ጋር አዋዶ ወደፊት መራመድ ነው። ለውጥ ደረጃ በደረጃ በሁለንተናዊ መልኩ ራስን፣ ቤተሰብን፣ ጎረቤትን፣ ህብረተሰብን፣ ማህበረሰብና አገርን መቀየር ነው። ነገር ግን ሁሌም ቢሆን ለውጥ ከራስ ይጀምራል። ራሱን ያለወጠ ቤተሰቡን ሊለውጥ አይችልም። ራሱን ያለወጠ አካባቢውን ሊቀይር አይችልም። ራሱን ያለወጠ ማህበረሰቡን፣ ህብረተሰቡንና አገሩን በተለያየ መልኩ ሊያሻሽል አይችልም።

ምንም እንኳን ለውጥ ሂደት ቢሆንም በዚህ ዓለም ራሱን በፍጥነት መቀየር የማይፈልግ ሰው የለም። ሁሉም ፈጣን ለውጥ ፈላጊ ነው። በተለይ ጤናማ አይምሮ ያለውና ነገን አሻግሮ የሚያይ በህይወቱ ሁለንተናዊ ለውጥ በፍጥነት ማምጣት ይፈልጋል። ህይወት በራሱ የማያቋርጥ ኡደት በመሆኑ ማንም ሰው ከዚህ ኡደት ውጪ ሊሆን አይችልም። ለዛም ነው የሰው ልጅ በዚህ በማያቋርጥ የህይወት ኡደት ውስጥ ሁሌም ቢሆን ራሱን ለፈጣን ለውጥ ዝግጁ የሚያደርገው። ራስን በፍጥነት መቀየር ሲባል ግን ሁሌም ቢሆን መነሻው ውድቀት፣ እጦት፣ ችግር፣ ዝቅ ማለት ....ወዘተረፈ ነው።

ለመሆኑ በህይወታችን ፈጣን ለውጥ እንዴት ማምጣት እንችላለን ? እንዴትስ በፍጥነት መቀየር እንችላለን ? አይታችሁ እንደሆነ ብዙዎቻችን ቶሎ መቀየር እንፈልጋለን። አቋራጭ መንገድ እንፈልጋለን። የማራቶን ሩጫ ማየት የሚፈልግ እኮ የለም። የመቶ ሜትር ርቀት ሩጫ ውድድርን ግን ሁሉም ሰው ያየዋል። ለምን? ቶሎ ፉት ይላታል። ማራቶን ሩጫ እኮ ያደክማል። ኢትዮጵያውያን ራሱ ሲሮጡ አስር ሺ ሜትር ሩጫ ቁጭ ብዬ ላይ ነው እንዴ እንላለን። ለምን? ፈጣን ነገር እንወዳለን። በአጭር ግዜ ሀብታም የሚሆኑበት ስራ ሲባል ጆራችንን ጣል እናደርጋለን። በቀላሉ ትዳር ማግኘት የሚፈልጉ ከሆነ በዚህ ስልክ ቁጥር ይደውሉ ሲባል አሀ ! ትዳር በዚህ መንገድ ይገኛል ለካ ብለን ጆራችንን እንሰጣለን።

ዛሬም ድረስ ሚሊየኖች በአጭሩ ለመክበር ሎተሪ ይቆርጣሉ። ነገር ግን ጥቂቶች ብቻ እጣ ደርሷቸው ይከብራሉ። አያችሁ እንግዴ እኛ ሰዎች በህይወታችን ውስጥ ፈጣን ለውጥ እንፈልጋለን። የአይምሮ ሀኪሞችና የማህበራዊ ሳይንስ አጥኚዎች ግን በፍጥነት ወይም ቶሎ መቀየር የሚፈልግ ሰው አንድ ነገር ያድርግ ይላሉ። ይኸውም ራሱን ይቀይር/ይለውጥ ነው። ስለዚህ አንተ ካልተቀየርክ ትዳርህ አይቀየርም። ኑሮህ አይቀየርም። ስራህና ትምህርትህ አይቀየርም። አንተ ስትቀየር ግን በዙሪያህ ያሉ ሰዎች አንተን ማክበር ይጀምራሉ። ምን አግኝቶ ተለወጠ ይላሉ። ከዛ በኋላ እድሎች ወደህይወትህ ይመጣሉ። ስለዚህ ሰው ሆይ ህይወትህን በፍጥነት መቀየር ትፈልጋለህ ? እንግዲያውስ የሚከተሉትን ስድስት ነጥቦች አስተውል

**1ኛ.መወሰን**

ወዳጄ በህይወትህ ፈጣን ለውጥ ማምጣት ከፈለክ መወሰን አለብህ። መድሀኒቱን ካልዋጥከው መዳን የሚባል ነገር የለም። ስለዚህ መወሰን አለብህ። አየህ አንዳንድ ግዜ ህይወትና እድል እንደባቡር ናቸው ካመለጡህ አታገኛቸውም። ስለዚህ ወስን፤ ቁረጥ። ቁጭ ብለህ አስብ። የሆነ ግዜ ላይ ቆራጥ ሆነህ የወሰንካቸው ውሳኔዎች የሰጡህ ደስታ አለ። የሰጡህ ስሜት አለ። አየህ አሁንም ከወሰንክ በኋላ ህይወትህን ስትቀይር የሚገጥምህን አስብ። ሰዎች መጥተው በጆሮህ ምን እንደሚሉህ አስብ። እንዴት እንደሚያደንቁህ ተመልከት። አንተ እኮ ጀግና ነህ ሲሉህ፤ እኔ አንተን ነው መሆን የምፈልገው ብለው ሲመኙ፤ አንቺ እኮ በጣም ጀግና ነሽ፤ ሲሉሽ አንቺ ራስሽን ስታደንቂ አስቢ፤ ስትለወጪ፤ በህይወትሽ ውስጥ የሚኖርሽን ነገር በአይምሮሽ ሳይው። ምን አይነት የተረጋጋ ህይወት እንደሚኖርሽ ፤ በምን አይነት መንገድ መንፈሳዊ ህይወትሽ፣ የገንዘብ ህይወትሽ፣ የስራ ህይወትሽ፣ ትምህርትሽ እንደሚቀየር አስቢ። ስእሉን በአይምሮሽ ሳይው።

አንተም ስሜቱን እስኪ በህይወትህ አጣጥመው። ምን አይነት እርካታ እንደሚኖርህ፤ ስትለወጥ፣ ህይወትህን ስትቀይር የሚኖርህ ደስታ፣ በቃ ከሰዎች እኮ አላንስም። እኔም ወጥቼ እገባለሁ። ሰርቼ አገኛለሁ። የምፈልገውን እየኖርኩ ነው ስትል አስብ። ይህንን ሁሉ ካሰብክ በኋላ ጥሩ ስሜት ውስጥ ከገባህ ወስን፤ ቁረጥ። ልክ ስትቆርጥ ህይወትህን መቀየር ትችላለህ።

**2ኛ.ወደኋላ የሚጎትትህን ነገር እወቅ**

አንዳንዴ አቅሙና ልምዱ ይኖርሃል። ዝግጁነቱም እንደዛው። እኔ እኮ ለምንም ነገር አላንስም ልትል ትችላለህ። ግን የጎተተህ፤ ያስቀረህ የሆነ እንከን አለ። የሆነ ጉድለት ይኖራል። ያ ጉድለት መዝምዞ ብዙ ነገር ያሳጣሀል። አንድ ሰው ራሱን ሲይዝ ራሴን አመመኝ ይላል። አንገቱን ሲይዝ አንገቴን አመመኝ ይላል። ዝቅ ብሎ ደሞ ልቤን አመመኝ ይላል። ለካ ሰውዬው ምኑንም አይደለም የታመመው። እጁን ነው የታመመው። አየህ አንተም የሆነች ትንሽዬ ጉድለትህ ብዙ ነገርህን እያጠፋችብህ ይሆናል። አንዳንዴ አብረሀቸው የምትውላቸው ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ ህይወትህን እያበላሹት። መበጠስ ያለበት ጓደኝነት ካለ መበጠስ አለበት። ያንተ ጠላት ስልክህ ሊሆን ይችላል። ማህበራዊ ሚዲያ ላይ ተጥደህ መዋልህ ሊሆን ይችላል ካለህበት፣ ከምትደርስበት ያስቀረህ፤ የጎተተህ፤ እንዳትለወጥ ያደረገህ። እንቅልፍ መውደድህ፣ ገንዘብ አጥፊ መሆንህ ይሆናል የጎተተህ። በስራህም ቢዝነስህም እንዳትቀየር ያደረገህ ውሎህም ከሆነ ቀይር። ከሚጠቅሙህ ጋር ዋል። አንድ አይነት ቀለም ያላቸው ወፎች አብረው ይበራሉ እንደሚባለው ራስህን ለመቀየር የሚጎትቱ ነገሮችን በሙሉ በጥሳቸው። ቁጭ ብለህ አስበው። ምንድን ነው ወደኋላ ያስቀረኝ በል። ያኔ ራስህን መቀየር ትጀምራለህ። ያውም በፍጥነት።

**3ኛ. በህይወትህ መስለህ ሳይሆን ሆነህ ተውን**

በህይወትህ ውስጥ አንዳንድ ግዜ መስለህ ሳይሆን ሆነህ የምትተውንባቸው ግዚያቶች አሉ። ለምሳሌ አንተ የምትፈልገውን ስኬት ቀድሞ ያሳካ ሰው አለ። አንተ መኖር የምትፈልግበት ቤት ውስጥ አሁን እየኖረ ያለ ሰው አለ። አንተ ህልሜ ነው የምትለውን ስራ አሁን እየሰራ ያለ ሰው አለ። አንተ ህልሜ ነው የምትለውን ገንዘብ እያንቀሳቀሰ ያለ ሰው አለ። አንተ ፍላጎቴ ነው የምትለውን መኪና እየነዳ ያለ ሰው አለ። ያ ሰው ምን አድርጎ ነው እዛ የደረሰው ? እሱን ሰውዬ ሁነው። በቃ ኮርጀው። እንዴት ነው የሚያስበው ? እንዴት ነው የሚወስነው ? እንዴት ነው የሚለብሰው ? እንዴት ነው የሚራመደው? እንዴት ነው ቀኑን፣ ግዜውን የሚያሳልፈው? እንዴትስ ነው ገንዘቡን የሚያጠፋው የሚለውን ለማወቅ እሱን ሰው መሆን አለብህ። የምትፈልገውን አታገኝም። የሆንከውን ነው የምታገኘው። መምሰል አለብህ። በህይወትህ መተወን መቻል አለብህ።

በዓለም ላይ አንድ የተከበረ ሼፍ ፒዛ እንዴት እንደሚበስል መረጃ ቢሰጥህና አንተ ቤትህ ገብተህ እያንዳንዱን ነገር አሟልተህ ፒዛውን ብትሰራ ከሼፉ እኩል አሪፍ ፒዛ አልሰራህም? ሰርተሀል። አሁንም ቢሆን በህይወትህ ባለሞያ መሆን ከፈለክ አንተን የቀደመህ ሰው ሊኖር ይችላልና እርሱን ምሰለው። ራሱን ሁነው። ህይወትህን ትቀይራለህ። ከየት አግኝቼ ልንኮርጅ ? ያንን ሰው ከየት ላገኘው እችላለሁ ? ልትል ትችላለህ። ዝምብለህ ፊልም እይ። መፅሀፍ አንብብ። ስለምታደንቀው ሰው የተሰራ ዘጋቢ ፊልም ተመልከት። የእርሱን ቃለምልልስ ተመልከት። በምን አይነት መልኩ በህይወቱ ውሳኔዎችን እንዳሳለፈ፣ ምን እንደሚያስደስተው፣ ምን ሰርቶ እዛ እንደደረሰ እይ፤ ኮርጅ። ለመኮረጅ ቀላል ምክንያት ነው ካንተ የሚጠበቀው። እርሱም ራስህን ማዘጋጀት ነው።

**4ኛ. እምነትህ ላይ ጠንክር**

በፍጥነት ህይወትህን መቀየር ከፈለክ እምነትህ ላይ ጠንክር። ዓለምን የቀየሩ ሰዎች በሙሉ አማኞች ናቸው። በሁሉም ዘርፍ ስኬታማ የሆኑ ሰዎች አማኞች ናቸው። አንተም አማኝ መሆን አለብህ። ካላመንክማ እንዴት ትቀየራለህ። እንደምትለወጥ እርግጠኛ መሆን አለብህ። እኔ እርግጠኛ ነኝ እለወጣለሁ፤ አምናለሁ እንድትል አማኝ መሆን አለብህ። እምነት ደግሞ የሚገርምህ እንደቫይረስ ነው ይጋባል። የሚሰርቅ ነገር ነው። ታዲያ ምን ይሻልሃል ? መፅሀፍ ቅዱስ ወይም ቁርዐን በየቀኑ አንብብ። ክርስቲያን ከሆንክ ቢያንስ አንድ ምዕራፍ ከመፅሐፍ ቅዱስ ሙስሊም ከሆንክ ደግሞ አንድ ሱራ ከቁርዐን አንብብ። ለምን መሰለህ ባነበብክ ቁጥር በስነልቦናህ በመፅሀፍ ቅዱስ አልያም ደግሞ በቁርዐን ውስጥ ካሉት ጋር ትውላለህ። በዚህም ለካ መለውጥ ይቻላል ትላለህ። በህይወትህም እርግጠኛ ትሆናለህ። አማኝ ከሆንክ በፍጥነት ራስህን ትቀይራለህ። እምነትህ ጠንካራ ከሆነ ህይወት በጣም ቀላል ትሆናለች።

**5ኛ.ስራሴ ያለሁት እኔ ነኝ በል**

አንተ ካልተቀየርክ ማንም አይቀየርም። ሰበበኛውን ቅበረው። ፈጣን ለውጥ አይደል የምትፈልገው ? ሰበብ የሚሰጥህን ውስጥህ ያለውን መጥፎ ድምፅ አቁመው። አንተ እኮ ደሀ ሀገር ነው የተወለድከው። እንዴት ራስህን ትቀይራለህ። የሚረዳህ የለም። እውቀት የለህም። ገንዘብም የለህም። ልምድም ቢሆን የለህም። እንዴት አድርገህ ራስህን ትቀይራለህ የሚለውን ሰበበኛ እንዳታዳምጠው። ድፈረው፤ በቃ እኔ እቀይራለሁ። ለራሴ ያለሁት እኔ ነኝ። ማንም አይደለም ህይወቴን የሚቀይረው። ለራሴ እራሴ ኃላፊነት እወስዳለሁ። መቶ ከመቶ ራሴ ነው የምቀይረው። ለራሴ ያለሁት እኔ ነኝ። ማለት ጀምር። ትጠነክራለህ። ህይወትህ መቀየር ይጀምራል።

አይተህ ከሆነ ስትጠነክር ሁሉም ሰው ይፈልግሀል። እሱ እኮ ጎበዝ ነው። ጠንካራ ነው። ዓላማ አለው። ይሰራል። ይበረታል ይሉሀል። መንግስት እንኳን የሚያበድረው ለሚሰሩ ሰዎች አይደል። ዝምብሎ ቢያበድርህማ ትጠፋለህ እኮ። የት ያምንሀል። የት የሰራኸውን፤ ምን ሰርተህ ታውቃለህ ከዚህ በፊት ይልሀል። ስለዚህ አያበድርህም። የምታሲዘው ነገር ያስፈልግሃል። አየህ ስትጠነክር ማንም ካንተ ጋር ያሽቃብጣል። ለራሴ ያለሁት እኔ ነኝ በል። ህይወትህን በፍጥነት ትቀይራለህ።

**6ኛ. ምክንያታዊ ሁን**

ለምሳሌ አንድ ሰው ደውሎልህ መቶ ሺ ብር እንድትሰጠኝ ፈልጌ ነው። በዚህ የባንክ አካውንት አስገባልኝ ቢልህ ይሄ ልጅ እንዴት ደልቶታል ይቀልዳል እንዴ ትላለህ። ግን ይወልህ አሁኑኑ መቶ ሺ ብር ካላስገባህ ቤተሰቦችህን አሁኑኑ ነው እዚሁ የምረሽናቸው ብትባል ትደነግጣለህ። መቶ ሺ ብሩን ከየትም ብለህ ታመጣዋለህ። ሌላ ግዜ መቶ ሺ ብር ስትባል የምትደነግጠው ሰው ቤተሰቦችህ ሊያልቁ ነው ስትባል ከየትም ታመጣዋለህ። አየህ በህይወትህ ውስጥ ምክንያት ነው ያጣኸው እንጂ አቅም አንሶህ አይደለም። ጉልበት አጥተህ አይደለም። ስለዚህ ምክንያት ያስፈልግሃል።

በነገራችን ላይ ህልም ሲኖርህ፤ ዓላማ ሲኖርህ አንተ ትቀየራለህ። ያንን ነገር ለማሳካት ስትል ትሰለፋለህ፤ ትለወጣለህ ሙሉ አቅምህን አንጠፍጥፈህ ትጠቀማለህ። ስለዚህ ምክንያት ያስፈልግሃል ማለት ነው። ፈጣን ለውጥ ማለት ነው። አንዳንድ ሰዎች ምን ይላሉ እኔ እኮ የምሰራው እንዲሁ ስሜ ሲጠራ እንዳይብጠለጠል ነው። ቢያንስ ባለሀብት እገሌ ብባል ጥሩ ነው ይላሉ። በጣም ጥሩ ነው። ዶክተር እከሌ ለመባል ነው የምማረው የሚልም ሰው አለ። ይህም በጣም ጥሩ ነው። ምክንያትህ ብቻ ምንም ይሁን የኔ ፍላጎት ትልቁ አስመጪና ላኪ መሆን ነው፤ ትልቁን ሆስፒታል፣ ትልቁን ሆቴል፣ ትልቁን ፀጉር ቤት መገንባት ነው ልትል ትችላለህ። ምክንያትህ ከሆነ ይህ በጣም ጥሩ ነው። እንድትሮጥ የሚያደርግህ ከሆነ ህይወትህን ትቀይራለህ።

አንድ ሰው ባንክ ቤት የሚቆጥሩባትን ማሽን ገዝቶ እቤቱ ያስቀምጣል። ሁል ግዜ ድምጿን ተረረረ ሲል ይሰማታል። እናም ይህ ማሽን እኮ የሚቆጥረው ገንዘብ ያስፈልገዋል። እርቦታል ይልና ፈጥኖና ወጥሮ ይሰራል። ራሱን ይቀይራል። ገንዘብ ያመጣና በማሽኑ ሲቆጥረው ያድራል። ከዛ ሁሌ ማሽኑን ይሰማዋል፤ ገንዘብ ያስፈልገኛል ይላል ይበረታል። በነገራችን ላይ ምክንያታችን ምንም ቢሆን ችግር የለውም። ነገር ግን ሰው ላይ ምቀኛ ሆነን፤ አሉታዊ አሳቢ ሆነን፣ መጥፎ አስበን ሰዎችን ጠልፈን ጥለን አይሁን ብቻ፤ ትልቁን ፎቅ የምትሰራው በሁለት መንገድ ነው። የመጀመሪያው ያሉትን ፎቆች ሁሉ ትደመስስና ያንተን ጂ ፕላስ ስሪ ረጅሙ ፎቅ ታስብላለህ። ሁለተኛው መንገድ ደግሞ በራስህ ጠንክረህ ረጅሙን ፎቅ ትሰራለህ። አየህ ምክንያት ሲኖርህ የኔ ረጅሙ ፎቅ ነው፤ እኔ ትልቅ ቦታ እደርሳለሁ ካልክ የሌላው አያገባህም። ለራስህ ትበረታለህ፤ ትጠነክራለህ። ምክንያት ያስፈልግሃል ወዳጄ።

ብዙውን ግዜ ለውጥ ሲጀምር በጣም ፈጣን ሊሆን ይችላል። አይተህ ከሆነ ስፖርት ስትጀምር እንዴት ጥሩ ስሜት ተሰማኝ ልትል ትችላለህ። አስራ አንድ ሰዓት በጥዋት የተነሳህ ሰሞን በጣም ደስ ይላል እኮ አንተ ትላለህ። ስትደጋግመው ግን ያ ስሜት ስለሚደጋገም ብዙም አታስተውሉም። ለውጡ አይታይህም። እናም ወዳጄ በፍጥነት ራስህን መቀየር ከፈለክ ምክንያታዊ ሁን።

> ምንም እንኳን ለውጥ ሂደት ቢሆንም በዚህ ዓለም ራሱን በፍጥነት መቀየር የማይፈልግ ሰው የለም። ሁሉም ፈጣን ለውጥ ፈላጊ ነው። በተለይ ጤናማ አይምሮ ያለውና ነገን አሻግሮ የሚያይ በህይወቱ ሁለንተናዊ ለውጥ በፍጥነት ማምጣት ይፈልጋል። ህይወት በራሱ የማያቋርጥ ኡደት በመሆኑ ማንም ሰው ከዚህ ኡደት ውጪ ሊሆን አይችልም

## ከቅዱስ አማኑኤል የአእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# አማኑኤል የአዕምሮ ሰፔሻላይዝድ ሆስፒታል የሚሰጣቸው አገልግሎቶች

የድንገተኛ የአዕምሮ ህክምና፤ የተመላላሽ የአእምሮ ህክምና፤ የአስተኝቶ የአዕምሮ ህክምና፤ የሱስ ህክምና በተመላላሽ እና በአስተኝቶ፤ የተሀድሶ ህክምና፤ የህፃናት የአዕምሮ ህክምና፤ የስነ ልቦና ህክምና (psychotherapy) የማህበራዊ አገልግሎት፤ የተመላላሽ ክፍል የውስጥ ደዌ ህክምና፤ የኤች አይ ቪ የምርመራና የጸረ-ኤች አይ ቪ ህክምና አገልግሎት፤ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት፤ የኒውሮ ሳይካትሪ ህክምና፤ ከህግ ጋር የተያያዘ የአዕምሮ ህክምና ።

የፋርማሲ አገልግሎት በድንገተኛ ፋርማሲ፤ በተመላላሽ ፋርማሲ፤ በተኝቶ ህክምና ፋርማሲ ማህበረሰብ አቀፍ ፋርማሲ፤ የክሊኒካል ፋርማሲ፤ የመድሃኒት መረጃ አገልግሎት የመድሃኒት ቅመማ፤ የላብራቶሪ አገልግሎት የድንገተኛ ላቦራቶሪ፤ አጠቃላይ ላቦራቶሪ ፤ የጭንቅላት ምርመራ አገልግሎት ይሰጣል። ስለ አዕምሮ ህመም ስናነሳ አንዱ የዚህ ችግር አካል የሆነው የሚጥል በሽታ (ኢፒ ሊ ፕሲ) ሲሆን እንደ ህመሙ ባህሪ በአይነት የተለያዩ ናቸው። ብዙ ጊዜ ህመምተኞች ወደ ህክምና መጥተው ህመማቸውንና የሚሰማቸውን ስሜት እያንዳንዱን ነገር ለህክምና ባለሙያዎች በበቂ ሁኔታ ለመግለፅ ሲቸገሩ ይስተዋላል በተለይም ከአዕምሮ ጋር ተያያዥ ለሆኑ ህመሞች። በመሆኑም የህክምና ባለሙያዎቹ የህመሙ ምልክቶችን ከበሽተኛው ተገንዝበው ተገቢውን ህክምና ለመስጠት እንዲረዳቸው የሚጥል በሽታ ያለባቸው ታካሚዎችን የአዕምሮ ምርመራ ወይም ኤሌክትሮኢንሴፋሎግራፊ መሳሪያ በመጠቀም ሙሉ የጭንቅላት ምርመራ ያደርጋሉ።

ይህ በእንግለዚኛው EEG (Electro encephalo graphy) የተባለ የጭንቅላት መመርመሪያ መሳሪያ የነርቭ



ችግር፤ የመንቀጥቀጥ፤ የጭንቅላት እጢ፤ ሌላ የጭንቅላት ጉዳት፤ በዘር የተላለፈ የሚጥል በሽታና ተመሳሰይ ምልክቶች ካሉ መሳሪያው የእያንዳንዱን መረጃ ያሳያል። ህክምናው ሲካሄድ ማሽኑ ከጭንቅላቱ ላይ የተገጠመለት በሽተኛ ምንም አይነት እንቅስቃሴ ማድረግ የሌለበትና ታካሚውን ምንም አይነት ድምፅ ሊረብሸው በማይችል ሁኔታ የሚከናወንና አልፎ አልፎም እንደ በሽተኛው እና ህመሙ ባህሪ ፈታኝ የሆነ የህክምና አይነት ነው።

አማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የጭንቅላት ምርመራ (EEG) ህክምና የሚሰጠው እድሜአቸው ከሰባት ዓመት በላይ ለሆኑ ታካሚዎች ሲሆን ባለው የግብዓት ችግር ምክንያት በአሁኑ ጊዜ አገልግሎቱን ለህፃናት እየሰጠ አይደለም። ይህ ህክምና የሚሰጠው ንፅህናው በተጠበቀ ወይም ፀጉሩ በተላጨ የታካሚው ጭንቅላት ላይ 19 የተለያዩ ኤሌክትሮ ኖዶችን (በመለጠፍ) በማስቀመጥ ሲሆን እነዚህ ኤሌክትሮ ኖዶች በጭንቅላት የተለያዩ ክፍሎች ማለትም በጭንቅላት የፊት ክፍል (frontal) በመካከለኛው የጭንቅላት ክፍል (centeral) ፤በኋለኛው የጭንቅላት ክፍል (septal) እና በጭንቅላት የጎን ክፍሎች (temporal) ላይ ይቀመጣሉ። እነዚህ ኤሌክትሮ ኖዶች ለህክምና ባለሙያው ችግሩ የተፈጠረበት የጭንቅላት ክፍል በኮምፒውተሩ ላይ ያመላክታሉ ማለት ነው።

ከዚህም በተጨማሪ ከሚሰጡት መረጃ በመነሳት ታካሚው የትኛው አይነት የአንጎል ክፍል እንደተጎዳ እና የጉዳቱ አይነት ማለትም የአንጎል ዕጢ መኖር፤ የነርቭ መጎዳት እና ሌሎችንም እንዳሉበት የህክምና ባለሙያው ተረድቶ ተገቢውን ህክምናና ክትትል እንዲያደርግ ያደርገዋል። ይህ ህክምና እንደ EEG ሁሉ የጭንቅላት ህክምና የሚሰጥበት ሲሆን በንዝረት አማካኝነት የሚከናወን ህክምና ነው። የመስኩ ባለሙያዎች እንደሚያስረዱት የህክምናው አጀማመር በድንገት ቢሆንም የአዕምሮ ህመም ያለባቸው ሰዎች ላይ ውጤቱ በተደጋጋሚ ሲታይ ሰፋፊ የሳይንስ ምርምሮች ተከትለው እዚህ ደረጃ ላይ የደረሰ የህክምና አይነት ሲሆን ውጤታማነቱን በታካሚዎች ላይ በተግባር ማየት ተችሏል።

በሌላ በኩል ደግሞ የኤሌክትሪክ ንዝረት ህክምና (ECT) የሚሰጠው በታካሚው አዕምሮ ላይ ብቻ ንዝረት እንዲፈጠር በማድረግ ሲሆን መናገር፤ መብላትና መንቀሳቀስ ለማይችሉ እና የአዕምሮ ህመም መድኃኒት ተሰጥቷቸው መዳን ላልቻሉ ታማሚዎች የሚሰጥ የህክምና አይነት ነው።

የኤሌክትሪክ ንዝረት ህክምና (ECT) በዚህ ችግር ውስጥ ለሚገኙ ሰዎች ወይም የአዕምሮ ህክምና መድሃኒቶችን ወስደው ለውጥ ላላማጡ (antipsychotic drug) ታካሚዎች እና አንድ ቦታ ላይ ሳይንቀሳቀሱ ስሜት አልባ ሆነው ለረጅም ጊዜ ለሚቆዩ (catatonia) ህመምተኞች የሚሰጥ ህክምና ሲሆን ይህንን ህክምና አንድ ሰው ወይም ታካሚ ቢበዛ 12 ጊዜ ብቻ እንዲወስድ የሚፈቅድ ቢሆንም በዚህ ችግር ውስጥ የሚገኙ ህመምተኞች ህክምናውን ሁለት ወይም ሶስት ጊዜ እንደወሰዱ አስደናቂ ለውጦችን ያሳያሉ። በተጨማሪም ይህ ህክምና ከፍተኛ የማዳን አቅም ያለው ሲሆን ከዚህ ጎን ጭንቀት ወይም ድባቴ ለሚባለው የአዕምሮ ህመም በጣም ውጤታማ የሆነ ህክምና ነው። እንደማንኛውም ህክምና የኤሌክትሪክ ንዝረት ህክምና (ECT) የራሱ የጎንዮሽ ጉዳቶችም አሉት። የራስ ምታት፤ ለአጭር ጊዜ የሚቆይ የመርሳት ችግር በታካሚው ላይ የሚስተዋሉ የጎንዮሽ ጉዳቶች ሲሆኑ ይህንን ህክምና የሚወስዱ ሰዎች ሙሉ የጤና ምርመራ ተደርጎላቸው ህክምናው ቢሰጣቸው ጉዳት የማያስከትል ሌላ አካላዊ እንከን ወይም ህመም እንደሌለባቸው በምርመራ ከተረጋገጠ በኋላ ነው።


Ahadu Bank

## እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው በሰላም አደረስዎ!

**ውድ የአሐዱ ቤተሰብ፤**

አሐዱ ባንክ አ.ማ በምስረታው ወቅት የተፈረሙ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው አክሲዮኖችን ለመሸጥ ይፈልጋል። በመሆኑም እነዚህን አክሲዮኖች በሀገሪቱ የንግድ ሕግ እና በባንኩ አሠራር መሠረት መግዛት የምትፈልጉ እንዲሁም የባንኩ ባለአክሲዮን መሆን ለምትፈልጉ ሁሉ በባንኩ ዋና በር ለንግድ ሕንጻ 3ተኛ ፎቅ አክሲዮን ሽያጭ ክፍል በመቅረብ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ግዢ መፈጸም የምትችሉ መሆኑን እናሳውቃለን።

ahadubank.com

አሐዱ፡ባንክ
ከብዙዎች ለብዙዎች!

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## በዘመናዊነቱ ሞዴል ተደርጎ የሚወሰደው የየካ-2 መኪና ማቆሚያ ፕሮጀክት

መሳኩ ኤርሴ



የየካ 2 መኪና ማቆሚያ ፕሮጀክት ከ920 እስከ አንድ ሺህ ተሽከርካሪዎችን ማቆም እንዲያስችል ተደርጎ እየተገነባ ይገኛል

በአዲስ አበባ ከተማ የተሽከርካሪ ብዛት እየጨመረ ይገኛል። ከተማዋ ይህን የተሽከርካሪ ብዛት ታሳቢ ያደረገ የመኪና ማቆሚያ ስፍራ ሳይኖራት ዓመታትን አሳልፋለች። የመኪና ማቆሚያ ቦታ በበቂ ሁኔታ አለመኖር በመኪና ባለቤቶች፣ በመኪናዎች እንዲሁም በከተማዋ ነዋሪዎች የእለተ እለት እንቅስቃሴ ላይ ተግዳሮት ሲፈጥር ቆይቷል።

ይህን ችግር ለመፍታት ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ የተለያዩ ጥረቶች እየተደረጉ ይገኛሉ። ህንጻ ገንቢዎች በምድር ቤታቸው የመኪና ማቆሚያን ታሳቢ ያደረገ ግንባታ እንዲያካሂዱ እየተደረገ ነው። ከተማዋ ዘመናዊ የመኪና ማቆሚያዎችን ወደ መገንባት መግባቷም ይታወቃል።

ቀደም ሲል በመገናኛ፣ በመርካቶ አንዋር መስኪድ አካባቢ የመኪና ማቆሚያዎችን መገንባታቸው ይታወሳል። ከአገራዊ ለውጡ ወዲህ ደግሞ ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት በመስቀል አደባባይና በአንድነት ፓርክ አካባቢ እጅግ ዘመናዊ የሚባሉ የመኪና ማቆሚያዎች በምድር ውስጥ ተገንብተዋል። ከፍተኛ ወጪ በመመደብ ነው ግንባታው የተካሄደው። የመስቀል አደባባይ የመኪና ማቆሚያ አንድ ሺህ 400 መኪናዎችን፣ የአንድነት ፓርክ መኪና ማቆሚያ ደግሞ አንድ ሺህ መኪናዎችን ማቆም ያስችላሉ።

ሁለቱ ፕሮጀክቶች የከተማዋን የመኪና ማቆሚያ ችግር የማስታገስ አቅም ቢኖራቸውም፣ በከተማዋ ካለው የመኪና ማቆሚያ ቦታ እጥረት አንጻር ችግሩን ሙሉ በሙሉ የሚቀርፉ ግን አይደሉም። በከተማዋ የትራፊክ እንቅስቃሴ ከፍተኛ በሆነባቸው የተለያዩ አካባቢዎች ተመሳሳይ የመኪና ማቆሚያዎችን መገንባት የግድ ነው።

የከተማዋ አስተዳደርም ይህን ታሳቢ ያደረገ የመኪና ማቆሚያ ግንባታ በሾላ ገበያ አካባቢ እያካሄደ ነው። በከተማዋ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ፅህፈት ቤት የሚካሄደው የዚህ የየካ -2 የመኪና ማቆሚያ ፕሮጀክት ተቆጣጣሪ መሃንዲስ ተወካይ መሃንዲስ ኢንጂነር ደስታ ግደይ እንደተናገሩት፤ ፕሮጀክቱ አረንጓዴ ስፍራን ጨምሮ በሰባት ሺህ 247 ስኩዌር ሜትር ስፋት ላይ እየተገነባ ይገኛል።

የመኪና ማቆሚያው ከመሬት በታች እና ከመሬት በላይ እየተሰሩ ባሉ ወለሎች ከ920 እስከ አንድ ሺህ ተሽከርካሪዎችን እና የተወሰኑ የንግድ ሱቆችን ማካተት እንዲችል ተደርጎ እየተገነባ ሲሆን፤ የግንባታ አፈጻጸሙም እስከ ሚያዚያ 6 ቀን 2015 ዓ.ም 43 በመቶ ደርሷል።

የመኪና ማቆሚያውን በፊት የአዲስ አበባ የኮንስትራክሽን ቢሮ በባለቤትነት ሲያስገነባ ነበረ፤ ፕሮጀክቱ ባለፈው ዓመት ግንቦት ወር ወደ ሜጋ ፕሮጀክቶች ተዘዋውሯል። ፕሮጀክቱ ወደ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ጽህፈት ቤት ከመዘዋወሩ በፊት ግንባታው በተያዘለት የጊዜ ገደብ እንዳልተከናወነ የሚያስታውሱት ኢንጂነር ደስታ፤ በተለይም ግንባታው በሚካሄድበት ቦታ የነበሩ ሰዎችን ለማስነሳት ጊዜ መውሰዱን ይናገራሉ። በመሃል በተለያዩ ምክንያቶች ግንባታው ተቋርጦም እንደነበርም ያስታውሳሉ።

በፕሮጀክቱ ላይ ማሻሻያ መደረግ ስለነበረበትም በ2022 ግንቦት ወር ወደ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ጽህፈት ቤት መጥቷል ነው የሚሉት። ፕሮጀክቱ ከቢሮው ወደ ጽህፈት ቤቱ እስኪዘዋወር በአምስት ዓመት ውስጥ የግንባታ አፈጻጸሙ 22 በመቶ እንደነበር አንስተዋል። ወደ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ጽህፈት ቤት ሲዘዋወር በ24 ወራት ወይም በሁለት ዓመት ለማጠናቀቅ ታቅዶ መሆኑንም ተናግረዋል።

እንደ ኢንጅነር ደስታ ማብራሪያ፤ የፕሮጀክቱ ግንባታ ከዓመታት በፊት ሲጀመር በግማሽ ቢሊየን ለማጠናቀቅ ታቅዶ የነበረ ሲሆን፤ ግንባታው ተቋርጦ ወደ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ጽህፈት ቤት ተላልፎ ግንባታው ዳግም ሲጀመር የግንባታው ወጪ ወደ 1 ነጥብ 19 ቢሊየን ከፍ ብሏል።

የአገሪቱና የአፍሪካ መዲና የሆነችውን አዲስ አበባን ለስሟ በሚመጥን መልኩ ውብ ለማድረግ የየካ- 2 መኪና ማቆሚያን የመሳሰሉ ፕሮጀክቶች ፋይዳቸው ከፍ ያለ ነው የሚሉት ኢንጂነር ግደይ፤ የፕሮጀክቱ ግንባታም ይህንኑ ትልም ለማሳካት በሚረዳ አኳኋን እየተከናወነ መሆኑን ጠቁመዋል።

ሾላ ገበያ አካባቢ የመኪና ማቆሚያ ባለመኖሩ መኪናዎችን በመንገዱ ግራና ቀኝ ማቆም የተለመደ መሆኑን የሚናገሩት ኢንጂነሩ፤ በዚህም ምክንያት መንገዱ በከፍተኛ ሁኔታ እየተጨናነቀ መሆኑን ተናግረዋል። ይህ የመኪና ማቆሚያ ለከተማዋ ውበት ከመጨመሩ ባሻገር በሾላ ገበያ አካባቢ ያለውን የመኪና ማቆሚያ ቦታ እጥረት በመቅረፍ የትራፊክ ፍሰትን ያሳልጣል ብለዋል።

በከተማ አስተዳደሩ በመገንባት ላይ ከሚገኙት ትላልቅ ፕሮጀክቶች መካከል አንዱ የሆነው ይህ ፕሮጀክት የተወሰኑ የመኪና ማጠቢያዎችንም ያካተተ የመኪና ማቆሚያ ህንጻ መሆኑን የጠቆሙት ኢንጂነር ደስታ፤ መኪና ማቆሚያው የራሱ ዘመናዊ የጥበቃ ካሜራዎች የሚገጠሙለት እንደመሆኑ የመኪና ባለቤቶችን ስጋት የሚያስወግድ ምቹና አስተማማኝ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ነው ይላሉ።

የመኪና ማቆሚያው በአገራችን እምብዛም ያልተለመዱ እና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተለመዱ የመጡ ቴክኖሎጂዎች ተግባራዊ የሚደረግበት ሲሆን፣ ከእነዚህ ቴክኖሎጂዎች መካከል መኪናዎችን ወደላይና ወደታች የሚያንቀሳቅሱ አሳንሰሮች እንደሚገጠሙለት አስታውቀዋል። አሳንሰሮቹ በዋናነት በመኪና ማቆሚያ ለመጠቀም ችግር ሊያጋጥማቸው የሚችሉ ተሽከርካሪዎችንም ለማንቀሳቀስ ያስችላሉ ተብሏል።

የየካ 2 መኪና ማቆሚያን ጨምሮ አብዛኞቹ የመኪና ማቆሚያዎች ግንባታ በቻይና ኩባንያዎች መሰራታቸውንና በመሰራት ላይ መሆናቸውን የጠቆሙት ኢንጂነር ደስታ፤ በርካታ ኢትዮጵያውያን ዜጎች በግንባታው ላይ ተቀጥረው በመስራት ላይ ይገኛሉ ብለዋል። በፕሮጀክቱ ግንባታ ላይ እየተሳተፉ ያሉ ዜጎች ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች ጥቅም ላይ እየዋሉ ባሉ ቴክኖሎጂዎች ላይ ተሳታፊ መሆናቸው የቴክኖሎጂ ሽግግር እውን ለማድረግ እድል ይፈራል ብለዋል። በቀጣይ የአገር ውስጥ ኩባንያዎች እነዚህን ቴክኖሎጂዎች በመጠቀም የመኪና ማቆሚያዎችን ይገነባሉ የሚል እምነት እንዳላቸውም ጠቁመዋል።

አጠቃላይ ባለድርሻ አካላት ባደረጉት የጋራ ርብርብ የፕሮጀክቱ ግንባታ ደግሞ ነፍስ እንዲዘራ ማስቻሉን የጠቆሙት ኢንጂነር ደስታ፣ ከከንቲባዋ ጀምሮ እስከ ወረዳ አመራር ባሉ የመንግስት የስራ ኃላፊዎች የሚደረገው ክትትል እና ድጋፍ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ብለዋል።

የፕሮጀክቱ ተቆጣጣሪ መሃንዲስ ኢንጂነር ፍስሃ ጌታቸው በበኩላቸው ፕሮጀክቱ ወደ ሜጋ ፕሮጀክቶች ጽህፈት ቤት ከተዘዋወረ ወዲህ ጥሩ መሻሻል እንደታየበት ገልጸው፤ ሆኖም በተያዘለት የጊዜ ገደብ በመሄድ ረገድ የተወሰነ መጓተት እንዳለበት አስታውቀዋል። ፕሮጀክቱ በዚህ ወቅት 50 ነጥብ15 በመቶ ሊጠናቀቅ ይገባ ነበር የሚሉት ኢንጂነር ፍስሃ፤ በሆነ ፐርሰንት ወደኋላ መቅረቱንም ጠቁመዋል።

ኢንጂነር ፍስሃ፣ በፕሮጀክቱ ላይ የተወሰነ መጓተት እንዲከሰት ያደረጉ የተለያዩ ምክንያቶችንም ጠቅሰዋል። የመኪና ማቆሚያው የሚገነባበት ቴክኖሎጂ እንደ አገር በፓርኪንግ ደረጃ የመጀመሪያ መሆኑን ጠቅሰው፣ ፖስትቴንሺንስ በሚባል መሳሪያ እንደሚገነባም ጠቁመዋል። ለፖስቴንሺን የሚውል ገመድ በውጭ ምንዛሪ ከውጭ አገር እንደሚገባም ጠቅሰው፣ ፕሮጀክቱ ለረጅም ጊዜ እንዲጓተት ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ ይህንን ገመድ ከውጭ የማስገባት ሂደት ረጅም ጊዜ በመውሰዱ ነው ብለዋል።

የግብአት እጥረትም አንዱ ችግር እንደነበር ኢንጅነሩ ጠቅሰዋል። የሲሚንቶ እና የብረት እጥረት ሲያጋጥም ነበር። በተለያዩ ጊዜያት በአገሪቱ ውስጥ ሲፈጠሩ የነበሩ የዋጋ መዋዠቆችም በፋይናንስም ሆነ በቁስ አቅርቦት ላይ ጫና አድርሰዋል ሲሉም ገልጸው፣ አሁንም ባለው ሁኔታ የሲሚንቶ አቅርቦት መኖሩ ሳይረጋገጥ ስራ ለመስራት አስቸጋሪ ሆኗል። በአንድ ጊዜ በብዛት መያዝ ስለሚያስፈልግ በብዛት ነው የሚገባው ይላሉ።

እንደ ኢንጅነር ፍስሃ ገለጻ፤ በገበያ ውስጥ ፒፒሲ እና ኦፒሲ የተሰኙ ሁለት የሲሚንቶ አይነቶች የሚገኙ ሲሆን፣ ለመኪና ማቆሚያው ግንባታ ጥቅም ላይ የሚውለው ኦ ፒ ሲ የተሰኘው የሲሚንቶ አይነት ነው። ይህ የሲሚንቶ አይነት በገበያ ውስጥ በቀላሉ የሚገኝ አይደለም። ይህም በፕሮጀክቱ ላይ የራሱን ጫና አሳድሯል። የብረት አቅርቦት ችግር ሌላኛው ነው። የብረት አቅርቦትም የውጭ ምንዛሪ ይፈልጋል። ይህም ሌላኛው ተግዳሮት ነው።

ፕሮጀክቱ በጥራት እንዲሰራ ከፍተኛ ጥንቃቄ እየተደረገ ነው። ከዚህ በፊት በአገራችን ውስጥ ባልተለመደ መልኩ አንዳንድ ለግንባታው የሚውሉ ግብአቶች ፍተሻ የሚካሄደው ከአገር ውጭ በዱባይ ነው። ይህ ሁኔታ ብዙ ጊዜ ይወስዳል፤ በአሁኑ ወቅት ግን ለግንባታው በጣም አስፈላጊ እና ውድ የሚባሉ ቁሶች ተፈትሸው ወደ አገር ውስጥ ገብተዋል። በመሆኑም ለግንባታው ከሚውሉ ቁሳቁስ ጥራት አንጻር የሚያሰጋ ነገር አይኖርም።

ኮንክሪቱን በተመለከተ በየሜትር ኪዩቡና በየጊዜው የጥራት ፍተሻ ይሰራል። በላብራቶሪ እየተጣራ ስራ ላይ እንዲውል በማድረግ የኮንክሪት ጥራት ቁጥጥር ስራ እየተሰራ ነው።

አሁን ባለው ሁኔታ የግንባታው ባለቤት የሆነው የሜጋ ፕሮጀክቶች ጽህፈት ቤትም ሆነ ኮንትራክተሩ ለፕሮጀክቱ ትኩረት ሰጥተው እየተንቀሳቀሱ መሆናቸውንም ኢንጅነር ፍስሃ ጠቅሰው፣ በተለይም ሜጋ ፕሮጀክቶች ጽህፈት ቤት ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን ተናግረዋል። ፕሮጀክት ፅህፈት ቤቱ የሲሚንቶም ሆነ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ቶሎ እንዲፈታ እያደረገ ነው ብለዋል።

የወሰን ማስከበር ችግሮች የሜጋ ፕሮጀክቶች ጽህፈት ቤት ባደረገው ርብርብ ተፈትተዋል። በሌሎች ጉዳዮች ዙሪያም ኮንትራክተሩም የሚያስፈልጉትን ይጠይቃል። ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱም ጥያቄው አስቸኳይ መፍትሄ እንዲያገኝ ያደርጋል ያሉት ኢንጅነር ፍስሃ፣ የኃይል መቆራረጥ፣ የሲሚንቶ እጥረትና የመሳሰሉ ውጫዊ ችግሮች ላይ ጫና ካልፈጠሩ በስተቀር ፕሮጀክቱ አሁን እየተገነባበት ባለው አካሄድ በተያዘለት ጊዜ ሊጠናቀቅ እንደሚችል አስታውቀዋል።

ኢንጅነር ፍስሃ እንደተናገሩት፤ በአሁኑ ወቅት እየጨመረ ካለው የኤሌክትሪክ ቻርጅ የሚጠቀሙ መኪናዎች አንጻር በመኪና ማቆሚያው ውስጥ ቻርጅ ማድረጊያ ቦታ ቢኖር እጅግ ተመራጭ ነው። ይሁን እንጂ ፕሮጀክቱ ሲጀመር የኤሌክትሪክ ቻርጅ የሚጠቀሙ መኪናዎችን ቻርጅ ማድረጊያ ቦታ ታሳቢ ሳይደረግ ግንባታው እየተካሄደ ነው። በፕሮጀክቱ ባለው ክፍት ቦታ ኤሌክትሪክ ቻርጅ ተጠቃሚ መኪናዎች ቻርጅ የማድረጊያ ቦታ ቢገነባ ዘመኑ ከደረሰበት ሁኔታ አንጻር ፋይዳው የጎላ ነው።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የኢትዮጵያንና የሱዳንን ግንኙነት ለማበላሸት የሚደረጉ ሴራዎች አይሳኩም!

የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩትም የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ሕዝቦች ሰፊው ታሪካቸው ከግጭት ትርክቶች ጋር የተያያዘ ነው። በዚህም የከፈሉት ሆነ እየከፈሉት ያለው ዋጋ በቀላሉ የሚሰላ አይደለም።አሁን ላሉበት ችግር እና ድህነት ዋነኛው ምክንያትም ይሄው እውነታ ነው።

ካለው ጂኦ - ፖለቲካል ስትራቴጂ አንጻር የብዙዎችን ትኩረት ከመሳቡ የተነሳ ፤አካባቢውን ለመቆጣጠር በግልጽም ይሁን በስውር የሚደረጉ ጥረቶች ለአካባቢው ሃገራት ሰላም እጦትና አለመረጋጋት እንደ አንድ ምክንያት የሚጠቀስ ነው።

በአብዛኛው በሀገራቱ የውስጥ ጉዳዮች የሚደረጉ ጣልቃ ገብነቶች፤ ግጭቶች ዘላቂ መፍትሄዎች እንዳያገኙ ከማድረግ ባለፈ፤ የሀገራቱ ሕዝቦች የተረጋጋና በሰላም የመኖር ህልማቸውን በማሳጣት በተደጋገሙ የግጭት አዙሪቶች ውስጥ እንዲኳዙ አስገድዷቸዋል።

የአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች ከድንበር መስመሮች ባለፈ ቤተሰብ የሆኑ ፣ የትኞቹንም አለመግባባቶች በሰላም መፍታት የሚያስችሉ የዳበሩ ትውልድ ተሻጋሪ መንፈሳዊ ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ እሴቶች ያሏቸው፤ በዚህም ዘመናትን ተሻግረው ዛሬ ላይ መድረስ የቻሉ ናቸው።

እነዚህ ሕዝቦች በተለያዩ ወቅቶች በተፈጠሩ የሰላም እጦቶች ብዙ ዋጋ ከፍለዋል፤ ከያንዳንዱ ግጭት ማግስት በብዙ የልብ ስብራትና አንገት መድፋት ተጋልጠዋል ። ከሁሉም በላይ እያንዳንዱ ግጭት በልማት ተመንድገው ትልቅ ሀገር የመሆን ራዕያቸውን ተናጥቋቸዋል።

ስለ ሰላም በየወቅቱ ብዙ ዋጋ ለመክፈል ቢገደዱም፤ በከፈሉት ዋጋ ልክ ሰላማቸውን አስጠብቀው፤ወደሚፈልጉት ልማት በመግባት ለራሳቸውም ሆነ ለመጪው ትውልድ የተመቸ አካባቢ ለመፍጠር የሚያደርጉት ጥረት ዛሬም በተግዳሮቶች የታጠረ ሆኗል።

የአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች ትናንት ላይ ከቀደመው የግጭት ትርክት ወጥተው ፤ አዲስ የሰላም ፣ የትብብርና የልማት ትርክት ለመጀመር በሚያስችል አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ ገብተው እንደነበርና ይህም ለሃገራቱ ሕዝቦች ታላቅ የምስራች ሆኖ መበሰሩ የሚታወስ ነው።

በዚህ አዲስ ጅማሬ ውስጥ ሀገራቱ በርግጥም ለራሳቸው ሰላም እንደማያንሱ በተጨባጭ ታይቷል። በሃገራቱ ሕዝቦች የልብ ጽላት ላይ ወንድማማችነትና ከዚህ የሚመነጭ የጋራ ተጠቃሚነት በደማቅ ቀለም የተጻፈ መሆኑም ተመልክቷል።

ይህ እውነተኛ የሆነው የሃገራቱ ሕዝቦች የጋራ መሻት በብዙ ተግዳሮቶች ውስጥ እያለፈ ቢሆንም፤ ለሃገራቱ ሕዝቦች ብሩህ ነገዎች አልፋና ኦሜጋ የመሆኑ እውነታ ዛሬም ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም።ፈተናዎችን በጽናት ተሻግሮ የተስፋቸው ብስራት መሰረት መሆኑ የማይቀር ነው።

ዛሬ ላይ እነዚህ ሕዝቦች በብዙ ተግዳሮቶች እየተፈተኑ ናቸው፤ የጋራ ሰላማቸው ሊያጎናጽፋቸው ከሚችለው የጋራ ተጠቃሚነት አንጻር፤ ራሳቸውን በተሻለ መልኩ ማዘጋጀትና ለጋራ ሰላማቸው የሚሆን ሁለንተናዊ ዝግጁነት መፍጠር ይጠበቅባቸዋል።

ከሁሉም በላይ ትናንትም ሆነ ዛሬ የአካባቢያቸውን ሰላም በብርቱ እየተፈታተነ ያለው ችግር ከእነርሱ አቅም በላይ አለመሆኑን ተረድተው፤ ለችግሮቹ ዘላቂ መፍትሄ በማፈላለግ ለተስፋቸው ተጨባጭ አቅም መሆን ይኖርባቸዋል።

በተለይም አሁን ላይ በሱዳን ያለውን ግጭት በሰላማዊ መንገድ በውይይትና በድርድር የሚቋጭበትን መንገድ በማፈላለግ ከሁሉም በላይ የአካባቢው ሃገራት ሕዝቦች በአስቸጋሪ ወቅት አንዳቸው ለአንዳቸው ተስፋ መሆናቸውን በተግባር ማሳየት ይጠበቅባቸዋል።

በግጭት ውስጥ ያሉ የሱዳን የፖለቲካ ኃይሎች ችግሮቻችውን፣ የሕዝቦቻቸውን የሰላም መሻት ታሳቢ ባደረገ መንገድ ፣ በሰከነ መንፈስ ተወያይተው ወደ ሰላም የሚመጡበትን አስቻይ ሁኔታ በማመቻቸት የመፍትሄው አካል መሆን ይገባቸዋል።

የሱዳን ሕዝብ በዘመናት ውስጥ ባካበታቸው መንፈሳዊ ፣ ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶች ተደግፎ ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት የሰላሙ ባለቤት የመሆን አቅሙም ብቃቱም ፤ጥበቡም ማስተዋሉም ያለው ሕዝብ ነው። ለዚህ ደግሞ ነገዎች ሕያው ምስክር ይሆናሉ።

ኢትዮጵያና ሕዝቦቿም ለሱዳን ወንድምና እህቶቻቸው ያላቸው ክብርና ፍቅር ሁሌም የጸና እንደመሆኑ ሱዳናውያን በራሳቸው መንገድ የራሳቸውን መፍትሄ እንዲያመጡ ለሚያደርጉት ጥረት ከፍተኛ ቦታ ይሰጣሉ። ዘመናትን የተሻገረውን የኢትዮ ሱዳን ወዳጅነት በሀሰት ወሬ ለማበላሸት የሚፈልጉ አካላትም እኩይ ሃሳባቸው መቼም ቢሆን የሚሳካ አይሆንም!


## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## ልዩ ኃይል በአዲስ አደረጃጀት መታቀፉ አስፈላጊም ወቅታዊም ነው!

ሜላት ኢያሱ

በሕገ መንግሥታችን አንቀጽ 52 ፣ ቁጥር 2 (ሠ) ላይ የክልል ሥልጣንና ተግባር በሚለው ስር እንደተቀመጠው ክልሎች የየራሳቸውን የፖሊስ ኃይል በማደራጀት እና በመምራት ሰላምና ጸጥታቸውን የማስጠበቅ ኃላፊነት ተሰጥቷቸዋል። በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 55 ቁጥር 7 ላይ የሕዝብ ተወካዮች ስልጣን እና ተግባር በሚለው ሥር ደግሞ የፌደራል መንግሥት የሀገር እና የሕዝብ መከላከያ ፣ የደህንነትና የፖሊስ ኃይል አደረጃጀትን እንደሚወስን ተቀምጧል። በሕገ-መንግስቱ ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው ክልሎች ከፖሊስ ያለፈ ሌላ የጸጥታ ኃይል እንዲያደራጁ አልተፈቀደላቸውም።

ባለፉት የኢህአዴግ አገዛዝ ዘመን ምንም አይነት ሕገ-መንግስታዊ መሰረት ሳይኖራቸው ተፈጻሚ ከሆኑ አደረጃጀቶች መካከል አንዱ የልዩ ኃይል አደረጃጀት መሆኑ በበርካቶች ይተች ነበር። በተለይም በተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ያሉ ጉምቱ ፖለቲከኞችና አክቲቪስቶች የልዩ ኃይልን አደረጃጀት አጥብቀው ከሚተቹት መካከል ግንባር ቀደሞቹ ነበሩ።

ይህ አደረጃጀት ሕገ-መንግሥታዊ መሰረት የሌለውና በተጎራባች ክልሎች መካከል ያለውን ሰላማዊ መስተጋብር እያበላሸ ያለ በመሆኑ ልዩ ኃይል አስፈላጊ አይደለም በሚል ይሞግቱ ነበር። በእርግጥም ባለፉት ዓመታት ሙግታቸው ትክክል እንደነበር ያረጋገጥንባቸውን በርካታ ሁነቶች ተመልክተናል።

በክልሎች መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶችን በሕገ መንግሥታዊ አግባብ ከመፍታት ይልቅ በልዩ ኃይሎች ጡንቻ የመፍታት ሙከራዎች ይደረጉ እንደነበር የምናስታውሰው ነው። ለአብነትም በሶማሌና በኦሮሚያ ፣ በአማራና በቤንሻንጉል፣ በአፋርና በሶማሌ ክልል ወዘተ ልዩ ኃይሎች መካከል ለተደጋጋሚ ጊዜ ይደረጉ የነበሩ የተኩስ ልውውጦችን መከላከያ ሰራዊት ጣልቃ እየገባ ያረጋጋ እንደነበር የምንረሳው አይደለም።

በወሰን አካባቢ የሚኖሩ የሁለት ክልል ማህበረሰቦች በግጦሽ እና በውሃ ምክንያት በተጋጩ ቁጥር የክልል ልዩ ኃይሎች ችግሩን በየራሳቸው መንገድ ለመፍታት በሚወስዷቸው ርምጃዎች ግጭቶቹ እየተባባሱ በርካታ ዜጎች ዋስትና አጥተው ከአካባቢያቸው መፈናቀላቸውንም አንረሳውም።

በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅ የነበሩ የክልል አመራሮችን በመግደል ስልጣን የመቆጣጠር ሙከራ የተደረገውም በልዩ ኃይሎች ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ከአንድ ክልል ወደ ሌላው ክልል የሚደረጉ ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችና የንግድ ትስስሮች ሳይቀሩ በልዩ ኃይሎች እቀባ ሲደረግባቸው ተመልክተናል።

የሕዝብ ልጅ የሆነው የሀገር መከላከያ ሰራዊት የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ በሕገ-መንግሥቱ የተሰጠውን ስልጣን እና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ልዩ ኃይሎች ሲያደነቃቅፉት እና አንዳንዴም ሲተኩሱበት ስናይ ደግሞ የዚህ ኃይል አደረጃጀት ትክክል አለመሆኑን የበለጠ እንረዳለን።

ዛሬ በመንግሥት እና በሕወሓት መካከል የተደረገው እርቅ እና አሁን ያለንበት የሰላም ድባብ በቅርብ ጊዜ ለተፈጠሩ አገራዊ ቀውሶች መንስኤ የሆኑ ጉዳዮችን እያነሳን እንድንማማርባቸው ላያደርገን ይችላል። ግን አንድ እውነታን ብናነሳ ክፋት ያለው አይመስለኝም።

በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ለፈነዳው የእርስበእርስ ጦርነት እና ኢትዮጵያ ላለፉት ሁለት ዓመታት ላጋጠማት የሠላም ቀውስ እንዲሁም በጦርነቱ ቀጣና ያሉት ሕዝቦቿ ለከፈሉት ዋጋ ወይም ለወደመው ንብረት አንዱ ምክንያት ይሄው የልዩ ኃይል አደረጃጀት እንደነበር መርሳት የለብንም።

ይህን ስንል ግን በሶማሌ ክልል ድንበር ተሻግረው ጥቃት ለመፈፀም የሞከሩ የአልሻባብ ታጣቂዎችን በመደምሰስ እና ባለፉት ሁለት ዓመታት በሰሜኑ የአገራችን ክፍል የተከሰተውን ግጭት እንዲሁም በሸኔ ታጣቂዎች ላይ በሚወሰደው ርምጃ የሁሉም ክልል ልዩ ኃይሎች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ያደረጉት አስተዋጽኦ ዋጋ አልነበረውም ማለታችን አይደለም።

**የኢፌዴሪ መከላከያ ሰራዊት ከረዥም ጊዜ ልምድና ተሞክሮ ያገኘናቸውን መረጃዎች በመቀመር የአደረጃጀት ለውጥ እንደሚያደርግ ይፋ አድርጓል። በዚህም መሰረት የክልል ልዩ ኃይሎች በሀገር መከላከያ ሰራዊት፣ በፌዴራል ፖሊስ እና በክልል ፖሊስ አደረጃጀት ውስጥ እንዲታቀፉ ለማድረግ እንቅስቃሴ መጀመሩን አስታውቋል**

ይሁን እና የልዩ ኃይል አደረጃጀት ለኢትዮጵያና ለሕዝቦቿ ሕልውና ከሚያበረክተው አስተዋጽኦ ይልቅ በሰላማችን ላይ እየፈጠረ ያለው ተጽዕኖ ሚዛን እየደፋ መምጣቱ ለሁላችንም ግልጽ ነው። ስለሆነም ይህ አደረጃጀት መስመር እንዲይዝ መድረጉ ሕዝብንም አገርንም ተጠቃሚ የሚያደርግ እንጂ የሚጎዳ አይደለም።

መከላከያ ሰራዊት በተሰጠው ስልጣን መሰረት የአገሪቱን ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ በተንቀሳቀሰ ቁጥር የሚገዳደረው ሌላ ኃይል መፈጠሩ እንደ አገር አንድ ሆነን እንዳንቆም የሚያደርግ ብቻ ሳይሆን የሚበታትነንም ጭምር መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። ይህ ደግሞ በተግባር የታየ ጉዳይ ነው።

የኢፌዴሪ መከላከያ ሰራዊት ከረዥም ጊዜ ልምድና ተሞክሮ ያገኘናቸውን መረጃዎች በመቀመር የአደረጃጀት ለውጥ እንደሚያደርግ ይፋ አድርጓል። በዚህም መሰረት የክልል ልዩ ኃይሎች በሀገር መከላከያ ሰራዊት፣ በፌዴራል ፖሊስ እና በክልል ፖሊስ አደረጃጀት ውስጥ እንዲታቀፉ ለማድረግ እንቅስቃሴ መጀመሩን አስታውቋል።

በዚህም ብዙኃኑ ሰላም ወዳድ ኢትዮጵያዊ ደስተኛ መሆኑን በማህበራዊ ሚዲያ ሲገልፅ ይታያል። አንዳንዶች እንደውም ውሳኔው በመዘግየቱ ብዙ ዋጋ እንዳስከፈን ጭምር በመጥቀስ በአፋጣኝ ወደ ተግባር እንዲገባ ሃሳብ ይሰጣሉ።

ከዚህ በተቃራኒ ግን ይህ በተፎካካሪ ፓርቲዎችና በአክቲቪስቶች ከበርካታ ዓመታት በፊት ሕገ-መንግሥታዊ መሰረት የለውም ተብሎ ሲተች የነበረው የልዩ ኃይሎች አደረጃጀት ዛሬ ደግሞ በሌላ አደረጃጀት እንዲዋቀር ሲደረግ እነዚሁ ፖለቲከኞች ለምን? ሲሉ እየሰማን ነው።

ፍላጎታቸው ምንድነው የሚለውን እንቆቅልሽ ለመፍታት ጊዜ አናጠፋም። እውነታው ግን ልዩ ኃይሎችን በአዲስ አደረጃጀት እንዲዋቀሩ ማድረግ የአገሪቱን ሰላም ከማስፈን ባሻገር ትልቁን የኢትዮጵያ ምስል የሚመለከት ጠንካራ የሀገር መከላካያ እና የፌዴራል ፖሊስ እንዲገነባ ያደርጋል። አንድ ወጥ የሆነ የጸጥታ ኃይል ሲገነባ ደግሞ ውጫዊም ውስጣዊም ስጋቶች እንዳይኖሩብን ያስችለናል።

እንደሀገር ካሉብን ስጋቶች አንጻር ጠንካራ እና ወጥ የሆነ ዘመናዊ የጦር ኃይል መገንባት ይጠበቅብናል። ይህንን እውን ለማድረግ ደግሞ የተበታተነውን ኃይላችንን ወደ አንድ በማሰባሰብ አስፈላጊውን ወታደራዊ ቁመና ተላብሰን በሁለንተናዊ ዝግጁነት በተጠንቀቅ መቆም ይጠበቅብናል፤ ለዚህ ደግሞ የልዩ ኃይሉን አደረጃጀት መቃኘት አስፈላጊና ወቅታዊ ነው።

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## የአዕምሮ እድገት ውስንነትን በፍቅር

መክሊት ወንድወሰን

**ድንገቴው እግር**

በስራ አጋጣሚ ወደ አንድ ተቋም አመራሁ። ይህ ተቋም የአእምሮ እድገት ውስንነት(ኦቲዝም) ያለባቸው ወገኖች መገኛ ነው። በዕለቱ እግሬ ወደ ብሄራዊ ማህበሩ እየረገጠ ነበር። ገና ወደ ውስጥ ከመዝለቄ ሰዎችን ለማየት የናፈቁ አይኖች ከአይኖቼ ሲጋጩ አስተዋልኩ።

የልጆቹ ዓይኖች ሰው እንደራባቸው ያሳብቃሉ ። ከመግቢያ በሩ ጥቂት አለፍ እንዳልኩ አንድ በፍጥነት ሲሮጥ የቆየ ልጅ በድንገት ደርሶ ተጋጨኝ። ለጊዜው ብደነግጥም አንዳች ቃል አልተነፈስኩም። ቀልጠፍ ብዬ ከመሬት የወደቀውን የእጅ ስልኬን ላነሳ ጎንበስ ከማለቴ በእጅጉ ከደነገጠው ልጅ ጋር ዳግም ተፋጠጥኩኝ። በፊቱ ጭንቀትና መደናገር ይነበባል። በጣም ደንግጦ ነበርና ደጋግሞ ይቅርታ ‹‹ይቅርታ›› ይለኝ ያዘ ።

ልጁ በእዚህ ብቻ የበቃው አይመስልም። በአይኖቹ ይቅርታውን መቀበሌን ለማረጋገጥ ይመስላል በትኩረት ማተረ ። አላስደነገጥኩትም ‹‹ችግር የለውም ያጋጥማል›› ብዬው ወደ ፊት ተራመድኩ። ካሰብኩት ክፍል ስደርስ በርካታ የአእምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ልጆች ምንጣፍ ፤ ሸማ እና ሌሎችንም የእጅ ስራዎች ሲከውኑ አስተዋልኩ። በሁኔታቸው መገርም መደነቄ አልቀረም።

ልጆቹ ስራቸውን የሚሰሩት በከፍተኛ ትኩረት ነው። ሁሉም በሚባል መልኩ በአይኖቻቸው ሰላም ብለውኝ ወደ ስራቸው አቀረቀሩ። ቆሜ የሚሰሩትን ሁሉ ማየት ጀመርኩ። ይህኔ ቅድም በድንገት የተጋጨሁት ልጅ ወደ እኔ ተመልሶ መጥቶ ነበር። ወዲያው ማንን እንደፈለኩ በተለየ አክብሮትና ትህትና ጠየቀኝ።

የፈለኩትን ሰው ማንነት ተናግሬ ወደ ውስጥ ዘለቅሁ። አመጣጤ የማህበሩን ስራ አስኪያጅ ለማግኘት ነበር። ወይዘሮ የሸዋጌጥ ክብረት ትባላለች። መምጣቴን እንዳየች በአክብሮት ተቀብላ አስተናገደችኝ። ውይይታችንን ከመጀመራችን በፊት እርስ በእርስ በመተዋወቅ ጥቂት አወራን። ቀለል አለኝ።

ወይዘሮ ሸዋጌጥ ክብረት በፍቅር የአእምሮ እድገት ውስንነት ብሄራዊ ማህበር ስራ አስኪያጅ በመሆን ታገለግላለች። ማህበሩን በ1987 ዓም 80 የሚሆኑ የአእምሮ እድገት ውስነት ባለባቸው ልጆች ወላጆች የተቋቋመ ነው። በአሁኑ ጊዜ ከ 15 ሺ በላይ አባላት አሉት ።

የማህበሩ ዋነኛ አላማ ለህብረተሰቡ በቂ ግንዛቤ መፍጠር ነው። በተጓዳኝም የአእምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ልጆች የተሻለ አገልግሎት እንዲያገኙ ያግዛል። ልጆቹ በልጅነታቸው የህመም ደረጃቸው ከተለየ በአካባቢው ወደሚገኙ የትምህርት ተቋማት ገብተው እንዲማሩ ይደረጋል።

በርካታ ወላጆች ልጆቻቸው ማንኛውም አይነት ጥቃት እንዳያገኛቸው ይሰጋሉ ። በተያያዘም ከሰዎች መገለል እንዳይደርስባቸው ልጆቻቸውን ይደብቃሉ። በልጆቻቸው የሚያፍሩና የሚሸማቀቁም አይታጡም። ይህ አይነቱ አጋጣሚም ልጆቻቸውን ለ20 እና 30 አመታትን በቤት ውስጥ አስረውና ደብቀው እንዲያቆዩዋቸው ምክንያት ይፈጥራል ።

**የወላጆች ነገር**

ወይዘሮ የሸዋ ጌጥ ወላጆች ስለልጆቻቸው ያላቸው ግንዛቤ የተለያየ ስለመሆኑ ይናገራሉ።

አንዳንድ ወላጆች በልጆቻቸው የደረሰው የጤና ችግር በርግማን እና በፈጣሪ ቁጣ እንደሆነ ያምናሉ። እሳቸው እንደሚሉት የማህበሩ ዋንኛ አላማ ወላጆች በልጆቻቸው ሀፍረትና ሀዘን እንዳይሰማቸው ማድረግ ላይ ያተኩራል ። ሁሌም ወላጆች ከጠነከሩ፣ ከበረቱ የልጆቻውን እና የራሳቸውን መብት ማስጠበቅ ይችላሉ።




**ቀልጣፋው ኪሩቤል**

በግቢው ኪሩቤል የሚባል የራስ መብት ተሟጋች ክፍል ኃላፊ በስራ ላይ ይገኛል። ኪሩቤል የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ይታይበታል። እንዲያም ሆኖ ከሌሎች ሰራተኞች እኩል ስራዎችን በጥንቃቄና በአግባቡ ይከውናል። ሁሌም ቢሆን ኪሩቤል በራሱ አቅዶ የሚሰራ ትጉህ ሰራተኛ ነው። በእጁ ያለውን ስራ ሳይጠናቀቅ ፈጽሞ ለመሄድ አይነሳም ። እንደውም አንዳንዴ የምሳ ሰአቱን እና ወደቤት የመሄጃ ጊዜውን ሳይቀር መስዋእት ያደርጋል።

የአእምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ልጆች ከሌላው ሰው በተሻለ ሀቀኞች ናቸው። ስራዎችን ሲከውኑ በአትኩሮት ነው። የሚሰማቸውን ስሜት ፊት ለፊት ይናገራሉ። የማህበራዊ ህይወት ተሳትፏቸው ደግሞ ከሌሎች ለየት ይላል።

ማህበሩ ግንዛቤ ከመፍጠር አኳያ ጥሩ ስራዎችን የሰራ ቢሆንም አሁንም የህብረተሰቡ ንቃተ ህሊና ላይ መስራት እንደሚኖርበት ወይዘሮ ሸዋጌጥ ያምናሉ፡ ። ማህበረሰባችን አሁንም ድረስ የአእምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ልጆች እንደማይችሉ አድርጎ ያስባል። ሁሌም የሰዎች ጥገኛ እንደሆኑ የሚኖሩ የሚመስላቸው ብዙ ሰዎች አሉ። እውነታው ግን ይህ አይደለም። የአእምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ልጆች ሰርቶ መግባት በራሳቸው ገቢ የመኖር አቅም እና ችሎታዎች አሏቸው።

ወይዘሮ ሸዋጌጥ በግቢው ስለሚገኝ አንድ ወጣት ያወጉኝ ይዘዋል። ወጣቱ የአእምሮ እድገት ውስንነት ያለበት ልጅ ነው። ልጅ ይባል እንጂ በደሞዝ ተቀጥሮ የሚሰራ ሰራተኛ መሆኑን ሰምቻለሁ። እኔም ብሆን አስቀድሜ አውቄ ዋለሁ ። ኪሩቤል ይባላል። የአእምሮ እድገት ውስንነት ያለበት ወጣት ነው ።

ኪሩቤል በባህሪው እጅግ ምስጉንና ተግባቢ ነው። ከስራ ገበታው በፍጹም አይቀርም አያረፍድም። ምናልባት ችግር እንኳን ካጋጠመው ደውሎ ይናገራል፣ አጥብቆ ይቅርታ ይጠይቃል። ምሳ ሰአት ነው ብሎ የጀመረውን ስራ ሳይጨርስ አይወጣም። አዳዲስ ሀሳቦችን በማምጣት ይተጋል። ያቃተውን ደግሞ ከሌሎች እርዳታ ጠይቆ ለፍጻሜ ያበቃዋል ። ከወይዘሮዋ የሰማሁት እውነት እያስደነቀኝ ስለኪሩቤል ቀሪ ታሪኮችን ማድመጥ ይዣለሁ።

ኪሩቤል ውይይቶች ሲኖሩ መድረኮችን ይመራል። የመክፈቻ ንግግርም ያደርጋል። የምሰማውን ነገር ማመን አልቻልኩም። ልጁን ለማየት እንደምፈልግ ተናገርኩ አፍታ አልቆየም ። ከኪሩቤል ጋር ተገናኘን።

**እኔና እሱ**

ስሙን ኪሩቢል አንተነህ ሲል ዳግም አስተዋወቀኝ እድሜው 23 አመት ነው። የአእምሮ እድገት ውስንነት አለበት። የሚኖረው ከወላጅ እናቱ ጋር መሆኑን አወጋኝ ። እናቱ ልጃቸውን በተለየ ፍቅር እና በእንክብካቤ ነው ያሳደጉት። ሁሌም ቢሆን በእሱ መኖር ደስተኛ ናቸው። ኪሩቤል ስለራሱ እንዲህ አለኝ።

‹‹ ሰዎች በአይን አይተው ብቻ የአእምሮ እድገት ውስንነት እንዳለብኝ አያውቁም። ምናልባት እኔ ወይም የሚያውቀኝ ሰው ካልነገራቸው ። የአእምሮ እድገት ውስንነት ከመስራት ፤ ከመማር፣ በስራ ውጤታማ ከመሆን እንደማያግድ እኔ አንዱ ማሳያ ነኝ ››

ኪሩቤልን በፍቅር የአይምሮ እድገት ውስንነት ተቋም ውስጥ ያለውን የስራ ድርሻ እንዲነግረኝ ጠየቅሁት። ኪሩቢል አሁን በፍቅር የአእምሮ ውስንነት ማህበር የራስ መብት ተሟጋች ኃላፊ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል። ስራውን በእጅጉ ይወዳል፣ ያከብራል ።

የእሱ የምንግዜም ተግባር የአይምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸውን ልጆች የፈለጉበት ደረጃ እንደሚደርሱ ማነቃቃት፣ ስራዎችን እንዴት መስራት እንዳለባቸው ማሳየት ፣ የልጆቹ ወላጆች ደግሞ ልጆቻቸው ያለባቸውን የአይምሮ እድገት ውስንነት እንዲቀበሉ ማድረግ ላይ ያተኩራል። ኪሩቤል በመስሪያ ቤቱ ብቻ ሳይሆን በሶሻል ሚዲያ ጭምር በመታገዝ በጎ መልዕክቶችን በማስተላለፍ ይታወቃል።

ኪሩቤል የአይምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ልጆች ወላጆች ምን እንደሚጠበቅባቸው ጠንቅቆ ያውቃል። ወላጆች እንደሱ ቤተሰብ በልጆቻቸው ላይ ያለውን የአይምሮ እድገት ውስንነት መቀበል ከቻሉ እና በአግባቡ ከተንከባከቧቸው ልጆቹ የሚፈልጉት ቦታ መድረስ እንደሚችሉ በቂ ግንዛቤን አዳብሯል።

ወላጆች ብዙ ጊዜ የአእምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ልጆች ሲኖሯቸው የልጆቻቸውን ችግር መቀበል አይፈልጉም። ወደ ተለያዩ የዕምነት ስፍራዎች በመውሰድ ልጆቹ እንዲድኑላቸው የራሳቸውን ጥረት ያደርጋሉ ። የአእምሮ እድገት ውስንነት የሚድን ችግር ሳይሆን በእንክብካቤ እና በድጋፍ ለውጥ የሚመጣበት ነው።

ኪሩቤል ይህን እውነታ ለማወቅ አስረጂ አስፈልጎት አያውቅም። በቻለው አቅም ሁሉ የራሱን ጥረት አድርጎ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ይጥራል። እሱ ሁሌም ቢሆን ስለ ወላጅ እናቱ መልካምነት ምስክር ከመሆን ታቅቦ አያውቅም። ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ እናቱን ከልብ ያመሰግናል።

‹‹ወላጅ እናቴ ያለብኝን ችግር ተቀብላ ድጋፍ ላገኝበት ወደምችለው ተቋም ወስዳኛለች ለዚህም ዛሬ እዚህ ላይ ልደርስ ችያለው››ይላል ወጣት ኪሩቤል ስለ እናቱ ሲናገር።

ወይዘሮ የሸዋጌጥ እንደሚሉት አዲስአበባ ላይ ከ 22 በላይ አካቶ ትምህርት የሚሰጥባቸው የመንግስት ትምህርት ቤቶች አሉ። በነዚህ ትምህርት ቤቶችም የአዕምሮ ዕድገት ውስንነት ያለባቸው ልጆች በእኩል ይማራሉ ። እንደ ወይዘሮዋ አስተያየት በቤተሰብ መሀል ልጆች ሲያድጉ የራስን ጥረትና ክትትል ማድረግ ያሻል ። አንዳንድ ሰዎች ለእንዲህ አይነት ልጆች ዝቅተኛ አመለካከት አላቸው። ይህ በመሆኑም ማንኛውንም ሥራ አምነው ለመስጠት አመኔታው የላቸውም ።

እንደወይዘሮዋ ሀሳብ ግን ይህ አይነቱ ያልተገባ አመለካከት ማንንም አይጠቅምም። ኪሩቤል በተቋሙ ሰራተኛ ሆኖ ሲቀጠር በማንነቱ ሳይሆን ባለው ችሎታና ዕውቀት ተመዝኖ ነው። ወይዘሮ የሸዋጌጥ ለወላጆች ይበጃል የሚሉትን መልዕክት እነሆ ይላሉ።

ሁሌም ቢሆን ወላጆች በልጆቻቸው ላይ ያልተለመዱ ለውጦችን ሲያስተውሉ መጠራጠር ይገባቸዋል ። ለምሳሌ ልጆቹ ቶሎ አፍ ካልፈቱ ፤ አንድ ነገር ላይ ብቻ ትኩረት ካደረጉ ፣ እንደ እኩዮቻቸው መራመድ ባለባቸው እድሜ መሄድ ካልጀመሩ ወደ ጤና ተቋም በመሄድ የልጆቹን የጤና ሁኔታ ማጣራት ይኖርባቸዋል።

ይህ ብቻ አይደለም ። ወላጆች የልጆቻቸውን ችግር ካወቁ በኋላ ልጆቹን ሊመጥኑ ወደሚችሉ ተቋማት በመውሰድ በትምህርትና በስነልቦና እገዛ እንዲያገኙ መጣር አለባቸው። ይህ አይነቱ ክትትልና ሙከራ ካለም እንደ ወጣት ኪሩቤል ጥሩ የሚባል ደረጃ ለማድረስ የሚያግዳቸው አይኖርም ።

**የፍቅር ገበታን በእኩል**

ፍቅር የአእምሮ ውስንነት ማህበር እንደቃሉ ሆኖ ሁሉንም ተማሪዎች በፍቅር አቅፎ ይዟል ። ተማሪዎቹ በእኩል የመማራቸው ሂደት ነገ ለሚደርሱበት ዓለም የተሻለ ዕውቀትና መልካም አስተሳብን ይዘው እንዲቀጥሉ ያግዛል።

በዓለማችን በርካታ የአእምሮ ዕድገት ውስንነት ያለባቸው ሰዎች በቀለም ትምህርት የተሻለ ደረጃ ላይ ደርሰዋል ። በፈጠራ ስራዎቻቸው እውቅናና ታዋቂነትን ያተረፉም አሉ። ጥቂት የማይባሉት ትምህርታቸውን እስከ ዲግሪ ደረጃ አሳድገዋል ። በትዳር ዓለም ከሀያ አመታት በላይ የቆዩ ጥንዶችም በአርአያነት ይጠቀሳሉ።

ወይዘሮ የሸዋጌጥ እንደሚሉትም በተቋሙ መጀመሪያ የአእምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ልጆች የቀለም ትምህርት እንዲማሩ ይሞከራል። ሙከራው የታሰበውን ያህል ውጤት ካላስገኘ ግን ልጆች በተለያዩ የሙያ ዘርፎች በቂ ስልጠና ይሰጣቸዋል። ይህ በመደረጉም ዛሬ በርካቶቹ እንደየፍላጎታቸው በተለያዩ ተግባራት ተሰማርተው ይገኛሉ። በአሁኑ ጊዜ ተቋሙ ከሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በዓመመልዕክት ለሌሎች

እንደኪሩቤል መሰል ወጣቶች ባማንነታቸው መገለልና አድሎ ካልተደረገባቸው ነገን በተስፋ ይሻገራሉ። ችሎታና ዕወቀታቸውን ሚያከብርላቸው ካገኙም ለበርካቶች አርአያና ምሳሌ ሆነው አገርን ይገነባሉ። ፍቅር አይምሮ ዕድገት ውስንነት ማህበር ሁሉንም ተማሪዎች በአንድ አሳበስቦ ፍቅር መመገቡ ነገ ለአይን የሚያጠግብ፣ ለአይምሮ የሚያረካ ተግባር መነሻ ይሆናል።

አዎ! የአእምሮ ዕድገት ውስንነት ያለባቸው ወገኖች ፍቅርን ከተቸሩ ራሳቸውን፣ ወገናቸውን፣ ብሎም አገርንና ዓለምን ይለውጣሉ። ዛሬ የምንተውላቸው በጎ አሻራም ለነገ ማንነታቸው ደማቅ ማህተም ሆኖ ታሪካቸውን ይቀይራል።

ኢኮኖሚ

ስኬት

# ስልጅ በተከፈለ መስዋዕትነት አገርን ከፍ ያደረገ ተግባር

ፍሬሕይወት አወቀ

ብዙዎች በትወና ሥራዎቿ ያውቋታል። እሷ ግን ብዙዎች ከሚያውቋት ከትወና ሥራዎቿ በበለጠ ሰው ተኮር ለሆኑ ሥራዎቿ አብዝታ ታደላለች። የአርቲስትነት ሙያን በእጅጉ የምታከብር ብትሆንም «አርቲስት» በሚለው የሙያ መጠሪያዋ ባትጠራ ትመርጣለች። ሕይወትን ቀለል አድርጋ መምራት ያስደስታታል። ውስጧ የሚያዝዛትን ለማድረግ ሁለት ጊዜ አታስብም። ፈጣን፣ ቀልጣፋና የውሳኔ ሰው ከመሆኗም በላይ ማንኛውንም ያመነችበትን ነገር ከውስጧ በመነጨ ዕምቅ ፍላጎት ትከውናለች። ለዚህ ባህሪዋም በነጻነት ግን ደግሞ ጥብቅ በሆነ ኢትዮጵያዊ ስነ ስርዓት ያሳደጓት ቤተሰቦቿ የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳሉ።

በትወና ሥራ የተዋጣላቸው ናቸው ከሚባሉ አርቲስቶች ተርታ የምትሰለፈው የዕለቱ የስኬት እንግዳችን ከትወና ሥራዋ ባለፈ የህክምና ማእከል ባለቤት የሆነችው የስዊዝ ዲያግኖስቲክስ የህክምና ማዕከል መስራችና ባለቤት የትናየት ታምራት ወይም ሚሚ ናት። የትናየት፣ «ሚሚ» በሚለው የቤት ስሟ በስፋት ትታወቃለች። ለህዝብ አይንና ጆሮ የደረሱ ጥቂት የማይባሉ የፊልም ሥራዎች ያሏት የትናየት፤ ከትወና ሥራዎቿ በላይ ጊዜዋን በበጎ ሥራ ማሳለፍ ያስደስታታል። ፈጣን፣ ቀልጣፋ፣ ተግባቢና ቅን አሳቢም ናት።

በልጇ ጤና ማጣት ብዙ ዋጋ ከፍላለች። ታድያ የከፈለችውን ዋጋ በማሰብ በአይነቱ ልዩ የሆነ የስዊዝ ዲያግኖስቲክስ የህክምና ማዕከልን በማቋቋም በወቅቱ ልጇ በአገር ውስጥ ማግኘት ያልቻለችውን አገልግሎት ዛሬ ለህዝቡ እንካችሁ ብላለች።

አዲስ አበባ ከተማ ልደታ አካባቢ ተወልዳ፣ አትላስ አካባቢ ያደገችው የትናየት መካከለኛ ገቢ ካላቸው ወላጆች ብትገኝም፣ አስተዳደጓ ከአብዛኛው ኢትዮጵያዊ የተለየ አይደለም። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቷን መጠነኛ ክፍያ በሚጠይቅ ትምህርት ቤት በክፍያ ብትማርም፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ደግሞ ከአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ጋር በመንግሥት ትምህርት ቤት ተምራለች። ይህም አብሮነትን መማር እንድትችል አግዟታል።

አንድ ቦታ ላይ ብዙ መቆየት የማትፈልገው የትናየት፤ ከትወና ሥራዎቿ አስቀድማ ገና በልጅነቷ የተለያዩ ሥራዎችን ሠርታለች። በሥራዎቿ ሁሉ ስኬትን መጎናጸፍ ለእርሷ አዲስ አይደለም።

ቀልጣፋና ፈጣን በሆነ ተፈጥሮዋ ጎበዝ ተማሪነቷ ታክሎበት በሕይወት መንገድ ውስጥ የስኬት መሰላልን መውጣት ችላለች። የአካውንቲንግ ትምህርቷን በአድማስ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ተከታትላ የመመረቂያ ጽሑፏን ባስገባች ማግስት ነው ሥራ መሥራት እንዳለባት የወሰነችው።

ያኔ የአባቷ ጓደኛ የሆኑ አንድ ሰው የቤትና የቢሮ ዕቃዎች ያስመጡ ነበርና እሳቸው ዘንድ ተቀጥራ መሥራት እንድትችል ወላጅ አባቷ ሁኔታዎችን አመቻቹላት። ይህ አጋጣሚ ሌላ የሥራ ዕድል ፈጥሮላት ከተመረቀች በኋላ ዘመናዊ በሆነ የህጻናት መዝናኛ ማዕከል ውስጥ የመቀጠር ዕድል አግኝታለች። ይህም ትላልቅና ታዋቂ ሰዎችን የመተዋወቅ አጋጣሚን ፈጥሮላታል።

በዚሁ አጋጣሚ የተዋወቀችው ሌላ ሰው ደግሞ ሌላ ሥራ ይዞ ከቀልጣፋዋ የትናየት ጋር በጋራ ለመሥራት አጥብቆ በመሻቱ የማተሚያ ቤት ሥራን በጋራ ሠርታለች። አዲስ ነገር ለማወቅ ከፍተኛ ፍላጎት ያላት የትናየት፤ የግራፊክ ዲዛይን ሥራን ከሀ እስከ ፐ ከድርጅቱ ባለቤት ተምራለች። ስካን (scan) ከማድረግ ጀምራ የማተሚያ ቤት ሥራን በሙሉ ጥንቅቅ አድርጋ ማወቅ ቻለች።

አንድ ቦታ ላይ መቆየት ባህሪዋ ያልሆነው የትናየት፤ በፈጣን ውሳኔዋ «የራሴን ሥራ መሥራት አለብኝ» በማለት ሥራውን ለቃ ወጣች። በአጭር ጊዜ ቆይታዋ በርካታ ሰዎችን መተዋወቅ የቻለችው ፈጣኗ የትናየት፤ ብዙም ሳትቆይ በቤተሰቦቿ ሳሎን ቤት የራሷን ማተሚያ ቤት ከፈተች። ያኔ ማተሚያ ማሽን ባይኖራትም የዲዛይን ሥራውን ጥንቅቅ አድርጋ በመሥራት የህትመት ሥራውን የማተሚያ ማሽን ያላቸው ድርጅቶች ጋ ወስዳ ታሳትም ነበር።


አርቲስት የትናየት ታምራት

በዚህ ሥራም በርካታ ደንበኞችን በማፍራት ከቢዝነስ ካርድ ጀምሮ ቢል ቦርድ፣ ኮፍያ፣ ቲሸርት፣ የመመረቂያ መጽሔትና ሌሎች በርካታ ሥራዎችን በጥራት መሥራት ጀመረች። ለዚህም አስቀድማ ትሠራበት ከነበረው ድርጅት ብዙ ዕውቀት መቅሰሟን አልሸሸገችም።

ሥራዋ እየሰፋ ሲመጣም የቤተሰቦቿ ሳሎን ቤት አልበቃትም። እናም የቤተሰቦቿን የሚከራይ ሶስት ክፍል ቤት ተከራይታ ከሳሎን ወጣች። ሥራው እየተሳለጠ ደንበኞቿም እየበረከቱ ሲመጡ ደግሞ ሌላ ፍላጎት መጣ። በቤተሰቦቿ ግቢ ውስጥ መሥራት ምቾት አልሰጥ አላት። ለዚህም መፍትሔ አላጣችም፤ ሁለት ጊዜ ሳታስብ በሰባት ሺ 500 ብር ግቢ ቤት ተከራይታ ከቤተሰቦቿ ግቢ ወጣች። ከቤተሰቦቿ ጉያ ተነጥላ ለመሥራት የወሰነችው የትናየት፤ በወቅቱ ከወላጅ እናቷ ተቃውሞ ቢገጥማትም አባቷ ግን ፈቃዳቸውን ሰጥተው በነጻነት ሥራዋን መሥራት እንድትችል አድርገዋታል።

በወጣትነት ትኩስ ኃይል የሥራ ዓለምን የተቀላቀለችው የትናየት፤ ገና ከልጅነቷ ጀምራ ሰዎችን ማቅረብ፣ መርዳትና ማገዝ ያስደስታታል። በምታገኘው ልክ ሰዎችን በመርዳት የምትታወቀው የትናየት «ያገኘሁትን በመስጠቴ ጎድሎብኝ አያውቅም» ትላለች።

በወቅቱ በኤች አይ ቪ የተያዙና ሌሎች ተያያዥ ችግር ያለባቸውን የማህበረሰብ ክፍሎች ታግዝ እንደነበርም ታስታውሳለች። በአፍላ ዕድሜዋ በሥራ ዓለም ውስጥ ገብታ ከላይ ታች ያለችው የትናየት፤ ወደ አርት ሞያ ውስጥም ሆነ በአይነቱ ልዩ የሆነ ስዊዝ ዲያግኖስቲክስ ዘመናዊ የላቦራቶሪ ማዕከልን ለመገንባት ምክንያት የሆነቻት በልጅነቷ የወለደቻት የመጀመሪያ ልጇ እንደሆነች ትናገራለች።

በዘጠኙም ወራት የእርግዝና ጊዜዋ በጽኑ ስትታመም የነበረችው የትናየት፤ ልጇን በሰላም ወልዳ ማሳደግ ብትችልም፤ ህጻኗ ግን ልጆች በጊዜ ሂደት የሚያመጡትን የዕድገት ለውጥ ማምጣት አልቻለችምና የጤና ችግር የገጠማት መሆኑን በማረጋገጥ ወደ ህክምና ተቋም ወሰደቻት። ወደ ህክምና ተቋም በሄደች ጊዜ እርሷ ከገጠማት ችግር በበለጠ ብዙ ችግሮችን፣ ህመምና ስቃዮችን መመልከቷን ታስታውሳለች። በተለይም ለህክምና ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ባቀናችበት ወቅት የብዙ እናቶችን ስቃይ አይታ አብራ ተሰቃይታለች፤ ህመማቸውን ከህመሟ ጋር ደርባ በመታመም በብርቱ ተፈትናለች።

«ጎሽ ለልጇ ስትል ተወጋች» እንዲሉ ለወትሮ ተርብ የነበረችው የትናየት፣ በልጇ ጤና ማጣት ክንፏ እንደተመታች ወፍ ኩርምት ብላ ዓመታትን አሳለፈች፤ ዕምቅ ችሎታዋን አዳፍና በብርቱ የተፈተነችው የትናየት፤ ለሶስት ዓመታት ልጇን ከመንከባከብ ውጭ ሥራ አልነበራትም።

ይህን የተረዳውና ቅርቧ የሆነው ሰራዊት ፍቅሬ ከደረሰባት ከፍተኛ የስነ ልቦና ስብራት ወጥታ አቅሟን መጠቀም አንድትችል ምክንያት ሆኖ የትወናውን ዓለም እንድትቀላቀል እጇን ይዞ እንዳስገባት ታስታውሳለች። በነጻነት እምቅ ችሎታዋን አውጥታ መጠቀም በመቻሏም እንደ ቀልድ የጀመረችው የትወና ሥራ ዕውቅናን አተረፈላት። ከትወና ሥራዋ ጎን ለጎን ለአፍታም ቢሆን የማትዘነጋው የልጇን ጤና መከታተል ነውና ለፈውሷ ያልደረሰችበት አልነበረም።

በልጇ ህመም የደረሰባትን ጉዳትና የመንፈስ ስብራት ተቋቁማ ወደ አርት የገባችው የትናየት፤ ከትወና በተጨማሪ የተለያዩ ፊልሞችንም ጽፋለች። ለአብነትም ሴት ልጅ ጠንካራ እንደሆነች ራሷን ምስክር በማድረግ «ያነገስከኝ» በሚለው የፊልም ሥራዋ ሴቶች ከተደገፉ አገርን መለወጥ እንደሚችሉ አሳይታለች። «ሃምሳ ሎሚ» በሚለው የፊልም ሥራዋ ደግሞ ህጻናት ላይ መሥራት ለለውጥ ትልቁ ምክንያት እንደሆነ መስክራለች። ከፊልም ሥራዋ በተጨማሪ የተለያዩ ሥራዎችን በመሥራት ከራሷ አልፋ ለብዙዎች ድካም ብርታትና መፍትሔ ለመሆን ከላይ ታች የምትለው የትናየት፣ ልጇ በገጠማት የጤና ችግር ምክንያት በቀላሉ መዳን የሚችለው ሕመሟ በህክምና ስህተት ይበልጡኑ መባባሱን አጫውታናለች።

ይሁንና አጋጣሚው ፈቅዶላት ልጇን ስዊዘርላንድ አገር ወስዳ ማሳከም የቻለችው የትናየት፤ ከአምስት ሰዓታት በላይ በወሰደ የቀዶ ህክምና የልጇ ጤና መሻሻል እንደታየበት ነው የገለጸችው። የትናየት ምንም እንኳን የህክምና ትምህርት ባይኖራትም በልጇ ህመም ምክንያት ለህክምናው ቅርብ ሆና ክፍተቶችን ታስተውል እንደነበር ታስታውሳለች። ይህን ክፍተት ለመሙላትም የህክምና ማዕከሉን በአገር ውስጥ አቋቁማ ዕድሉን ያላገኙ ሰዎች የህክምና አገልግሎቱን እንዲያገኙ ለማድረግ ስትወስን ሁለት ጊዜ አላሰበችም። ስዊዘርላንድ አገር ያየችውን ዘመናዊ ህክምና አገሯ ላይ ቢኖር ብላ ተመኘች። ህልሟን ዕውን ለማድረግም ያለ የሌለ ሃብትና ንብረቷን በመመደብ ስዊዝ ዲያግኖስቲክስ ዘመናዊ የላብራቶሪ ማዕከልን በመቶ ሚሊዮኖች ገንዘብ ማቋቋም ቻለች።

ኢትዮጵያ ውስጥ በህክምናው ዘርፍ ያለውን ክፍተት በሚገባ የተረዳችው የትናየት፤ እጅግ በጣም ጎበዝ የሆኑ ሀኪሞች ኢትዮጵያ ውስጥ ስለመኖራቸው ትናገራለች። ይሁንና እነዚህ ጎበዝ ሀኪሞች የተሳሳተ የላብራቶሪ ውጤት ሊደርሳቸው እንደሚችልና የህክምና ስህተት ሊፈጠር እንደሚችል ትገልጻለች። ይህ ዘመናዊ የላብራቶሪ ማዕከል ግን የህክምና ስህተት እንዳይፈጠር ከማድረግ ባለፈ ወደ ውጭ አገር ተልኮ ይመረመር የነበረውን ምርመራ በማስቀረት ፈጣንና ጥራት ያለው አገልግሎት የሚሰጥ፤ እጅግ ዘመናዊ የላብራቶሪ ማዕከል እንደሆነ ነው የተናገረችው።

ዘመናዊ ህክምና ለዜጎች የግድ እንደሆነ የምታምነው የትናየት፤ በልጇ ምክንያት ያስተዋለችውን የህክምና ክፍተት ለማሟላት በተነሳች ጊዜ ከመንግሥት አበረታች የሆኑ ድጋፎችን አለማግኘቷ ግን ቅር እንዳሰኛት ትናገራለች። እሷ ግን የሚፈለገውን መስዋዕትነት ከፍላ ዘመናዊ የላቦራቶሪ ህክምና ማዕከሉ አገልግሎት እንዲሰጥ አድርጋለች። በዚህ አጋጣሚ በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ሆነው ሥራን የሚያደናቅፉ አካላት ስለመኖራቸው የታዘበችው የትናየት፣ ማገዝና መደገፍ ቢያቅታቸው ቢያንስ እንቅፋት እንዳይሆኑ ስትል መልዕክቷን አስተላልፋለች።

ወደ ሥራው ስትገባ ነገሮች አልጋ በአልጋ አልነበሩም፤ አስቸጋሪ የተባሉ ውጣ ውረዶችን አልፋ በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ የሌሉ እጅግ ዘመናዊ የህክምና ማሽኖችን በአገር ውስጥ አስገብታ ህዝብ እንዲገለገልበት አድርጋለች። እነዚህ የህክምና መሳሪያዎች ለህብረተሰቡ በእጅጉ አስፈላጊ እንደሆኑ የምትጠቅሰው የትናየት፤ ስዊዝ ዲያግኖስቲክስ ከ40 በላይ የሆኑ ምርመራዎችን ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ ለማህበረሰቡ እየሰጠ መሆኑን በማስታወስ ማህበረሰቡ ይህን አጋጣሚ ተጠቅሞ የተለያዩ ምርመራዎችን በማድረግ ጤናውን እንዲጠብቅ ትመክራለች።

ከዚህ ቀደም ወደ ውጭ አገር ተልኮ ውጤቱ እስኪመጣ እስከ 45 ቀን ይፈጅ የነበረውን የላብራቶሪ ህክምና በአሁኑ ወቅት በባህሪው ሁለት ቀናት የሚፈልግ ውጤት ካልሆነ በስተቀር በአብዛኛው በሰዓታት ልዩነት ውስጥ የላብራቶሪ ውጤት ማግኘት ይቻላል። «ስዊዘርላንድና አሜሪካ እንዲሁም በሌሎች የዓለም አገራት አሁን ላይ ያለው የህክምና ቴክኖሎጂ በስዊዝ ዲያግኖስቲክስ ማዕከል ውስጥ ያለ የህክምና ቴክኖሎጂ ነው» የምትለው የትናየት፤ አገልግሎቱ ለማህበረሰቡ እጅግ አስፈላጊ የሆነ የጤና መፍትሔ ነው ትላለች።

በኢትዮጵያ የላብራቶሪ ህክምና ማዕከል ልዩ የሆነው ስዊዝ ዲያግኖስቲክስ ከቢዝነስ በላይ እንደሆነ የምትናገረው የትናየት፤ የብዙዎችን ድካምና እንግልት ያስቀረና ሕይወት ማዳን የሚችል ነው። ከዚህም በላይ ማዕከሉ በአገልግሎት አሰጣጡ አገርን ከፍ ማድረግ የቻለና የዘመነ መሆኑን በኩራት ትገልጻለች።

በቀጣይም ስዊዝ ዲያግኖስቲክስ ኢትዮጵያን በላብራቶሪ ህክምና ዘርፍ ከፍ በማድረግ፤ ከምስራቅ አፍሪካ ምሳሌ የሆነች ቀዳሚ የጤና ማዕከል እንድትሆን ማድረግ ፍላጎቷ መሆኑን አጫውታናለች። እርግጥ ነው ለተግባራዊነቱ በርካታ መሰናክሎች ይኖራሉ የምትለው የትናየት፤ የትኛውም እንቅፋት ግን ፍጥነቷን ሊገታ ይችል ይሆናል እንጂ ከጉዞዋ ሊያስቀራት እንደማይችል ነው የተናገረችው።

በስዊዝ ዲያግኖስቲክስ የህክምና ማዕከል ውስጥ የሚገኙ ዘመናዊ የህክምና መሳሪያዎች በሙሉ ከስዊዘርላንድ፣ ጀርመንና ቻይና የመጡ መሆናቸውን ጠቅሳ፣ ለአገር ውስጥ ባለሙያዎች ስልጠና በመስጠት የቴክኖሎጂ ሽግግር ማድረግ እንደተቻለም ገልጻለች። በማዕከሉ ከ40 የሚበልጡ ባለሙያዎች የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው መሆኑን ገልጻለች።

ሰዎች የምርመራ ውጤታቸው ከእጅ ንክኪ ነጻ በሆነ መንገድ ተዘጋጅቶ ያለምንም እንግልት ባጠረ ጊዜ እንደሚያገኙት የገለጸችው የትናየት፤ ሰዎች ወደ ማዕከሉ መምጣት ሳይጠበቅባቸው ባለሙያዎች ካሉበት ቦታ ሄደው ናሙናዎችን እንደሚወስዱና ውጤቱም በተመሳሳይ የእጅ ስልክን በመጠቀም በተለያዩ አማራጮች ካሉበት ቦታ የሚደርሳቸው መሆኑን አስረድታለች። ለዚህም ማዕከሉ በቂ ባለሙያዎች፣ መሳሪያዎች፣ ሞተረኞችና መኪኖች አሉት። ይህም ሥራውን ቀልጣፋ አድርጎታል ስትል ታብራራለች።

ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ወጪ በማድረግ የብዙዎችን ችግር ለማቃለል የምትሰራው የትናየት፤ በግሏም ሆነ በድርጅቷ ስም የተለያዩ ድጋፎችን ታደርጋለች። መንግሥታዊ ለሆኑ ጥሪዎች ለአብነትም በኮሮና ወረርሽኝ ጊዜ ከአስር ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ በማድረግ ብዙዎችን አግዛለች። «ገበታ ለአገር» ለተሰኘው ፕሮጀክትም እንዲሁ አምስት ሚሊዮን ብር ድጋፍ ያደረገች ሲሆን፤ በቀጣይም አገርና ህዝብን በሚጠቅም ማንኛውም የልማት ሥራ ተሳትፎዋን እንደምታጠናክር አረጋግጣለች።

የትናየት «እርስ በእርስ ከመወነጃጀል ወጥተን አገርን ከፍ በሚያደርግ ሥራ ላይ እንጠመድ፤ በሚከፋፍለን፣ በሚያራርቀንና የልጆቻችን ነገ የሆነችውን ኢትዮጵያን በሚያጠፋ ተግባር ውስጥ ገብተን ተባባሪ አንሁን» የሚል መልዕክቷን በማስተላለፍ ሀሳቧን ቋጭታለች።

# ስፖርት






# የከዋክብት እንስቶች የማራቶን ፍጥጫ

**ቦጋስ አበበ**

ከአለማችን ትልልቅ የማራቶን ውድድሮች ዋነኛው የለንደን ማራቶን ነገ ይካሄዳል። ይህ ታላቅ የሩጫ ድግስ እንዳለፉት አመታት ሁሉ ዘንድሮም በርካታ የአለም ከዋክብት አትሌቶችን በአንድ ላይ የሚያፋልም ሲሆን በዚህ አመት ግን በአርባ ሁለት ኪሎ ሜትሩ ውድድር የሚፎካከሩ የርቀቱ ፈርጦች ቁጥር መበርከቱ የተለየ አድርጎታል። በወንዶች መካከል የሚካሄደው ውድድር በበርካታ ከዋክብት አትሌቶች እንደሚደምቀው ሁሉ በሴቶች መካከል የሚደረገውም ፉክክር የበለጠ በኮከቦች የደመቀ ነው።በዚህም ርቀቱን ከ2:18 ሰአት በታች ማጠናቀቅ የቻሉ ስድስት ሴት አትሌቶችን ጨምሮ በርካታ የረጅም ርቀት ከዋክብቶች ለመጀመሪያ ጊዜ እርስበርስ ይፋለማሉ። ከእነዚህ መካከል ዋና ዋናዎቹን በጥቂቱ እንመልከት።

በነገው የለንደን ማራቶን ኬንያዊቷ አትሌት ብሪጊድ ኮስጌ ከሌሎች የበለጠ ትኩረት ያገኘች አትሌት ነች። በ2019 የቺካጎ ማራቶን 2:14:04 ሰአት በመሮጥ የርቀቱን የአለም ክብረወሰን በሰላሳ ሰከንድ ማሻሻል የቻለችው ይህች አትሌት የተለየ ትኩረት ቢሰጣት አይገርምም። 2019 እና 2020 ላይ የለንደን ማራቶንን በተከታታይ ያሸነፈችው ኮስጌ ዘንድሮ ሶስተኛ ድሏን አልማለች። ኮስጌ በአጠቃላይ ዘንድሮ በለንደን ማራቶን ስትፎካከር አራተኛዋ ሲሆን ከሁለቱ ተከታታይ ድሎቿ ባሻገር 2018ና 2021 ላይ ሁለተኛ ሆና ማጠናቀቋ ይታወሳል።

ያለፈው ውድድር አሸናፊዋ ኢትዮጵያዊት አትሌት ያለምዘርፍ የኋላው ዳግም ለቻምፒዮንነት




በነገው የለንደን ማራቶን በርካታ የርቀቱ ፈርጦች የሚያደርጉት ፉክክር ይጠበቃል፣

የታጩች ሲሆን፤ የአለም አስራ ሁለተኛው ፈጣን ሰአት ባለቤት ናት። ይህም ሰአቷ(2:17:23) ከአመት በፊት በሃምቡርግ ማራቶን ያስመዘገበችው ነው። ይህም ማራቶንን ለመጀመሪያ ጊዜ በሮጠች አትሌት የተመዘገበ ፈጣኑ ሰአት እንደሆነ ይታወቃል። ያለምዘርፍ ለመጀመሪያ ጊዜ በለንደን ማራቶን ተሳትፋ ባለፈው አመት ስታሸንፍ መሃል ላይ ወድቃ እንደነበር ይታወሳል። ያምሆኖ ያስመዘገበችው 2:17:26 ሰአት በለንደን ማራቶን ታሪክ ሶስተኛው ፈጣን ሰአት ነው።

ባለፉት ቅርብ አመታት በመካከለኛና ረጅም ርቀት የመም ውድድሮች ከዋክብት የነበሩ በርካታ አትሌቶች ፊታቸውን ወደ ማራቶን እያዞሩ ይገኛሉ። በርካቶቹ በአትሌቶችም በነገው የለንደን ማራቶን በአንድ ላይ የ42 ኪሎ ሜትር ፉክክር ያደርጋሉ። ከነዚህ መካከል ኢትዮጵያውያኑ ከዋክብት አልማዝ አያናና ገንዘቤ ዲባባ ባለፈው አመት የመጀመሪያ የማራቶን ውድድራቸውን አምስተርዳም ላይ ማድረጋቸው የሚታወስ ሲሆን በ2016 ሪዮ ኦሊምፒክ የ10ሺ ሜትር ክብረወሰንን መስበር የቻለችው አልማዝ በ2:17:20 በሆነ ሰአት አሸናፊ ስትሆን ገንዘቤ ሁለተኛ ሆና ነበር ያጠናቀቀችው። ሁለቱ ኢትዮጵያውያን ከዋክብት ባለፉት ቅርብ አመታት በተለይም በ5ሺ ሜትር ያሳዩትን ድንቅ ፉክክር በታላቁ የማራቶን ውድድር ከሌሎች የርቀቱ ፈርጦች ጋር ይደግማሉ ተብሎ በጉጉት ይጠበቃል።

ትውልደ ኢትዮጵያዊቷ የኔዘርላንድስ አትሌት ሲፈን ሃሰን ባለፈው ቶኪዮ 2020 ኦሊምፒክ በ5እና 10ሺ ሜትር የወርቅ በ1500 ሜትር ደግሞ የነሐስ ሜዳሊያ ካጠለቀች በኋላ የመም ውድድር ስኬታማ ዘመኗም ባለፈው አመት የአለም ቻምፒዮና ሲጠልቅ ታይቷል። በዚህም ፊቷን ወደ ማራቶን አዙራ በነገው የለንደን ማራቶን የመጀመሪያ ፍልሚያዋን ታደርጋለች። ሲፈን በቶኪዮ ኦሊምፒክ ዋዜማ የአልማዝ አያናን የ10ሺ ሜትር የአለም ክብረወሰን መስበር ብትችልም 48 ሰአት ሳይሞላው በኢትዮጵያዊቷ ድንቅ አትሌት ለተሰነበት ግደይ መነጠቋ ይታወሳል።

ግዙፍ የአትሌቲክስ ስኬት ካላቸው ከነዚህ አትሌቶች በተጨማሪ በርካታ ጠንካራ ኢትዮጵያውያን አትሌቶችም በነገው ፉክክር ቀላል ተፎካካሪ እንደማይሆኑ ይጠበቃል። ከነዚህ መካከል 2022 ላይ በዚሁ ለንደን ማራቶን 2:18:32 በሆነ ሰአት ሶስተኛ ሆና ያጠናቀቀችው መገርቱ አለሙ ተጠቃሽ ነች። የነገው ውድድሯም ለንደን ላይ ሶስተኛዋ ሲሆን 2020 ላይ አምስተኛ ደረጃን ይዛ ማጠናቀቋ አይዘነጋም። 2017 ላይ በማራቶን መወዳደር የጀመረችው ይህች አትሌት የነገው ውድድሯ አስራ አራተኛ ይሆናል።

## በድጋሚ የወጣ ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ

የደቡብ ወሎ ዞን ማረሚያ ቤቶች መምሪያ/ ደሴ ማረሚያ ቤት/ በስሩ ለሚገኙ የህግ ታራሚዎች ለምግብ ማብሰያ የሚውል:-

የባህር ዛፍ የማገዶ እንጨት / ከግንቦት 1 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ማቅረብ የሚችሉ ነጋዴዎች ለአንድ ዓመት በማጫረት ከአሸናፊው ጋር ውል ለመያዝ ይፈልጋል፡፡

**ስለዚህ፡-**

1. በዘርፉ በዘመኑ የታደሰ ሕጋዊ ንግድ ፈቃፈድ ያላቸውና የዘመኑን ግብር የከፈሉ ለመሆናቸው ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
2. የግዥው መጠን ብር 200,000.00 /ሁለት መቶ ሺህ ብር / እና በላይ ከሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የተመዘገቡ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፡፡
3. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ በጨረታ ሰነዱ ላይ የተቀመጠውን ብዛት የሞሉትን የጠቅላላ ዋጋ ድምር ብር በአንድ ዓመት አባዝተው የዚያን 1% በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ፣ በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና/በአማርኛ የተተረጐመ/ ወይም በመ/ቤቱ ገንዘብ ያዥ በጥሬ ገዙብ በመሂ/1 ማስያዝ ይኖርበታል፣
4. በጨረታው መወዳደር የሚፈልግ ተጫራች የጨረታውን ሰነድ ከደሴ ማረ/ቤት ቢሮ ቁጥር 8 በመቅረብ የማይመለስ ብር 50.00 /ሃምሣ ብር / ከፍሎ መውሰድ ይቻላል፡፡
5. ተጫራቾች ማስታወቂያው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ተከታታይ የሥራ ቀናት ከቀኑ 8:30 ድረስ የጨረታ ሰነዳቸውን ሞልተው በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ አድርገው በደቡብ ወሎ ደሴ ማረሚያ ቤት ቢሮ ቁጥር 9 ለዚሁ በተዘጋጀ ሣጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡
6. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ጨረታው በተዘጋበት ቀን ከቀኑ 8.30 ሰዓት ታሽጐ 9:00 ሰዓት ይከፈታል፡፡ ቀኑ ቅዳሜና እሁድ ወይም የበዓል ቀን ከሆነ የሚቀጥለው የሥራ ቀናት ከቀኑ 8:30 ሰዓት ታሽጐ 9:00 ሰዓት ይከፈታል፡፡
7. የጨረታው አሸናፊ በአሸነፉት መሰረት ውል ባይወስዱ ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ገንዘብ ከመንግሥት ገቢ ይሆናል፡፡ አሸናፊ ከሆኑ በኋላ ያሸነፉበትን የማገዶ እንጨት ማረ/ቤቱ ድረስ በራሱ ወጪ ያስረክባል፡፡
8. አንዱ ባቀረበው የጨረታ ዋጋ ላይ ተንተርሶ ሌላው ማቅረብ የለበትም
9. አቅርቦቱን በተመለከተ ማረ/ቤቱ በሚፈልገው መጠንና ልክ መሰረት ወር ከመግባቱ በፊት ከ25–30 ቀን ድረስ የወሩን የማገዶ እንጨት አጠቃሎ ማቅረብ የሚችል መሆን አለበት፡፡
10. የጨረታው አሸናፊ የውል ማስከበሪያ 10% የአንድ ዓመት ጠቅላላ ዋጋ የሚያሲይዝ ሲሆን ተጫራቾች ማብራሪያ የሚፈልግ ቢሮ ቁጥር 9 በመምጣት ወይም በስልክ ቁጥር 0331116516 በመደወል ማብራሪያ መጠየቅ ይቻላል፡፡
11. ለታራሚዎች በአማካይ በየወሩ የሚቀርብ የማገዶ እንጨት ብዛት በጨረታ ሰነዱ ላይ የሚገለጽ ይሆናል
12. መ/ቤቱ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ ሙብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ማረሚያ ቤቶች መምሪያ**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

በከሳሽ፡- ፌ/ጠ/ዐ/ህግ እና በተከሳሽ፡- ሰኢድ ነገያ ኡመር መካከል ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 5ኛ ችሎት ባለው ኮንትሮባንድ ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ በ24/08/2015 ዓ.ም በ3፡30 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡ ተከሳሽ በቀጣይ ቀጠሮ ባይቀርቡ በሌሉበት ፍርድ እንደሚሰጥ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

በከሳሽ፡- ፌ/ጠ/ዐ/ህግ በተከሳሽ፡- 3ኛ አደፍርስ ሀብቴ ገ/ህይወት መካከል ስላለው አራጣ ወንጀል ክስ ጉዳይ በ24/8/2015 ዓ.ም ሲሆን ቀነ ቀጠሮ በ4፡00 ሰዓት ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 3ኛ ጉ/ታክስ ወንጀል ችሎት እንዲቀርቡ ባይቀርቡ ከሆነ ግን ክሱ በሌላችሁበት ታይቶ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑ አውቃችሁ በእለቱ እንድትቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት**

በይግባኝ ባይ ፌ/ጠ/ዐ/ህግ እና መልስ ሰጭ ታገሰ ገ/ማርያም ሚልኬሶ ወንጀል ጉዳይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግላቸው ፍ/ቤቱ በ22/7/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት አዟል፡፡ በዚህ መሰረት መ/ሰጭ የሆኑት 1ኛ ታገሰ ገ/ማርያም ሚልኪሶ በ25/8/2015 ዓ.ም 3፡30 ሰዓት በፌ/ከ/ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ 6ኛ ወንጀል የይግባኝ ሰሚ ችሎት ድረስ እንድትቀርቡ አዟል፡፡ በቀጠሮ ቀን የማይቀርቡ ከሆነ ግን ጉዳዩ በሌሉበት የሚታይ መሆኑን ፍርድ ቤቱ አሳውቃል፡፡

**የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቦሌ ምድብ ችሎት**

በከሳሽ/አመልካች፡- ተስፋጋብር ኪዳነማሪያም አብርሃ እና በተከሳሽ/ተጠሪ፡- ወ/ሮ አከበረት ባህታ መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ 1ኛ ቤተሰብ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ/ተጠሪ በ24/8/2015 ዓ.ም በ8፡30 ሰዓት መልስ ለመቀባበል በ25/8/2015 ዓ.ም በ9፡00 ሰዓት ለስምምነት 01/09/2015 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት ክስ ለመስማት ላሉት ቀጠሮዎች እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

የባለንብረት ስም ሀ/ማሪያም ማዘንጊያ በዛብህ የሠሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-79060 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር WJME3TRE2GC329382 ሞዴል AT380T38H የሞተር ቁጥር F3BEE681G*B220-242188* የሊብሬ ቁጥር 0141808 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ4/8/2015 አመልከተዋል፡፡

ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፍቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ንፋስ ስልክ ላፍቶ ቅ/ጽ/ቤት**